በታጣው ፡ ሰው ፡ ፈንታ ፡ ሲጠፋ ፡ እሚተካ ፤
ያግር ፡ እንጀራውን ፡ ሊጋግር ፡ ሊያቦካ ፤

ይገደዳል ፡ የግድ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ እንደከብት ፤
ይህ ፡ ነውና ፡ ጥንትም ፡ የሕይወቱ ፡ ሥርዓት ።

ነበረ ፡ ተለምዶ ፡ ተንቀባርሮ ፡ ኑሮ ፤
ብስጭት ፡ ተተካ ፡ ካሁኑ ፡ ጀምሮ ።

ባሌ ፡ እኔን ፡ ቢወደኝ ፡ እኔ ፡ ርሱን ፡ ብወደው ፤
አካባቢው ፡ ካለ ፡ መቼ ፡ የሚሆን ፡ ነው ።

አንድ ፡ አካል ፡ በሆኑ ፡ በተመሳሰሉ፤
ለማፍረስ ፡ ጋብቻን ፡ ጣልቃ ፡ ይገባሉ ።

በመልኩ ፡ ሁሉንም ፡ እይዛለሁ ፡ ብል ፤
ከዚያም ፡ ከዚያ ፡ ሳልሆን ፡ ቀረሁ ፡ በማህል ።

ያልተወለደ ፡ ልጅ ፤ ልጅ ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፤
መመኘት ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡ ይሄዳል ፡ ኮብልሎ ።

ያልተወለደ ፡ ልጅ ፡ ያሳያል ፡ ጥላቻ ፤
ይጥላል ፡ አጋልጦ ለመዘባበቻ ።

ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ጣጣ ፤ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ጭንቅ ፤
እያሳደጉ ፡ ልጅ ፡ መኖር ፡ በድብቅ ።

የትዳር ፡ ጋጋታው ፤ ለምን ፡ ነው ፡ ሁካታው ፤
ገብይቶ ፡ ደስታን ፡ ትርፉ ፡ መከራ ፡ ነው ።

ትዳር ፡ ትዳር ፡ ብዬ ፡ የጓጓሁለት ፤
ያን ፡ ዛላ ፡ ያን ፡ ውበት ፡ የሠዋሁለት ፤

አጋለጠኝ ፡ እንጂ ፡ ምን ፡ ጠቀመኝ ፡ ከቶ ፤
በተስፋ ፡ ለተስፋ ፡ የሚኖረው ፡ ጓጉቶ ፤
መቼም ፡ ተስፋ ፡ አይቆርጥም ፡ ይህን ችግር ፈርቶ ።



ክፍል ፡ ፯ ፡

# የወይዘሮ፡ ዘነበች፡ የገዳም ፡ኑሮ ፡

ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ከሚቹ ፡ ባላቸው ፡ ጋር ፡ ያፈሩትን ፡ ማናቸውንም ፡ ሀብት ፡ ለልጃቸው ፡ አስረክበዋል ። ባል ፡ ፈትተው ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ እንደተቀመጡ ፤ በድካማቸው ፡ ወደ ፡ ሠሩት ፡ ቤት ፡ እንዲመለሱ ፡ ቢጠየቁ ፤ አለመወሰናቸውን ፡ አስታውቀውን ፡ ነበር ። ነገሩን ፡ ረስተነው ፡ በሰላማዊ ፡ ኑሮ ፡ ላይ ፡ እንዳለን ፤ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የማነጋግራችሁ ፡ ጉዳይ ፡ አለኝ ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፤ ፀሐይ ፡ ደንገጥ ፡ አለችና ፡ ምነው ፡ እማማ ፡ ምን ፡ ጉዳይ ፡ አገኘሽ ፡ ብላ ፡ ጥያቄ ፡ አቀረበች ።

ርሳቸውም ፡ ቀጠል ፡ አድርገው ፤ የማያስደነግጠው ፡ ያስደነግጥሻል ። ልነግራችሁ ፡ ካሰብኩ ፤ ሰንብቻለሁ ። ያንቺን ፡ ድንጉጥነት ፡ እያስታወስኩ ፤ ሳልነግራችሁ ፡ ዘገየሁ ። አኗኗሬን ፡ ገና ፡ ያልወሰንኩ ፡ ስለሆነ ፤ ወደፊት ፡ ወስኜ ፡ እንደምነግራችሁ ፡ ገልጬላችሁ ፡ ነበር ። ራሴን ፡ በራሴ ፡ አነጋገርኩ ። ጥሪ ፡ እስኪደርሰኝ ፡ ድረስ ፡ ማንኛውንም ፡ መንገድ ፡ መከተል ፡ እንደሚሻለኝ ፡ ከልብ ፡ አሰብኩ ። አስተያየቴ ፡ በአንድ ፡ አቅጣጫ ፡ ሳይወሰን ፡ በብዙ ፡ ሁኔታዎች ፡ ተመራመረ ። እስካሁን ፡ ባለኝ ፡ ዕድሜ ፡ በዚህ፡ዓለም ፡ ያገኘሁትን ፡ ትርፍ ፡ አስታወስኩ ። «ቢከፍቱት ፡ ተልባ» እንደሚባለው ፡ ከድካም ፡ በቀር ፡ ይህን ፡ አተረፍኩ ፡ የምለው ፡ ፈጽሞ ፡ የለም ፡ እንዳልል ፡ አንቺ ፡ ከሰውነቴ ፡ ተከፍለሽ ፡ መገኘትሽን ፡ ብቻ ፡ እንደትርፍ ፡ ስቈጥረው ፡ ሌላው ፡ ከንቱ ፡ ድካም ፡ ነው ።

ይህ ፡ ያለፈ ፡ ሲሆን ፤ ወደፊት ፡ ምን ፡ አገኛለሁ ፡ ብዬ ፡ ሳስብ ፤ ሰውነቴ ፡ እየተዳከመ ፤ ውበቴና ፡ ለዛዬ ፡ እየጠፋ ፤ ዓለምን ፡ ስንቅ ፤ በዓለም ፡ ዘንድ ፡ እኔም ፡ የተናቅሁ ፡ እሆናለሁ ።

እንግዲህ ፡ በመጨረሻ ፡ የሚጠብቀኝ ፡ ዕድል ፡ ይህ ፡ ከሆነ ፤ ለምን ፡ ልበጥበጥ ፡ ብዬ ፡ የመከብብ ፡ እናት ፡ በመጨረሻ፡ጊዜ ፡ የመረጡትን ፡ ከማድነቅና ፡ ከማመስገን ፡ ጋር ፡ ስለመረጥኩ ፤ ርሳቸው ፡ የተከተሉትን ፡ ዓላማ ፡ ተከትዬ ፡ የጥሪ ፡ ደብዳቤዬን ፡ ልጠባበቅ ፡ ምርጫ ፡ ስላደረግሁ ፤ ሐሳቤን ፡ ብታውቁልኝ ፡ እወዳለሁ ፡ አሉ ።

ፀሐይ ፡ የእናትዋን ፡ ሐሳብ ፡ ባወቀች ፡ ጊዜ ፤ በዚያ ፡ በሚያም ረው ፡ ዓይንዋ ፡ ዕንባዋን ፡ እያፈሰሰች ፡ አለቀሰች ። እናትዋም ፡ ልጄ እባክሽን ፡ ሆደ—ባሻ ፡ አትሁኝ ። በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሆደ—ባሻ ፡ ሰዎች ፡ መኖር ፡ አይችሉም ። በኖርን ፡ መጠን ፡ ከዓለም ፡ የምናገኘው ፡ ትምህርት ፡ ራሳችንን ፡ በራሳችን ፡ እያጽናናን ፡ እንድንቆይ ፡ ነው። እንደሰው፡ ፈቃድ ፡ ቢሆንማ ፡ አንቺና ፡ እኔ ፡ ሳንለያይ ፡ እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ ድረስ ፡ አብረን ፡ ብንኖር ፡ እወድ ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ እያወቅንና ፡ እያ ደግን ፡ ስንሔድ ፡ የኑሮ ፡ ግዴታ ፡ ያለያየናል ።

ከዚህ ፡ የባሰ ፡ ሌላ ፡ ደግሞ ፡ እንዳለ ፡ እስቲ ፡ እናስታውስ ። ለደ ቂቃ ፡ ተለያይተው ፡ መልሰው ፡ እስኪገናኙ ፡ የሚነፋፈቁት ፡ ለዘለዓ ለም ፡ በማያገናኘው ፡ ሞት ፡ ይለያዩ፡የለም ? ሰው ፡ ከሰው ፡ ለመገናኘት፡ ምንጩ ፡ ሰው ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ራሱን ፡ በራሱ ፡ ያቆ ማል ፤ ሲለይም ፡ ራሱ ፡ ይለያል ፡ እንጂ ፡ ይዞ ፡ ወይም ፡ አስከትሎ ፡ አይሄድም ። ዓለም ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ያስተምረናል ።

በፍቅር ፡ በመተሳሰባችን ፡ ደስ ፡ ይለኛል፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ በዚህ፡ ዓለም ፡ የሚደረገው ፡ ወይም ፡ የሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ለጊዜ ፡ ማሳ ለፊያ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ሁሉም ፡ እንዳልነበር ፡ ይሆናል ፡ አሉ ፡ ወይዘሮ፡ ዘነበች ።

እማማ ፡ አለች ፡ ፀሐይ ፤ ሆዴ ፡ ስለባባ ፡ አለቀስኩ ፡ እንጂ ፡ ቆር ጠሽ ፡ የተነሳሽበትን ፡ በኔ ፡ ለቅሶ ፡ እንደማትተይው ፡ ዐውቃለሁ ። ያለቀስኩት ፡ ያለፈውን ፡ አስታውሼ ፡ ነው ፤ የመክብብን ፡ እናት ፡ ወድ ጃቸው ፡ በመግባባት ፡ ስኖር ፤ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከኛ ፡ ተለይ ተው ፡ ለመኖር ፡ ያላቸውን ፡ ፈቃድ ፡ ገለጡልን ፤ ማስቀረት ፡ አልቻ ልንም ።

እማማ ፤ ሁሉንም ፡ ከመረመርሽ ፡ በኋላ ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ያለ ውን ፡ ዕድሜሽን ፡ በአንድ፡በተወሰነ፡ ሰዓት ፡ ለማሳለፍ ፡ መረጥሽ ፤ ይህ፡ ምርጫሽ ፡ እንዲሰናከል ፡ አልፈልግም ። «ሰውነቴ ፡ እየተዳከመ ፤ ውበ ቴና ፡ ለዛዬ ፡ እየጠፋ ፤ ዓለምን ፡ ስንቅ ፡ እኔም ፡ በዓለም ፡ ዘንድ ፡ የተ ናቅሁ ፡ እሆናለሁ ፡ » ያልሽው ፡ የሚታለፍ ፡ አይደለም ።

በዚህ ፡ ዓለም ፡ ከለዛውና ፡ ከውበቱ ፡ ጋር ፡ የሚቆይ ፡ ወይም ፡ የሚ ያረጅ ፡ የለም ። ከዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚገኘው፡ ቅርስ ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ብቻ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ሐሳብሽ ፡ እንዲሟላ ፡ እንመኝልሻለን ፡ አለቻቸው ።



በጣም ፡ አመሰግናለሁ ፡ አሉና ፡ በአንድ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ተወ ስኖ ፡ መቀመጥ ፡ ብቻ ፡ አገልግሎት ፡ አይሆንም ። በጤናና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታ ፡ ተዳክመው ፡ የሰው ፡ ርዳታ፡ የሚፈልጉትን ፡ በጉልበቴ፡ ለመርዳት ፡ እፈልጋለሁ ። ከሰው ፡ ርዳታ ፡ የሚፈልጉ ፡ በብዛት ፡ የሚ ገኙበት ፡ ዋልድባ ፡ መሆኑን ፡ ስለሰማሁ ፤ ይህንኑ ፡ ገዳም ፡ መርጫለሁ ፤ ብለው ፡ መልስ ፡ ሰጡ ፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበች ።

በውይይታቸው ፡ ጣልቃ፡ በመግባት ፡ በአንድ ፡ በተወሰነ ፡ ቤት፡ ወይም ፡ ቦታ ፡ መቀመጥ ፡ በሽታ ፡ ይሆናል ። ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ እየተዘ ዋወሩ ፡ መሥራት ፡ ሰውነትን ፡ ስለሚያጠነክር ፡ መልካም ፡ እስበዋል። የመረጡት ፡ ገዳም ፡ ከሰው ፡ ርዳታ ፡ የሚፈልጉ ፡ ብዙ ፡ ደካማዎች ፡ እንዳሉበት ፡ ሰምቻለሁ ። ለኛ ፡ ግን ፡ ይርቃል ፤ ቢሆንም ፡ የርስዎን ፡ ሐሳብ ፡ ካጠቃለለ ፡ ለኛ፡ ቢርቅም ፡ ምንም ፡ አይደለ ፡ ብዬ ፡ ምክሬን፡ አካፈልኳቸው ።

ሐሳባቸው ፡ በኛ ፡ በልጆቻቸው ፡ ስለተደገፈ ፡ ደስ ፡ አላቸውና ፡ እየመላለሱ ፡ ከአመሰገኑ፡ በኋላ ፤ የሚያስፈልጋቸውን ፡ ከፀሐይ ፡ ጋር፡ እየተመካከሩ ፡ ማዘጋጀት ፡ ጀመሩ ። ወራቱ ፡ ጥር ፡ ስለነበር ፤ ጥምቀ ትን ፡ ከኛ፡ ጋር ፡ ውለው ፡ የሁዳዴ ፡ ጾም ፡ ሲገባ ፡ ሳምንት ፡ ሲቀረው፡ ሔዱ። ሥፍራውን ፡ ለማወቅና ፡ ማናቸውንም ፡ ሁኔታ ፡ ለመመልከት፡ እኔ ፡ አብሬአቸው ፡ ሄድኩ ።

ገዳሙ ፡ በጫካ ፡ የዳበረ ፤ ከአዕዋፍ ፡ በቀር ፡ የሰው ፡ ድምፅ ፡ የማ ይሰማበት ፡ ስለሆነ፤ ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ አይለምዱት ፡ ይሆን ? በማለት፡ ሥጋት ፡ ያዘኝ ። በብዙ ፡ ቤተሰብ ፡ መካከል ፡ የኖሩ ፡ ከሰው ፡ ተለይ ተው ፡ በዚህ ፡ ጫካ ፡ እንደምን ፡ ይኖራሉ ፡ እያልኩ ፡ ከማሰቤ ፡ የተ ነሣ ፡ «እመየቴ ፡ ኧረ ፡ የሚዘልቁት ፡ አይመስለኝም ። ሐሳብዎን ፡ ለውጠው ፡ እንመለስና ፡ ለኛ ፡ ቅርብ ፡ ከሚሆነው ፡ እናቴ ፡ ከነበረች በት ፡ ሆነው ፡ አገልግሎትዎን፡ ቢቀጥሉ ፡ የሚሻል ፡ ይመስለኛል ፡ አል ኳቸው ። «አይደረግም፡ አሉና ፡ ሰው ፡ ለሥጋዊ ፡ ምቾቱና ፡ ደስታው፡ ካሰበ ፤ በዚህ ፡ ሊኖር ፡ አይችልም ፤ ካላሰበ ፡ የሚመረጠው ፡ ይህ ፡ ዓይ ነቱ ፡ ሥፍራ ፡ ነው» ፡ እያሉ ፡ ሲገዙ ፤ ሰዎች ፡ ከሚኖሩበት ፡ ደረስን። ግሁሳን ፡ የሆኑ ፡ ለማየት ፡ የሚያስፈሩና ፡ ግርማ—ሞገስ ፡ በላያቸው ፡ ላይ ፡ የሠፈረባቸው ፡ ሰዎች ፡ አገኘን ።

ከድንጋጤ ፡ ጋር ፡ ሰላምታ ፡ ብንሰጣቸው ፤ ሐሳባቸው ፡ በሌላ ፡ የተመሰጠ ፡ በመሆኑ ፤ ማንንም ፡ ባለመመልከታቸው ፡ ለሰላምታችን፡ መልስ ፡ ሳይሰጡን ፡ ቀሩ ።

ወይዘሮ ፡ ዘነበችና ፡ እኔ ፡ በዝግታ ፡ እርምጃ ፡ ስንሄድ ፡ ሰው ፡ ተቀብለው ፡ የሚያነጋግሩትን ፡ አገኘን ። የእንግድነትና፡ የአክብሮት፡ አቀባበል ፡ ካደረጉልን ፡ በኋላ ፤ የሔዱበትን፡ ዓላማ ፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበች፡ ገልጠው ፡ አስረዱ ።

የገዳሙ ፡ አበ—ምኔት ፡ የወይዘሮ ፡ ዘነበችን ፡ ሐሳብ ፡ ካዳመጡ ፡ በኋላ ፤ ፈተናውን ፡ ከቻልሽ ፡ ሐሳብሽ ፡ መልካም ፡ ነው ። ይልቁንም ፡ በዚህ ፡ ያለው ፡ ችግር ፡ የጉልበት ፡ ርዳታ ፡ ለሚያስፈልጋቸው ፡ በቅርብ ፡ ሆኖ ፡ አገልግሎት ፡ የሚሰጥ ፡ ማግኘት ፡ ነው ። ከፍ ፡ ያለውን ፡ ችግር ፡ የሚያቃልል ፡ ሐሳብ ፡ ያለሽን ፡ ስንቀበል ፤ ሐሳብሽን ፡ ፈጽመሽ ፡ ዋጋሽን ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንድታገኚ ፡ እንመኝልሻለን ፡ አሉና ፡ ሥፍራውን ፡ አንድ ፡ በአንድ ፡ አስጐበኙዋቸው ። እየተዘዋወሩ ፡ ሲመለከቱ ፤ እኔም ፡ ነበርኩ ፤ በታው ፡ የደስ—ደስ ፡ ያለው ፤ የሽታው ፡ መዓዛ ፡ መንፈስን ፡ የሚመግብና ፡ የሚያድስ ፡ ነው ። እንኳን ፡ አስበው ፡ የሔዱት ፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ይቅሩና ፡ ለማድረስ ፡ የሄድኩት ፡ እኔም ፡ ተማረኩ ።

ሀብትና ፡ ሥልጣን ፡ ቢኖር ፡ ወይም ፡ ከትልቅ ፡ ቤተሰብ ፡ ቢወለዱ ፤ የመንፈስ ፡ ፀጥታና ፡ ደስታ ፡ ሰው ፡ ከተነሣው ፡ ሕይወታዊ ፡ ኑሮው ፡ ሁሉ ፡ ታማሚ ፡ ነው ። ሰው ፡ የመንፈስ ፡ ፀጥታና ፡ ደስታ ፡ ካገኘ፤ ሳይመገብ ፡ ጠግቦ ፡ ያድራል ። ሳይታመም ፡ አያሌ ፡ ዘመናት ፡ መኖር ፡ ይችላል። ከዚህ ፡ አሁን ፡ ማን ፡ አለ ፤ ውስጡና ፡ አካባቢው ፡ መዓዛ ፡ ስላለው፡ መንፈስን ፡ ያድሳል ። አሁን ፡ የተሰማኝን ፡ ያህል፡ የመንፈስ ፡ ደስታ ፤ እስካሁን ፡ ባለው ፡ ሕይወቴ ፡ ካገኘሁት ፡ ጋር ፡ አይመዛዘንም ፡ አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ በተመስጦ ።

ፀሐይ ፡ የኑሮ ፡ ጓደኛ ፡ እንድትሆነኝ ፤ ባገኘኋት ፡ ጊዜና ፡ ካገኘኋትም ፡ በኋላ ፡ ይሰማኝ ፡ የነበረው ፡ የመንፈስ ፡ ደስታ ፡ የመጨረሻ ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ አምኜ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ባለሁበት ፡ የሚሰማኝ፡ የውስጥ፡ ደስታ ፡ ስለተለያየብኝ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ ለማስረዳት ፡ ቃላት ፡ እንኳን ፡ አላገኘሁም ።



ጉብኝቱን ፡ ስንጨርስ ፡ ለወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ልዩ ፡ የማረፊያ ፡ቦታ ተሰጣቸው ። በጤናና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያት ፡ ለተዳከሙት ፡ አገልግሎት ፡ ለመስጠት ፡ ሥራ ፡ ሲጀምሩ ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ተመለስኩ ።

በፀሐይና ፡ በኔ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ የመተሳሰብ ፡ ፍቅር ፡ ጊዜ ፡ የማይለውጠው ፡ ስለሆነ ፤ ከቤቴ ፡ ስደርስ ፤ ከፀሐይ ፡ ጋር ፡ አንገት ፡ ለአንገት ፡ ተያይዘን ፡ በአጭር ፡ ቀናት ፡ ባደረግነው ፡ መለያየት ፤ የተሰማንን ፡ ናፍቆት ፡ ከተገላለጥን ፡ በኋላ ፤ ስለእናትዋ ፡ ደኅንነት ፡ እንዴህ ፡ ብላ ፡ ጠየቀችኝ ። ውዴ ፡ ሆይ ፡ እማማ ፡ ደኅና ፡ ደረሰች ? ወደፊት ፡ ኑሮዋ፡ እንደምን ፡ ይመስልኻል ? ፈተናውን ፡ የምትቋቋመው ፡ ይመስልኻል ፡ ፍቅሬ ፡ ሆይ ! በደኅና ፡ ደርሰዋል ? ፈተናውን ፡ የምትቋቋመው ፡ ይመስልሃል ? ያልሽው ፡ ጥያቄ ፡ ጥሩ ፡ ነው ። እንደደረስን ፡ የተቀበሉን ፡ አረጋዊ ፡ «ፈተናውን ፡ ከቻልሽ ፡ ሐሳብሽ ፡ ጥሩ ፡ ነው» ፡ አልዋቸው ።

በሥፍራው ፡ ስንደርስ ፡ ከአዕዋፍ ፡ በቀር ፡ ሰውም ፡ አይታይም ፡ ድምፅም ፡ አይሰማም ። እንዲያውም ፡ ሥፍራው ፡ ያስፈራል ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ የሚዘልቁት፡ አይመስለኝም። ሐሳብዎን ፡ ይለውጡና ፡ እንመለስ። ዓላማዎን ፡ ከፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፡ የኔ ፡ እናት ፡ በነበረችበት ፡ ይቀመጡ ፡ አልኳቸው ።

ርሳቸው ፡ ግን ፡ የተነሡበትን ፡ ዓላማ ፡ ከግቡ ፡ ለማድረስ ፡ የቆረጡ ፡ ስለሆነ፤ ሰዎች ፡ ወደ ፡ አሉበት ፡ ጉዞዋችንን ፡ እንቀጥል ፡ አሉኝ።

«ዝም ፡ አይነቅዝም » እንደሚባለው ፡ በዝምታ ፡ ስንጓዝ ፡ ወደ ፊታችን ፡ በሄድን ፡ መጠን ፡ መንፈስን ፡ የሚያለመልም ፡ ሽታ ፡ ሸተተን ። በሽታው ፡ መዓዛ ፡ መንፈሳችን ፡ ስለታደሰ ፡ በሕይወት ፡ ዘመናችን ፡ ያልገጠመን ፡ የመንፈስ ፡ ደስታ ፡ በሕዋሳታችን ፡ ውስጥ ፡ መላ ። በበኩሌ ፡ በወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ዕድል ፡ ቀናሁ ። ያንቺ ፡ነገር ፡ ሆኖብኝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እኔም ፡ በዚያው ፡ ብኖር ፡ በወደድሁ ። በልቦናዬ ፡ ያለውን ፡ ለአንቺ ፡ አልደብቅም ፡ በውነቱ ፡ ተማርኬ ፡ ነበር ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ በጉልበታቸው ፡ እያገለገሉ ፡ ትሩፋት ፡ ለማግኘት ፡ በመቊረጣቸው ፡ የተመኙትን ፡ አግኝተዋል ። የሰው ፡ ርዳታ ፡ የሚጠይቁት ፡ ብዙዎች ፡ ስለሆኑ ፡ ሥራው ፡ ይበዛባቸውና ፡ ይደክማሉ ፡ ብዬ ፡ ከመሥጋቴ ፡ በቀር ፤ በዚያ ፡ የሚገኘው ፡ ጸጋ

መንፈስን ፡ በደስታ ፡ ስለሚያረካና ፡ ሥጋን ፡ ስለሚያለመልም ፣ በዚያ ፡ በቅድስና ፡ ሥፍራ ፡ የቅድስና ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ መመረጥ ፡ ልዩ ፡ ዕድል ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ አስረዳኋት ።

ውዴ ፡ ሆይ ፣ ለእናቴ ፡ ስላደረግህላት ፡ ወሮታ ፡ አመሰግናለሁ ። አለችና ፡ ፀሐይ ፣ እናቴ ፡ ደስ ፡ ቢላት ፡ እንደምወድ ፡ ታውቃለህ ። ሰው ፡ በዋለበት ፡ በማናቸውም ፡ ዓይነት ፡ ተግባር ፡ ላይ ፡ ደስታ ፡ ከገጠመው ፡ የዓለም ፡ ትርፉ ፡ የድካሙም ፡ ውጤት ፡ ይህ ፡ ነው ። ደስታ ፡ ከራቀ ፡ ሥራ ፡ አይቃናም ። ሐሳብ ፡ የሚመነጨው ፡ ከአዕምሮ ፡ ሲሆን ፣ የሰው ፡ አዕምሮ ፡ በደስታ ፡ ከረካ ፡ የሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ይቃናል ።

እናቴ ፡ ደስ ፡ ካላት ፡ ብዙ ፡ የጉልበት ፡ ሥራ ፡ ብትሠራም ፣ ድካምዋ ፡ በምታገኘው ፡ ደስታ ፡ እየተዋጠ ፡ ሳታውቀውና ፡ ሳይሰማት ፡ ጊዜዋን ፡ ታሳልፈዋለች ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ስለምንጐበኛት ፡ የአኗኗርዋን ፡ አኳኋን ፡ ለመረዳት ፡ እንችላለን ፡ ብላ ፡ ሐሳብዋን ፡ ስትገልጥልኝ ፡ ልቤ ፡ በፍቅርዋ ፡ ተነካ ።

ፀሐይ ፡ በናትዋ ፡ መሄድ ፡ ተስምተዋት ፡ የነበረው ፡ ቅሬታ ፣ ደስታ እንጂ ፣ ኀዘን ፡ ወይም ፡ ብስጭት ፡ እናትዋን ፡ እንዳላገኛቸው ፡ ባወቀች ፡ ጊዜ ፡ ቅሬታዋና ፡ ኀዘንዋ ፡ ከሰውነትዋ ፡ ወጥቶ ፡ ሐሳቡዋ ፡ ወደ ፡ ቤትዋ የውስጥ ፡ አስተዳደር ፡ አዘነበለ ።

በከተማ ፡ የሚማሩ ፡ ልጆቻችን ፡ ለዕረፍት ፡ የሚመጡበት ፡ ጊዜ ፡ በመቃረቡ ፡ በዕረፍት ፡ ጊዜያቸው ፡ ስለሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ ጥናት ፡ ማድረግ ፡ እንዳለባቸው ፡ አሰባ ፣ ጌታዬ ! ልጆቻችን ፡ ለዕረፍት ፡ የሚመጡበት ፡ ጊዜ ፡ ተቃረበ ፣ ከመጡ ፡ በኋላ ፡ ይህን ፡ ይሥሩ ፡ ከማለት ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜያቸውን ፡ በሥራ ፡ ማሳለፍ ፡ እንዳለባቸው ፡ በመሠረቱ ፡ የተስማማንበት ፡ ስለሆነ ፣ የሥራውንም ፡ ዓይነት ፡ መመደብ ፡ ያለብን ፡ ይመስለኛል ። በአንተ ፡ በኩል ፡ ምን ፡ ሐሳብና ፡ አስተያየት ፡ አለ ፡ ብላ ፡ ፀሐይ ፡ ጠየቀችኝ ።

እንግዳ ፡ ነገር ፡ አታምጪ ፣ ወንድምሽ ፡ ነኝ ፡ እንጂ ፡ ጌታሽ ፡ አይደለሁም ፡ እንዳልኩ ፣ ምን ፡ የሚያስገርም ፡ ነገር ፡ አገኘህ ፡ መከብብ ፡ አለችና ፡ ከኛ ፡ በፊት ፡ የነበሩትን ፡ በእግዚአብሔር ፡ የተባረኩትን ፡ የነአብርሃምን ፡ ታሪክ ፡ ረሳኸው ? ወይስ ፡ የዛሬ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ኑሮ ፡ በገንዘብ ፡ ፍቅር ፡ የተመሠረተ ፡ እንጂ ፡ በውስጡ ፡ እውነተኛ ፡ ፍቅር ፡



እንደሌለ ፡ ልቦናህ ፡ ስለሚያውቅ ፡ አስገረመህ ? ሣራ ፡ አብርሃምን ፡ ጌታዬ ፡ ትለው ፡ አልነበረም ? መከባበራቸው ፡ ምን ፡ ጉዳቸው ። ርግጥ ፡ ነው ፡ የዘመኑ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ኑሮ ፡ ወግን ፡ ወይም ፡ ሥርዓትን ፡ ለማድረስ ፡ ጋብቻ ፡ ይፈጸማል ፡ እንጂ ፣ ዛሬ ፡ የተፈጸመ ፡ ጋብቻ ፡ ነገ ፡ ፍችን ፡ ሲያስከትል ፡ ይታያል ።

ከፍች ፡ የሚደርሱ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ የተባባሱት ፡ ናቸው ። ሌሎችስ ፡ አንድ ፡ ቤት ፡ አብረው ፡ በመቀመጣቸው ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ከመባላቸው ፡ በቀር ፡ መተማመን ፣ ፍቅር ፣ መተሳሰብ ፣ የሌለው ፡ ኑሮ ፡ ስለሆነ ፣ በየበኩላቸው ፡ እየተማሙ ፡ ያንዱን ፡ ቀድሞ ፡ ማለፍ ፡ አንዱ ፡ እየተመኘ ፣ «ኑሮ ፡ ካሉት ፡ መቃብር ፡ ይሞቃል ፣ »እንደተባለው ፡ ያለ ፡ ኑሮ ፡ ይኖራል ፡ በማለት ፡ ንግግሯን ፡ ልትቀጥል ፡ ስታስብ ፣ ፍቅሬ ፡ ሆይ ፣ ንግግርሽ ፡ ልቤን ፡ ስለነካው ፡ ይህ ፡ የሆነበት ፡ ምክንያት ፡ ምን ፡ ይመስልሻል ? ብዬ ፡ ጠየቅኋት ።

ዛሬ ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ የሚታየው ፡ ፍቅር ፡ ከልብ ፡ ያልሆነ ፡ በጥቅም ፡ የተሸፈነ ፡ ሆኖ ፣ ወረቱ ፡ ቶሎ ፡ ያልፍና ፡ ወደሌላ ፡ ይተላለፋል ። በዚያም ፡ አይቆይ ። እንደዚሁ ፡ ካንዱ ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ይንከራተታል ።

በመጀመሪያ ፡ በፍቅር ፡ ተፈላልጎ ፡ የተገናኘ ፡ ሰው ፡ በዚያው ፡ ሳይቀጥል ፣ እንደ ፡ ዓይን ፡ ብሌን ፡ አድርጎ ፡ ያይበት ፡ በነበረው ፡ ዓይን ፡ በጥላቻ ፡ መታየት ፣ በጥሩ ፡ አስደሳች ፡ ቃላት ፡ ልብ ፡ በተማረከበት ፡ አንደበት ፡ መስደብ ፣ ይዳስስበት ፡ በነበረው ፡ እጅ ፡ መደብደብ ፣ ይህ ፡ ከሰማይ ፡ የወረደ ፡ ቅጣት ፡ ነው ፣ ከማለት ፡ በቀር ፡ በኔ ፡ በኩል ፡ ሌላ ፡ ትርጉም ፡ አልሰጠውም ። በዚህ ፡ ዓለም ፡ እንዳማረበት ፡ ያለፈ ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ። ይህ ፡ ነገር ፡ ጣልቃ ፡ ገብቶ ፡ ስሜቴን ፡ የገለጥኩልህ ፡ ጌታዬ ፡ ብልህ ፡ ከመገረምህ ፡ የተነሣ ፡ ነውና ፡ በል ፡ የመጀመሪያውን ፡ ጉዳያችንን ፡ እንቀጥል ፡ አለች ፡ ፀሐይ ።

አይ ፡ ፀሐይ ! በኔና ፡ በአንቺ ፡ ሕይወት ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ እንደ ማይደርስብን ፡ ርገጠኞች ፡ ነን ፡ አልኩና ፡ የጀመርኩትን ፡ ልቀጥል ፡ ስል ፣ ይቅርታህን ፡ መከብብ ፡ ጊዜ ፡ የሚያመጣውን ፡ ዐዋቂው ፡ የጊዜ ፡ ባለቤት ፡ እንጂ ፣ ሌላ ፡ ዐዋቂ ፡ ስለሌለ ፣ በኛ ፡ ሕይወት ፡ አይደርስም ፣ ይደርሳል ፣ ብለን ፡ መናገር ፡ አንችልም ። ይህን ፡ ተውትና ፡ አድርገውና ፡ ሌላውን ፡ እንቀጥል ፡ አለች ።

ይቅርታ ፡ እንደጠየቅሽኝ ፤ ይቅርታ ፡ እየጠየቅሁ ፤ እባክሽ ፡ ጠረ ጠርሽኝ ፡ እንዴ ፤ ጊዜ ፡ የሚያመጣውን ፡ ማንም ፡ አያውቅ ፡ ያልሽ ? ብዬ ፡ እንደገና ፡ ጠየቅኋት ።

ምነው ፡ አንተ ፡ እንደዚህ ፡ ነገሩ ፡ አብሰለሰለህ ፤ ሰው ፡ እንኳን ፡ የሩቁን ፡ የደቂቃውን ፡ የማወቅ ፡ ችሎታ ፡ ያልተሰጠው ፡ ሲሆን ፤ ጊዜ ፡ የሚያመጣውን፡ የጊዜ ፡ ባለቤት ፡ ያውቃል ፡ እንጂ ፤ እኛ ፡ እንደዚህ ፡ ነን ፡ አይባልም ፡ ያልኩህ ፡ በዚህ ፡ አስተሳሰብ ፡ ነው ፡ ብላ ፡ መለሰ ችልኝ ።

ልጆቻችን ፡ እንደመጡ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራ ፡ እንዲሠሩ ፡ ማድረግ ፡ ግዴታችን ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ ጫዋታችንን ፡ ለወጥኩና ፡ የሚሠሩዋቸውን ፡ ዝርዝር ፡ ሥራዎች ፡ አወጣሁ ። በመሠረታዊ ፡ ሐሳቡ ፡ ተስማማን ። የልጆቻችንን ፡ የመምጫ ፡ ቀን ፡ በናፍቆት ፡ ስንጠባበቅ ፤ ልጆቻችን ፡ መጡ ። በደስታ ፡ ተቀበልናቸው ። እንግድነታቸውን ፡ ሳናቃልል ፡ ከውጭ ፡ ለሚመጣ ፡ እንግዳ ፡ የሚደረገውን ፡ አቀባበል ፡ አደረግንላ ቸው ።

ልጆቹ ፡ ለሁለት ፡ ቀን ፡ ዕረፍት ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፤ በረኸኛው ፡ የዕ ረፍት ፡ ጊዜ ፡ የሚሠሩትን ፡ ሥራ ፡ አስረዳኋቸው ። በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ በየምድብ ፡ ሥራቸው ፡ ገቡ። ሠርተው ፡ ካለማወቃቸው ፡ የተነሣ ፡ ለሦ ስት ፡ ቀን ፡ ያህል ፡ ድካም ፡ ተሰማቸው ። አዘውትረው ፡ በመሥራታ ቸው ፡ አካላቸው ፡ እየተፍታታ ፡ ጥንካሬ ፡ በማግኘታቸው ፤ አካልን ፡ ያለሥራ ፡ ማለሳለስ ፡ ለካስ ፡ አይጠቅምም ፡ እያሉ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተወያዩ ።

ወንዱ ፡ ግብርናና ፡ የመሳሰለውን ፤ሴቶቹ ፡ ባልትናና ፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ የተያያዘውን ፡ በትጋት ፡ በመከታተል ፡ የኛ ፡ የወላጆቻቸው ፡ የድካም፡ ተካፋዮች ፡ ሆኑ ። በሥራው ፡ ላይ ፡ በቆዩ ፡ መጠን ፡ የበለጠ ፡ ደስታ ፡ ስለተሰማቸው ፤ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ወንዱ ፡ ልጃችን ፡ እንዲህ ፡ አለ ። በትምህርት ፡ ዓለም ፡ ውስጥ ፡ ያለን ፡ በመሆናችን ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ የማያንስ ፡ ጊዜ ፡ ተራርቀን ፡ ቆይተናል ። ተነፋፍቀን ፡ በተገ ናኘንበት ፡ ወቅት ፡ አባትና ፡ እናት ፡ ለልጆቻቸው ፡ የሚያደርጉት ፡ የማ ቀላመጥ ፡ ወግ ፡ ደርሶን ፡ በመንቀባረር ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜያችንን ፡ እና ሳልፋለን ፡ ስንል ፤ አድካሚ ፡ ሥራ ፡ አዘጋጅታችሁ ፤ በመጣን ፡ በሦ ስተኛ ፡ ቀን ፡ ሥራ ፡ በመጀመራችን ፡ የከተማውንና ፡ ከተማ ፡ የያዘ ውን ፡ ጠባይ ፡ ልናጫውታችሁ ፡ ዕድል ፡ አላገኘንም ።



ረኸሙን ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ በዋዛ ፡ በፈዛዛ ፡ ሳናሳልፍ ፡ በሥራ ፡ እንድናሳልፍ፡ ባደረጋችሁት፡ አስተሳሰብ ፤ አባባንና ፡ እማማን ፡ እናመ ሰግናችኋለን ፡ ብሎ ፡ ተቀመጠ ።

ዋ ፤ እረ ፡ ካዳመጣችሁኝ ፡ የከተሜን ፡ ወላጆች ፡ የልጅ ፡ አስተዳ ደግ፡ልንገራችሁ ፡ አልኩና ፡ በረኸሙ ፡ የዕረፍት ፡ ወራት ፡ በልዩ ፡ ልዩ፡ ሥራ ፡ እየዋሉ ፡ ጊዜያቸውን ፡ የሚያሳልፉበት ፡ ገንዘብ ፡ በመ ቸር ፡ ሙሉ ፡ ነፃነት ፡ በመስጠት ፡ እንዲደሰቱ ፡ ያደርጋሉ ፡ እንጂ ፤ በአንድ ፡ በኩል ፡ ትምህርት ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ለአካል ፡ ክፍሎች ፡ ጥን ካሬ፡ የሚሰጥ ፡ ሥራ ፡ ሊያሠርዋቸው ፡ ቀርቶ ፡ ራሳቸውን፡ በራሳቸው፡ እንኳን ፡ አይረዱም ፡ ስል ፡ አስረዳኋቸው ።

ፀሐይ ፡ ቀጠል ፡ አደረገችና ፡ ልናያችሁ ፡ ከተማ ፡ መጥተን ፡ ሳለ፡ አብራችሁኝ ፡ ባደራችሁበት ፡ ሌሊት ፡ የነገራችሁኝን ፡ ታስታውሳላ ችሁ ፤ ከንግግራችሁ ፡ ብዙ ፡ ተምሬያለሁ ።

መውለድና ፡ መዋለድ ፡ የፍጥረት ፡ ግዴታ ፡ ነው ። ትልም ፡ ይወ ልዳል ። የትውልድ ፡ አመጣጥ ፡ በሁለት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ሆኖ ፡ የእገሌ ፡ አባትና ፡ እናት ፤ ወይም ፡ የእንገሌ ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ ልጆች ፡ እየተባለ ፡ ቢነገርም ፤ አስገኝና ፡ ተገኝ ፡ የመለያ ፡ ስም ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ የልጅ ፡ ወይም ፡ የልጆች ፡ መገኘት ፡ በበለጠ ፡ የሚጠቅመው ፡ ለሀገ ርና ፡ ለኅብረተ ፡ ሰቡ ፡ ነው ።

መሠረታውያን ፡ አስተሳሰባችንን ፡በዚህ ፡ ላይ ፡ የምንመሠረት ፡ ከሆነ ፤ ከማንም ፡ ማን ፡ ይገኝ ፤ ልጅ ፡ ወይም ፡ ልጆች ፡ የምንላቸው ፡ ሁሉ ፡ ለሀገርና ፡ ለኅብረተሰቡ ፡ ጠቃሚ ፡ ሆነው ፡ እንዲገኙ ፡ እንጂ ፡ ኅብረተሰቡን ፡ ጠልተው ፡ የኅብረተሰቡን ፡ ኅልፈተ ፡ ዓለም ፡ እየተ መኙ ፡ እነሱም ፡ በኅብረተሰቡ ፡ አስተያየት ፡ ከመጠላት ፡ ጋር ፡ ከሚ ሰጡት ፡ ጥቅም ፡ ይልቅ ፡ የሚያስከትሉት ፡ ጉዳት ፡ እያደረ ፡ እየተ ሰማ ፡ በሚያልፍ ፡ ትውልድና ፡ በሚተካ ፡ ትውልድ ፡ መካከል ፡ የቂ ምና ፡ የበቀል ፡ ታሪክ ፡ መሠረት ፡ ይሆናሉ ። በዚህ ፡ አሳሳቢ፡ ጉዳይ፡ አካባቢውና ፡ ኅብረተሰቡ ፡ ካልተባበረበት ፡ የጥቂቶች ፡ ቍጥር ፡ ለጠ ቅላላው ፡ ሙሉ ፡ ደኅንነት ፡ ሊያስገኝ ፡ አይችልም ።

በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ የተመላ ፡ ጭውውት፡ ይዘን ፡ ሳለ፡ ከፀሐይ ፡ እናት ፡ ከወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ መልእክት ፡የያዘ ፡ መምጣቱን ፡

አረፈ ፡ ልቤ ፡ የሚባለው ፡ አሽከር ፡ ገብቶ ፡ ሲናገር ፡ በተለይም ፡ ፀሐይና ፡ እኔ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ድንጋጤ ፡ ተሰማን ።

መልእክተኛው ፡ ሰላምታ፣ ሰጥቶ፣ ከወይዘሮ፣ ዘነበች፣ የተጻፈውን፣ ወረቀት ፡ ሰጠ ። እኔና ፡ ፀሐይ ፡ ልጆችም ፡ ሳይቀሩ ፡ ከበን ፡ አነበብነው። የደኅንነታችሁን ፡ ወሬ ፡ ባጣ ፡ ደኅና ፡ አይደላችሁ ፡ ይሆን ፡ ብዬ ፡ ስለ ፡ ሠጋሁ ፡ ነው ፡ መልእክተኛ ፡ መላኬ ፤ ብትችሉ ፡ መጥታችሁ ፡ እዩኝ ፡ የሚል ፡ ሆነ ።

በዚህ ፡ ተረጋጋንና ፡ የወይዘሮ ፡ ዘነበችን ፡ ደኅንነትና፣ አኗኗር፣ ተራ ፡ በተራ ፡ እየተቀባበልን ፡ ጠየቅን ፤ መልእክተኛው ፡ ደኅንነታቸውን ፡ ካበሰረ ፡ በኋላ ፡ በትሩፋታቸው ፡ ምን ፡ ያህል ፡ መወደድንና ፡ መከበርን ፡ እንዳገኙ ፡ አስረዳን ።

ወንድሜ ፤ ሥራውን ፡ ቻለችው ፡ የምትሠራው ፡ ምን ፡ ይሆን ? በተድላ ፡ በደስታ ፡ ተለሳልሳ ፡ የኖረች ፡ ናት ፡ እንደምን፣ ችላ፣ ሠራች፣ ብላ ፡ ፀሐይ ፡ ስትጠይቅ ፡ ከዓይኖችዋ ፡ ዕንባዋ ፡ ፈሰሰ ።

መልእክተኛው ፡ ለጥያቄዋ ፡ ሲመልስ ፤ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ መቸገራቸው ፡ አልቀረም ፤ በዚያ ፡ ለወደቁ ፡ መናንያን ፡ ምግብ ፡ ማብሰል ፤ መፍጨት ፤ ውሃ ፡ መቅዳት ፤ በጣም ፡ የተዳከሙትን ፡ ንጽሕና ፡ መጠበቅ ፤ ልብሳቸውን ፡ ማጠብ ፤ የሚኖሩበትን ፡ በዓት ፡ ማጽዳት፤ ይህንና፣ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ሲሆን ፤ በበለጠ ፡ አድካሚው ፡ ሥራ ፡ ወፍጮና ፡ እንጀራ ፡ ጋገራ ፡ እንደዚሁም ፡ ውሃ ፡ ከወንዝ ፡ ወርዶ ፡ መቅዳት ፡ ነው ።

እነዚህ ፡ ሥራዎች ፡ በጣም ፡ ከባድ ፡ በመሆናቸው ፡ እጃቸው ፡ ተላልጦ ፡ ሻክረዋል፤ ውሃ ፡ የተሸከሙበት፣ ጀርባቸው፣ ሻኛ ፡ እውጥቶ፣ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ አስቸግሯቸው ፡ ነበር ፤ ይሁንና ፡ ቆራጥ ፡ መናኒት ፡ ስለሆኑና ፡ ፈተናውን ፡ ስለተቋቋሙት ፡ ለጊዜው ፡ እየቆሰለ ፡ ያስቸግራቸው ፡ የነበረው ፡ አካላቸው ፡ ገብሮ ፡ ዛሬ ፡ እንኳን ፡ የሀል ፡ ዘር ፡ ድንጋይ፣ መፍጨት፣ ይችላሉ፣ ባለ ፡ ጊዜ ፤ ፀሐይ ፡ እዬ ፡ ብላ ፡ በከፍተኛ ፡ ድምፅ ፡ አለቀሰች ። መልእክተኛው ፡ ደንግጦ ፡ እመየቴ ፡ ምን የሚያስለቅስ ፡ ነገር ፡ አገኘዎ ፤ የሚያስለቅሰው ፡ ይልቅ ፡ የናንተ ፡ ኑሮ ነው ። ርሳቸውም ፡ ከቅዱሳት ፡ አንስት ፡ እንደ ፡ አንዷዋ ፡ የተቆጠሩ ፡ ብቃት ፡ ባላቸው ፡ ቅድስናቸው ፡ የተመሰከረላቸው ፡ ሆነዋል ። የለም፣ ኧረ ፡ ምነው ፡ እመየቴ ፤ ይህ ፡ የናንተ ፡ ከኑሮ ፡ ተቆጥሮ፣ ደስ፣ ይላችሁ፣



ይሆን ? እይምሰልዎ ፤ ላለለት ፡ ደስታ ፡ እዚያ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እዚህ ፡ ደስታ ፡ የለም ። ሞልቶ ፡ ላይሞላ ፡ ቆላ ፡ ደጋ ፡ ሲረግጡ ፡ የሚቀረው ፡ ዓለማዊ ፡ ኑሮ፣ ከኑሮ ፡ ተቆጥሮ፣ ይደከምበታል። ደስታው ፡ ምን ፡ ነው? የሥጋ ፡ ደስታ ፡ ነው ፡ ወይም ፡ የመንፈስ ፡ ደስታ ፡ ነው ? ሰውን ፡ የሚያጠግበው ፡ የመንፈስ ፡ ደስታ ፡ ስለሆነ ፤ ደስታው ፡ በየጊዜው ፡ አይለወጥም፣ አብሮ ፡ ንዋሪ ፡ በሆነ ፡ በዘወትር ፡ ደስታ ፡ መንፈሳቸው ፡ እንደረካ ፡ ይኖራል ።

ከናንተ ፡ አኗኗር ፡ የሚገኘው ፡ ደስታ ፡ በሥጋ ፡ ላይ፣ የሚያንገብብ ፡ ስለሆነ ፤ እንኳን ፡ ኗሪ ፡ ሊሆን ፡ ለግማሽ ፡ ቀን ፡ ከናንተ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ሳይቆይ ፡ ታይቶ ፡ የሚጠፋ ፡ ነው ።

እናትዎ ፤ ታይቶ ፡ በማይጠፋ ፡ በመንፈስ ፡ ደስታ ፡ ጠግበው ፡ በሰውነታቸው ፡ ላይ ፡ የሚታየው ፡ ግርማ ፡ ሞገስ ፡ ሌላ ፡ ነው። ምንም፣ እንኳ ፡ እጃቸው ፡ ቢጐለድፍ ፡ ውበታቸውና ፡ ልምላሜያቸው ፡ በእልፍኝ ፡ ውስጥ ፡ የተሞሸረችን ፡ ሙሽራ ፡ ይመስላሉ ። ለቅሰው ፡ ለሳቸው፣ ሳይሆን ፡ ይልቁንም ፡ የርሳቸውን ፡ እድል ፡ ስጠን ፡ ብሎ ፡ ማልቀስ ፡ ይጠቅማል ፡ እንዳለ ፤ ሌላውን ፡ ሐሳብ ፡ ከመቀጠሉ ፡ በፊት፣ እኔ ፡ የንግግሩን ፡ ተራ ፡ በመውሰድ ፤ ወንድሜ ፡ ንብረትን ፡ አስትቶ ፡ የሚያስድድ ፡ ተናገርከ ። ሆኖም ፡ ፀሐይ ፡ እናትዋን ፡ ከመውደድዋም ፡ በላይ ፡ በድሎትና ፡ በምቾት፣ ኗሪ ፡ የነበሩ ፤ የሞቀ፣ ቤታቸው ፡ የተፈታው ፡ በባላቸው ፡ ሞት ፡ ነው ። ትናንት ፡ በባላቸው ፡ ሞት ፡ የሞቀ ፡ ንብረታቸው ፡ ፈርሶ ፡ ቍጥራቸው፣ በዛ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ በማስተዳደር ፡ ያዙና፣ ይናዘዙ፣ የነበሩ ፡ የሴት ፡ ወይዘሮ፣ ዛሬ፣ ወፍጮ፣ ፈጭና፣ ውሃ ፡ ቀጂ ፡ በመሆናቸው ፡ አዝና ፡ ነው ፡ ያለቀሰችውና ፡ ሐሳብዋን ፡ በትክክል ፡ ብታውቀው ፡ እወዳለሁ ፡ አልኩት ።

መልእክተኛው ፡ ሐሳቡን ፡ ቀጠል ፡ አድርጎ፤ የሰው ፡ ሁሉ ፡ አስተያየት ፡ እንደመልኩ ፡ የተለያየ ፡ ነው ። አንዱ ፡ ወዶት ፡ የሚከተለውን ፡ ሌላው ፡ ይንቀዋል ፤ ወይም ፡ ይጠላዋል። ከያዘውና ፡ ከወደደው፣ በቀር ፡ ሌላ ፡ የያዘውና ፡ የወደደው ፡ ምንም ፡ ምን ፡ መስሎ ፡ አይታየውም ።

እናንተ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ድካም ፡ የምትወጡበትና ፡ የምትወርዱበት ዓለማዊ ፡ ኑሮ ፤ እናንተ ፡ ከፍተኛ ፡ ዋጋ ፡ ሰጥታችሁ ፡ ስትደሰቱበት ፤ የኔና ፡ የኔ ፡ ብጤዎች፣ ግን ፡ ድካማችሁን ፡ ከንቱ ፡ ድካም ፡ አድርገን፣

በማየት ፡ እንስቅባችኋለን ። እናንተ ፡ ደግሞ ፡ በኛ ፡ መጐሳቆል ፡ ንቀት ፡ ያድርባችኋል ፣ ነገር ፡ ግን ፡ ፀሐይዋ ፡ ለናንተም ፡ ለኛም ፡ እኩል ፡ ሙቀትዋን ፡ ትሰጣለች ። በቀኑ ፡ ብርሃን ፡ እኩል ፡ እንዘዋወራለን ። በሌሊቱ ፡ እኩል ፡ እናንቀላፋለን ። ከረምትና ፡ በጋ ፡ እየተለዋወጡ ፡ በክረምት ፡ ልምላሜና ፡ አዝርዕት ፣ በበጋ ፡ እሸትና ምርት ፡ እኩል ፡ እናያለን ፡ የዕለት ፡ ምግብ ፡ እኩል ፡ እናገኛለን ። የዕለት ፡ ልብስ ፡ እኩል ፡ እንለብሳለን ። የሞት ፡ ጥሪ ፡ ሲደርሰን ፡ እኩል ፡ እንካፈላለን። እንግዲህ ፡ የሰው ፡ አቅዋም ፡ በነዚህ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው።

መልእክተኛው ፡ ረጋ ፡ ብሎ ፡ ሲናገር ፣ ፀሐይና ፡ እኔ ፡ ፍጹም ፡ በሆነ ፡ ፀጥታ ፡ በማዳመጥ ፡ ላይ ፡ ሳለን ፣ ፀሐይ ፡ ራስዋን ፡ እያወዛወዘች ፡ እውነትህን ፡ ነው ፡ እኮ ፣ ብላ ፡ በንግግሩ ፡ ተመሰጠች ።

መልእክተኛው ፡ ንግግሩን ፡ በመቀጠል ፡ ሰው ፡ በጣም ፡ ተታላይ ፡ ስለሆነ ፣ ሐሳቡ ፡ ረዥም ፡ ሕይወቱ ፡ አጭር ፡ ነው። ለፍላጎቱ ፡ ወሰን ፡ ስለሌለው ፡ ችግርን ፡ ራሱ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ እየፈጠረ ፡ ሲቸገር ፡ ይኖራል። ራሱ ፡ የፈጠረውን ፡ ችግር ፡ ለማሸነፍ ፡ ይታገላል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ሳያሸንፍ ፡ ራሱ ፡ ተሸንፎ ፡ ሲወድቅ ፡ በርሱ ፡ ውድቀት ፡ ብቻ ፡ ችግሩም ፡ አብሮ ፡ ይዘጋል ።

ይህን ፡ እያየ ፡ ሌላው ፡ ደግሞ ፡ ይቀጥላል ፣ በሌላው ፡ ያየው ፡ ድካም ፡ ምን ፡ ውጤት ፡ እንደሰጠ ፡ አያገናዝብም ። ሌሎች ፣ በየበኩላቸው ፡ ይወጣሉ ፡ ይወርዳሉ። ፍጻሜውያቸው ፡ ግን፣ ያ ፡ በቅድሚያ ፡ ከደከመና ፡ ድካሙ ፡ ሁሉ ፡ ከንቱ ፡ ሆኖ ፡ ከቀረ ፡ የተሻለ ፡ ውጤት ፡ ሳያገኝ ፡ በዚያው ፡ መንገድ ፡ እነሱም ፡ እንዚያም ፡ ያልፋሉ ።

ከዚህ ፡ የባሰ ፡ ሌላ ፡ ደግሞ ፡ አለ ። የፍላጐት ፡ መስፋፋትና ፡ የራስ ፡ መውደድ ፡ ኃይል ፡ ሰዎችን ፡ በጣም ፡ እየተጫነ ፡ አንዱን ፡ አንዱ፣ ሌላውን ፡ ሌላው ፡ አሳልፈው ፡ ይሰጡታል ። የፍላጐት ፡ ወሰን ፡ ማጣት ፡ በቃኝ ፡ በሚለው ፡ አነጋገር ፡ ሳይለወጥ ፡ መቅረቱ ፡ በጣም ፡ የሚያሳዝን ፡ ነው ።

ሰውን ፡ ሰው ፡ ገደለው ፣ አገዳደሉ ፡ ሁሉ ፡ ከጭካኔ ፡ የተያያዘ ፣ ሰው ፡ ሆኖ ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ሊፈጽመው ፡ የማይገባውን ፡ ሰው ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ይፈጽማል ። ራሱ ፡ የሚኖርበትን ፡ ጊዜ ፡ ሳያውቅ ፡ ለግል ፡ ፍላ



ጐት ፡ ሲል ፡ በሌላው ፡ ላይ ፡ እጁን ፡ በጭካኔ ፡ ይዘረጋል ። ይሠነዝራል ። የያዘውን ፡ ይቀማል ፣ የለበሰውን ፡ ይገፋል ።

እንስሳትና ፡ የዱር ፡ አራዊት ፡ ከሌላው ፡ ጋር ፡ በጥላቻ ፡ ይፈላለጉ ፡ እንጂ ፡ በአንድ ፡ ዓይነት ፡ አምሳል ፡ የተፈጠሩት ፡ ሌላው ፡ እንዳያጠቃቸው ፡ ተባብረው ፡ ራሳቸውን ፡ ይጠብቃሉ ። ሰው ፡ በሥነ ፡ ፍጥረት ፡ አቅዋም ፡ አንድ ፡ ሆኖ ፡ በቋንቋ ፣ በባህል ፣ በመልክ ፡ ይለያይ ፡ እንጂ ፣ የወል ፡ ስሙ ፣ ባሕርዩም ፡ ሰው ፡ የሚሠራውን ፡ ስለሚሠራ ፡ በቋንቋና ፡ በባህል ፡ ቢለያይም ፣ መሠረታዊ ፡ አቅዋሙ ፡ ሰው ፡ መሆኑን ፡ እያስታወሰ ፣ ፍቅርን ፡ ሊገዛ ፡ ሲገባው ፣ ፍቅርን ፡ አርቆ ፡ ጥላቻን ፡ አትርፎ ፡ ከቀን ፡ ወደቀን ፡ ራሱን ፡ እየገደለ፣ ደሙን ፡ እያፈሰሰ ፡ ደሙ ፡ እንደ ፡ አቤል ፡ ደም ፡ ከምድር ፡ ወደ ፡ ሰማየ ፡ ሰማያት ፡ ይጮኻል ። እንግዲህ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ የናንተ ፡ ዓለም ፣ ዓለም ፡ ነው ፡ ብላችሁ ፡ መከራ ፡ የምታዩበት ፡ ብሎ ፡ ካሰረዳ ፡ በኋላ ፣ ትሄዱ ፡ እንደሆነ ፣ በኔ ፡ መሪነት ፡ ብትሄዱ ፡ መልካም ፡ ይመስለኛል ። ስሞኑን ፡ የምትመጡ ፡ ከሆነ ፣ ከበዓቱ ፡ ተለይቼ ፡ በውጭ ፡ ውሎ ፡ ማደር ፡ ደስ ፡ ስለማይለኝ ፡ ነገ ፡ ጥዋት ፡ እመለሳለሁ ፡ አለን ።

ቀደም ፡ ብለን ፡ ያሰብንበት ፡ ስለሆነ፣ ነገም ፡ ቢሆን ፡ ለመሔድ ፡ እንችላለን ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ከናታችን ፡ ተልከህ ፡ የመጣህ ፡ ስለሆነ፣ አረፍ ፡ ብለህ ፡ በመካከላችን ፡ ውለህ ፡ ብታድር ፡ እናታችን ፡ በመካከላችን ፡ እንዳሉ ፡ ያህል ፡ በመቍጠር ፡ ደስ ፡ ይለናል፣ ከተቀደሰ ፡ ገዳም ፡ የመጣን ፡ ሰው ፡ ተቀብለን ፡ ብናስተናግድ ፡ ረድኤት ፡ የሚደርሰን ፡ መሆኑን ፡ ስለምናምን ፡ መስተንግዶአችንን ፡ ተቀበል ፡ ብለን ፡ ለመንነው ።

ስለአስተሳሰባችሁ ፡ አመሰግናለሁ ። ይሁን ፡ እንጂ ፣ ሰው ፡ ለሁለት ፡ ጌታ ፡ መገዛት ፡ እንደማይችል ፡ ተነግሮዋል ። ሰው ፡ የሁለት ፡ ዓለም ፡ ስደተኛ ፡ ሆኖ ፡ መኖር ፡ አይገባውም ። አንዱን ፡ ይዞ ፡ በአንዱ ፡ ተወስኖ ፡ መኖር ፡ አለበት ፡ እንጂ ፣ ጥቁር ፡ ወይም ፡ ነጭ ፡ ቆብ ፡ አስረዝሞ ፣ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ገዳም ፣ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ እያሉ ፡ በከተማ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ እያለው ፡ ከተማውን ፡ ሲከተል ፡ ይህ ፡ ሲሰለቸው ፡ ወደ ፡ ገዳም ፡ መለስ ፡ ብሎ ፡ በገዳሙ ፡ ያለውን ፡ ሲከተል ፣ በአንዱም ፡ ላይ ፡ መሠረታዊ ፡ አቅዋም ፡ ሳይኖረው ፡ ከንቱ ፡ ሆኖ ፡ ይቀራል ።

ዓለምን ፡ ዓለም ፡ አድርገው ፡ የያዙ ፡ ዓለማዊ ፡ ቤታቸውን ፡ በተቀደሰ ፡ ጋብቻ ፡ አሟልተው ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጠብቀው ፡ ከሚያገኙት ፡ አሥራት ፡ በኩራት ፡ ሰጥተው ፡ ስለሚኖሩ፡ ዓለምን ፡ በሥጋና፡ በነፍሳቸው ፡ ገዝተው ፡ ይኖራሉ ።

ዓለምን ፡ ንቀናል ፤ ከዓለም ፡ ውጭ ፡ ነን ፡ በገዳማትና ፡ በመሳሰሉት ፡ ተወስነን ፡ እንኖራለን ፤ ከዕለት ፡ ምግብና ፡ ልብስ ፡ በቀር ፡ ሌላው ፡ ለኛ ፡ ምናችን ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ? መንፈሳዊ፡ አርበኞች፡ የሆኑ ፡ ሚባቸውን ፡ እየሳቱ ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ፍላጎት ፡ ሲያጓጓቸው ፡ ዓለምን፡ ወደው ፡ ይከተላሉ ። ሲሰለቻቸው ፡ ዓለምን ፡ ጠልተው ፡ በገዳማቱ ፡ ኑሮ ፡ ተወስነው ፡ ለመኖር ፡ ይፈልጋሉ ። ይህ ፡ የሐሳብ ፡ መለዋወጥ ፡ በሰዎች ፡ ላይ ፡ ሊጫወት ፡ የቻለው ፡ በያዙት ፡ ካለመጽናት ፡ በአመኑበት ፡ ካለመቁረጥ ፡ በተወሰነ ፡ ሥፍራ ፡ ተሰብስቦ ፡ ካለመቀመጥ ፡ የተገኘ ፡ ጠባይ ፡ ነው ። ሰው ፡ ቅድስናውን ፡ ሊጠብቀው፡ የሚችለው፡ በቆራጥ ፡ መንፈስ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ፍላጎትንና ፡ ምኞትን ፡ ለማቸነፍ ፡ ራስን ፡ በራስ ፡ ለማዘዝ ፡ ሲችል ፡ ነው ። ከዚህም ፡ ጋር ፡ ራስን ፡ ከፈተና ፡ ለማዳን ፡ በተወሰነ ፡ ሥፍራ ፡ ሰብሰብ ፡ ማለት ፡ ከሁሉ ፡ ነገር ፡ ያድናል ። ስለዚህ ፡ ነው ፡ ከበዓቱ ፡ ወጥቼ ፡ መስንበት፡ የማልፈልገው፡ እንጂ ፡ እናንተን ፡ ለማስደሰት ፡ ብሰንብት ፡ እወድ ፡ ነበር ። ዛሬ ፡ ግን፡ እዚሁ ፡ ስንጫወት ፡ እናድራለን ። የእግዚአብሔር ፡ ጠለ ፡ በረከት ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ ይፍሰስ ፡ ብሎ ፡ መረቀን ።

ነገ ፡ የምትሄድ ፡ ከሆነ ፡ እኛም ፡ እንሄዳለን ። በሉ ፡ እናንተ ፡ ተጫውቱ ፡ ለነገ ፡ የሚያስፈልገንን ፡ ላዘጋጅ ፡ ብላ ፡ ፀሐይ ፡ ወደ ፡ ጓዳዋ ፡ ገባች ። መልእክተኛው ፡ «ጨዋታችንን ፡ ያጣጣምን ፡ ይመስለኛል ። የቀረም ፡ ቢኖር ፡ ነገ ፡ በመንገድ ፡ ላይ፡ እንነጋገራለን ፡ » ስላለ፡ ጥቂት ፡ እንዲያርፍ ፡ ነግሬው ፡ ወጣ ፡ አልኩ ።

በማግሥቱ፡ አሽከሮች ፡ ይዘን ፡ ጉዞዋችንን፡ ከመልክተኛው፡ ጋር፡ ቀጠልን ፤ ሳይታወቀንና ፡ ድካም ፡ ሳይሰማን ፡ እንድንደርስ ፡ ጭውውታችን ፡ መነሻ ፡ እንዲኖረው ፡ ስለሚያስፈልግ ፡ ከምን ፡ እንነሣ፡ ብሎ፡ መልእክተኛው ፡ መልስ ፡ ሰጠ ።

እትታዘበኝና ፡ አሁን ፡ በምትኖርበት ፡ አኗኗር ፡ ተወስነህ ፡ ለመኖር ፡ ዕድሜህ ፡ የሚፈቅድ ፡ አይመስልም። በዚህ፡ ዕድሜህ፡ ይህን፡



አኗኗር ፡ የመረጥህበትን ፡ ምክንያት ፡ ብትገልጥልን ፡ እንወዳለን ፡ አልኩት ። መልእክተኛው ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፡ አለና ፡ ይህን ፡ የመረጥኩበትን ፡ ምክንያት ፡ የምገልጥላችሁ ፡ ከሆነ ፡ ሙሉ ፡ የሕይወት ፡ ታሪኬን ፡ በቅድሚያ ፡ መናገር ፡ ይኖርብኛል ፡ ብሎ ፡ ቀጠለ ።

«እስካሁን ፡ ባለኝ ፡ ዕድሜ ፡ ብዙ ፡ ዐየሁ ። ብዙ ፡ መረመርኩ ። ከሀገር ፡ ወደ ፡ ሀገር ፡ ከሥፍራ ፡ ወደ ፡ ሥፍራ፡ እየተዘዋወርኩ ፡ ብዙ፡ አጠናሁ ። ጥናቴንም ፡ የመሠረትኩት ፡ በሰው ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ ላይ ፡ ስለነበረ ፡ ዓለምና ፡ ሰው ፡ ሰውና ፡ ዓለም ፡ ሰውና ፡ ሰው ፡ እንደ ምን ፡ ባለ ፡ አኳኋን ፡ እንደሚኖሩ ፡ ዐየሁ። ለመኖርም ፡ ሞከርኩ ።

ከሀገር ፡ ወደ ፡ ሀገር ፡ ከሥፍራ ፡ ወደ ፡ ሥፍራ ፡ የተዘዋወርኩት፡ በራሴ ፡ አስተሳሰብ ፡ አልነበረም ። አባትና ፡ እናቴ ፡ ከኔ ፡ በቀር፡ ሌላ፡ ልጅ፡ የላቸውም፡ ነበር። አንድ፡ በመሆኔ፡ እንደ፡ ዓይን፡ብሌን፡ ጠብቀው፡ ተከባክበው ፡ አሳደጉኝ ። ትምህርት ፡ ለመከታተል ፡ ዕድሜዬ ፡ ሲፈቅድ ፡ ከጐረቤት ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ እየላኩኝ ፡ ትምህርት ፡ መማር ፡ ጀመርኩ ። አባትና ፡ እናቴ ፡ ድኆች ፡ ከዕለት፡ ምግብና፡ ልብስ ፡ በቀር ፡ ሌላ፡ ምንም ፡ የሌላቸው ፡ ሲሆኑ ፡ መደበኛ ፡ ሥራቸው ፡ ግብርና ፡ በገበያ ፡ ቀን ፡ ጥቃቅን ፡ የችርቻሮ ፡ ንግድ ፡ ጭምር ፡ እየነገዱ፡ በአነስተኛ ፡ ገቢ ፡ ይተዳደሩ ፡ ነበር ።

ይዞታዬን ፡ ያየ ፡ የባለጸጋ ፡ ልጅ ፡ እንጂ ፡ የደኃ ፡ ቤተሰብ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የሚገምት ፡ አልነበረም ። አባትና ፡ እናቴ ፡ ለኔ ፡ ከማሰባቸው ፡ የተነሣ ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አዘውትሬ ፡ ከመሄድ ፡ በየምክንያቱ ፡ ብቀር ፡ ይወዱ ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ የትምህርትን ፡ ጠቃሚነት ፡ ዐውቄ ፡ ሳይሆን ፡ በዕድሜ ፡ እኩ ፡ ከሆኑኝ ፡ ባልንጀሮቼ ፡ ጋር ፡ ተገናኝቼ ፡ ለመጫወት ፡ ዕድል ፡ የማገኘው ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ በመሆኑ ፡ ከምቀር ፡ መሄድን ፡ በበለጠ ፡ በመምረጤ ፡ አዘውትሬ ፡ እሄዳለሁ ። ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሄጄ ፡ እስከመለስ ፡ የማያምኑኝ ፡ አባትና ፡ እናቴ ፡ ባላወቁት ፡ ቀንና ፡ ሰዓት ፡ ለመጨረሻ ፡ ጥለውኝ ፡ የሚሄዱባት ፡ ማንም ፡ ያልጠበቃትና ፡ ያላሰባት ፡ ጉደሎ ፡ ቀን ፡ መጣች ።

ውይ ፡ ወንድሜ ፡ ምን ፡ ሊመጣ ፡ ይሆን ፡ ብላ ፡ ፀሐይ ፡ በመደንገጥ ፡ ጠየቀች ። ኧረ፡ ገና ፡ ጉዱን፡ ትሰማላችሁ፡ በትዕግሥት፡ አዳምጡ፡ ብሎ ፡ ገለጣውን ፡ ሊቀጥል ፡ ሲል ፡ ፀሐይ ፡ ወንድሜ ፡ በእሁኑ ፡ እነጋ

ገርህና ፣ ቀጥለህም ፣ የምትናገረውን ፣ በመፍራቴ ፣ ልቤ ፣ መታ፣ ብላ፣ እግርዋ ፣ የበቅሎውን ፣ ርካብ ፣ እጅዋ ፣ ልጓሙን ፣ መያዝ ፣ አቅቶት ፣ ዛለ ። በመካከሉ ፣ ንግግሩ ፣ ተቋርጦ ፣ ዕረፍት ፣ ከደረግን ፣ በኋላ ፣ ጉዞ ስንቀጥል ፣ በል ፣ ወንድሜ ፣ ቀጥል ፣ እንስማ ፣ አልኩት ።

ፀሐይ ፣ ድንገተ ፣ ከሆነች ፣ ምኑን ፣ ቀጠልኩት ፣ አለና ፣ ዓይኑን፣ ጣል ፣ ሲያደርግ ፣ ዓይን ፣ ለዓይን ፣ ተያዩና ፣ የኔን ፣ ፍርሃት ፣ ርሳውና ፣ እባክህን ፣ ቀጥል ፣ አለችው ።

ከተፈቀደልኝ ፣ እሺ ፣ ልቀጥል ፣ አለና ፣ አባትና ፣ እናቴ፣ ድኆች፣ ከዕለት ፣ ምግብና ፣ ልብስ ፣ በቀር ፣ የሌላቸው ፣ መሆናቸውን ፣ ነግሬያ ችኋለሁ ። የሚኖሩት ፣ በአንዲት ፣ የሰንበሌጥ ፣ ከዳን ፣ ቤት ፣ ሲሆን ፤ ይህችውንም ፣ ቤት ፣ የሠርዋት ፣ በጢሰኝነት ፣ ከተራራ ፣ ሥር ፣ ነው። ቀን ፣ የዕለት ፣ ተግባራቸውን ፣ ሲያከናውኑ ፣ ውለው ፣ እኔም ፣ ከትምህ ርት ፣ ቤት ፣ ውዬ ፣ በዚያቸው ፣ በሞቀችና ፣ የደስ ፣ ደስ ፣ ባላት ፣ ቤታ ችን ፣ የዕለት ፣ ምግባችንን ፣ ተመግበን ፣ ከተኛን ፣ በኋላ ፣ ጊዜው ፣ የክረምት ፣ መውጫ ፣ ስለነበር ፣ ሌሊቱን ፣ ነፋስ ፣ የቀላቀለ ፣ ከባድ ፣ ዝናም ፣ ሲዘንም ፣ ከተራራው ፣ የተናደው ፣ ቋጥኝ ፣ ድንጋይ ፣ ከቤታ ችን ፣ ላይ ፣ ወጥቶ ፣ አባትና ፣ እናቴ ፣ በተኙበት ፣ ሲቀሩ ፣ እኔን ፣ ወደውጭ ፣ ስለጣለኝ ፣ ለጉድ ፣ የፈጠረኝ ፣ ነኝና ፣ ከሞት ፣ ዳንኩ ።

ዕዩት ፣ የሰው ፣ አስተሳሰብና ፣ በሰው ፣ ላይ ፣ የሚደርሰውን ፣ እንደ ፣ ዓይን ፣ ብሌን ፣ ተጠንቅቀው ፣ ይጠብቁኝ ፣ የነበሩት ፣ አባትና፣ እናቴ ፣ ጭራሹን ፣ ትተውኝ ፣ ሄዱ ።

ከሩቅ ፣ ዘመድ ፣ የቅርብ ፣ ጐረቤት ፣ እንደሚበልጥ ፣ ከነጋ፣ በኋላ፣ የደረሰብንን ፣ አደጋ ፣ ጐረቤቶች ፣ ሲያዩ ፣ ተጨጨኸው ፣ ቢመጡ ፣ እኔን ፣ ከነሕይወቴ ፣ ሲያገኙኝ ፤ አባትና ፣ እናቴ ፣ እንኳን ፣ ሕይወታ ቸውን ፣ አስከሬናቸውን ፣ ማግኘት ፣ ስላልተቻለ ፣ ያካባቢው፣ ሕዝብ፣ በብዛት ፣ ተሰብስቦ ፣ ቋጥኙን ፣ ፈልጠው ፣ ክብደቱ ፣ ከተቀነሰ፣ በኋላ፣ ቢገለበጥ ፣ አባትና ፣ እናቴ ፣ ተጨፍልቀው ፣ ተገኙ ።

ከመቃብር ፣ መልስ ፣ ከቅርብ ፣ ጐረቤት ፣ አንዱ ፣ ወደቤቱ ፣ ወሰ ደኝ ። እያጽናና ፣ ያለችግር ፣ እንደሚያሳድገኝ ፣ ሙሉ ፣ ተስፋ ፣ ሰጠኝ። ይሁንና ፣ ብዙ፣ ልጆች ፣ ስላሉት ፣ ልጆቹ ፣ በየምክንያቱ ፣ እየተጣሉኝ፣



የአባትና ፣ የእናቴ ፣ ይዞታና ፣ አስተያየት ፣ በቅጽበት ፣ ተለውጦ ፣ ከሰው ፣ እጅ ፣ በመውደቁ ፣ ማዘን ፣ ብቻ ፣ ሳይሆን ፣ ልቅሶዬ፣ የመረረ፣ ሆነ ። የልጆች ፣ ጠብ ፣ ተለዋዋጭ ፣ ስለሆነ ፤ ከልጆቹ ፣ ጋር ፣ አሁን ፣ ብንጋጭ ፣ ረስተነው ፣ ወዲያው ፣ ሰላማዊ ፣ ጭውውት ፣ እያደረግን ፣ ብረሳውም ፣ የልጆቹ ፣ እናት ፣ ይህ ፣ ዕድለቢስ ፣ ገፊ ፣ እያሉ ፣ ጥላቻቸ ውን ፣ በአስተያየታቸው ፣ ላይ ፣ ሁሉ ፣ እየገለጡ ፣ አባትና ፣ እናቴን ፣ አላስረሳም ፣ አሉኝ ፣ እንዳለ ፤ በነገሩ ፣ ፍላፃ ፣ ልቤ ፣ ስለተወጋ ፤ ዋ ፣ ሰው ! አልኩና ፣ ይህ ፣ አሠቃቂ ፣ ኀዘን፣ ከደረሰብህ ፣ ምን ፣ ያህል ፣ ጊዜ፣ ነው ፣ ብዬ ፣ ጠየቅሁት ። ከሦስት ፣ ወር ፣ አይበልጥም ። ይልቁንም ፣ ለአባትና ፣ ለእናቴ ፣ አንድ ፣ በመሆኔ ፣ ይዞታዬ ፣ እንደ ፣ ባለጸጋ ፣ ልጅ እንጂ ፣ የደኃ ፣ ልጅ ፣ አልመስልም ፣ ነበር ። ይህንኑም ፣ እኝሁ ፣ ሴት ፣ ያውቃሉ ፣ ብሎ ፣ መልከተኛው ፣ በኀዘን ፣ በተሰበረ ፣ ድምፅ ፣ መልስ ፣ ሰጠ ።

ይህስ ፣ ሆነ ፤ መጨረሻው ፣ ከቶ ፣ ምን ፣ ይሆን ? አለችና፣ ፀሐይ፣ የታሪኩን ፣ መጨረሻ ፣ ለማወቅ ፣ መናፈቅዋን ፣ ገለጠች ።

በርጋታ ፣ ስለአዳመጣችሁኝ ፣ አመሰግናለሁ ፤ አለና ፣ ታሪኩን ፣ ቀጠለ ። ያስጠጉኝ፣ ሰው ፣ ሚስት፣ ፊታቸው ፣ እንደ ፣ እሳት ፣ ስለአቃ ጠለኝ ፣ ዓይናቸውን ፣ ላለማየት ፣ ሐሳቤ ፣ ወደ ፣ መራኝና ፣ እግሬ ፣ ወደ አደረሰኝ ፣ መሄድ ፣ መርጩ ፣ ጠፋሁ ።

በዚህ ፣ ጊዜ ፣ ያስጠጉኝ ፣ የአባትና ፣ የእናቴ ፣ የቅርብ ፣ ወዳጅ ፣ አዝነው ፣ ፍለጋቸውን ፣ አጠንክረው ፣ ተከታተሉኝ ። በጠፋሁ ፣ በሦ ስት ፣ ቀን ፣ በጉዞ ፣ ላይ ፣ አገኙኝ ። በጣም ፣ ደነገጥኩ ። መናገር ፣ አቃ ተኝ ። በምን ፣ ምክንያት ፣ እንደጠፋሁ ፣ ምርመራው ፣ ቀጠለ ፤ በሚስ ታቸው ፣ ምክንያት ፣ መሆኑን ፣ መናገር፣ አልወደድኩም፤ ምርመራው፣ ግን ፣ ጠንክረብኝ፣ ብነግርም፣ ያዝናሉ ። ርስም፣ ከሚያዝኑ ፣ እኔ፣ ዕድለ— ቢሱ ፣ ከዓይናቸው ፣ ብሌን ፣ አብልጠው ፣ ይጠብቁኝ ፣ የነበሩትን፣ አባ ትና ፣ እናቴን ፣ ያጣሁት ፣ ብንከራተት ፣ ይሻላል ፣ አልኳቸው ።

በከፍተኛ ፣ ድምፅ ፣ የለም ፤ የለም ! የምሰማው ፣ ቢያሳዝነኝም ፤ ባያሳዝነኝም ፤ ማወቅ ፣ አለብኝ ፣ ንገረኝ ፣ አሉ ።

የደረሰብኝን ፣ መሸሸግ ፣ አልቻልኩም ። እንዲያውቁት፣ ከፈለጉ፣ ዝርዝር ፣ ሁኔታው ፣ ይቅርና ፣ የባለቤትዎ ፣ ፊት ፣ እሳት ፣ ሆኖ ፣ ስላቃ

ጠለኝ ፡ መኖር ፡ አልቻልኩም ። የርሳቸው ፡ ፊት ፡ በገረፈኝና ፡ በእቃ ጠለኝ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ የአባትና ፡ የእናቴ ፡ ትዝታቸው ፡ ከፊቴ ፡ እየተደቀነ ፡ በዚህ ፡ ዕድሜዬ ፡ ይህን ፡ ዕድል ፡ የሰጠኝኝ ፡ እውነት ፡ በኔ ፡ በደል ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ከቅውልድ ፡ የመጣውን ፡ ግፍ ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ ልትገልጥ ፡ ነው ! እያልኩ ፡ ዕድሌ ፡ ይህ ፡ ከሆነ ፡ በአንድ ፡ ሥፍራ ፡ ተቀምጬ ፡ እድለቢስ ፡ ከምባል ፣ ከሀገር ፡ ወደ ፡ ሀገር ፡ ከሥፍራ ፡ ወደ ፡ ሥፍራ ፡ ብዘዋወር ፡ የሚሻል ፡ መስሎ ፡ ስለታየኝ ፣ ቤትዎን ፡ ጥዬ እንደወጣሁ ፣ ሐሳቤ ፡ ወደ ፡ መራኝና ፡ እግሬ ፡ ወደ፡ አደረሰኝ፡ መጣሁ፡ አልኳቸው ።

በጣም ፡ አዘኑ ፣ ተከዙ ፣ ሞትን ፡ ያህል ፡ ትልቅ ፡ የመጨረሻ ፡ መለያየት ፡ በሰው ፡ መካከል ፡ ሲኖር ፣ እስከዚያ፡ ድረስ፡ ተስማምቶና ፡ ተሳስቦ፡ መኖር ፡ እንዴት ፡ ለሰው ፡ ያቅተው ፡ አሉና ፡ ንግግራቸውን ፡ በመቀጠል ፣ ከሰው ፡ ፊት ፡ የወደቅኸው ፡ በአባትና ፡ በእናትህ ፡ ሞት፡ እንጂ ፣ ከዚያ ፡ በፊትማ ፡ እንደምን ፡ ባለ ፡ አኳኋን ፡ ትኖር ፡ እንደ ፡ ነበር ፣ የዓይን ፡ ምስክሮች ፡ አይደሉንም ? ባለቤቱ ፡ ይህን ፡ ስታውቅ ፡ እንዴት ፡ በአንተ ፡ ላይ ፡ ይህን ፡ ሠራች ? ያልጠበቅሁትንና ፡ የማላምነውን ፡ ሰማሁ ። አይሆንም ፡ አልልም ፡ ሰው ፡ ናት ፣ ትሠራ ፡ ይሆናል ፣ እንተን ፡ አላስተባብልም ። በዚህ ፡ ዕድሜህ ፡ ለማን ፡ ብለህ ፡ በራስህ ፡ ላይ ፡ ትዋሻለህ !

ይሁንና ፡ ልጅ ፡ ነህ ፣ በዚህ ፡ ዕድሜህ ፡ ቂም ፡ አትያዝ ፣ ነገሯ፡ የመረረህ ፣ አባትና ፡ እናትህን ፡ እያስታወስክ ፡ ይሆናል ። ወደ ፡ ቤት ፡ እንሂድና ፡ ባለቤቴ ፡ ይቅርታ ፡ እንድትጠይቅህ ፡ አደርጋለሁ ። በር ስዋ ፡ ምክንያት ፡ ተማረህ ፡ እንደምትሄድ ፡ ብታውቅ ፡ እንደማትናገርህ ፡ ርግጠኛ ፡ ነኝ ፡ አሉኝ ።

አዬ ፡ ይህማ ፡ እንደምን ፡ ይሆናል ፣ ባለቤትዎ ፡ ይቅርታ ፡ ጠያቂ፡ እኔ ፡ ይቅርታ ፡ ተጠያቂ ፡ ሆነን ፡ አብረን ፡ የምንኖር ፡ ይመስልዎታል ? ከሆነማ ፡ እኔ ፡ ይቅርታ ፡ ጠይቄ ፡ ርሳቸው፡ ይቅር ፡ ብለው፣ በርኅራኄ፡ ዓይናቸው ፡ ቢያዩኝ ፡ ደስ ፡ ባለኝ ። «ብርሌ ፡ ከነቃ ፡ አይሆንም ፡ ዕቃ» እየተባለ ፡ ሲተረት ፡ እሰማው ፡ የነበረው ፣ በኔ ፡ ላይ ፡ ደርሷል ። ቢሆንም ፡ ድካምዎን ፡ ማሰብና ፡ ለድካምዎ ፡ ዋጋ ፡ መስጠት ፡ አለብኝ ። ፈቃድዎንም ፡ መፈጸም ፡ ይኖርብኛል ፡ አልኳቸውና ፡ ተመለስን ።



በቤታቸው ፡ ስንደርስ ፡ ባለቤታቸው ፡ ደንግጠው ፡ ባላቸውን ፡ በፍራቻ ፡ አስተያየት ፡ እየተመለከቱ ፡ ልጄ ፡ ምን ፡ አልኩህ ፣ ምን ፡ ብበድልህ ፡ ነው ፡ እንደዚህ ፡ ጨክነህ ፡ የሄድከው ፡ ብለው ፡ እያለቀሱ ፡ ሳሙኝ ።

የአባትና ፡ የእናቴ ፡ ትዝታ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ በፊቴ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ እንጂ ፡ ገና ፡ ስላልጠፋ ፣ ለማልቀስ ፡ ምክንያት ፡ ስለምፈልግ ፣ ይልቁንም ፡ ለቅሶው ፡ በኔ ፡ ባሰ ። ለቅሶውን ፡ ተወት ፡ እናድርግና ፡ ከሩቅ ፡ መንገድ ፡ ተጉዘን ፡ ድካም ፡ የተሰማን ፡ ስለሆነ ፣ ምግብ ፡ ተመግበን ፡ አረፍ ፡ እንበል ፡ ብለው ፡ ባለቤቱ ፡ ስለተናገሩ ፣ ዕንባችንን ፡ ጠራርገን ፡ ፀጥ ፡ አልን ።

በማግስቱ ፡ ጥዋት ፡ ቁርስ ፡ ካደረግን ፡ በኋላ ፣ ስለወደፊቱ ፡ አኗኗራችን ፡ ባለቤቱ ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ንግግር ፡ በማድረግ ፡ መምሪያ ፡ ሲሰጡ ፣ ባለቤታቸውም ፡ ሆነ ፡ ልጆቻቸው ፣ እኔን ፡ እንዳያስቀይሙ ፣ የኔን ፡ የኑሮ ፡ ሁኔታ ፡ በቅርብ ፡ ራሳቸው ፡ ብቻ ፡ እንደሚከታተሉ ፡ ተናገሩ ።

ምንም ፡ መልስ ፡ አልሰጠንም ። በቁርስም ፣ በምሳም ፣ በራትም ፣ ጊዜ ፡ በርሳቸው ፡ አጠገብ ፡ ከፊታቸው ፡ እንድመገብ ፡ አደረጉ ። ሆኖም፡ ባለቤታቸው ፣ በአንደበታቸው ፡ አይናገሩ ፡ እንጂ፣ ምን፡ያህል ፡ ጥላቻና ፡ ይልቁንም ፡ ጠፍቼ ፡ በሔድኩ ፡ ጊዜና ፡ ከተመለስኩም ፡ በኋላ ፣ ባለቤታቸው ፡ የተናገርዋቸውን ፡ እያስታወሱ ፣ በኔ ፡ ላይ ፡ ያላቸው ፡ ጥላቻ ፣ ስለበረታባቸውና፡ በፊታቸው፡ ስለሚነበብ፡ ሆድ—ባሻ፡ እየሆንኩ ፡ ይከፋኝ ፡ ጀመር ።

ባለቤቱ ፡ መከፋቴን ፡ በፊቴ ፡ ዕያዩ ፡ ይጠይቁኛል ። ያጣሁ ፡ መስለኝ ፡ ምንም ፡ የጐደለብኝ ፡ የለም ፡ እያልኩ ፡ ፍንጭ ፡ አልሰጥ ፡ እንጂ ፣ በሌለሁበት ፡ ከቤተሰቦቻቸው ፡ ጋር ፡ መነጋገራቸው ፡ አልቀረም ። ርሳቸው ፡ በቅን ፡ ልቦና ፡ ስለኔ ፡ የሚያደርጉት ፡ ቁጣ ፣ በቤተሰባቸውና ፡ በኔ ፡ መካከል ፡ ጥላቸው ፡ እየተባባሰ ፡ ዓይኔን ፡ ለማየት ፡ አለመፈለጋቸውን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታ ፡ ገለጹልኝ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ የመኖር ፡ ተስፋዬ ፡ ተቆርጦ ፣ ለሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ እግሬ ፡ ወዳደረሰኝ ፡ ጠፍቶ ፡ መሄድን ፡ መረጥሁ ።

ሐሳብህን ፡ አትርሳና ፡ ያልተወሰነ ፡ አቅጣጫ ፡ ይዘህ ፡ እግርህ ፡ ወደ ፡ አደረሰህ ፡ ስትሔድ ፡ አትፈራም ? በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ዕድሜህስ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነበር ፡ ብዬ ፡ ጠየኩት ።



8*

የተለመደ ፡ ተረት ፡ አለ ፡ «የቸገረው ፡ ርጉዝ ፡ ያገባል ፤ ስትወል ድበት ፡ ገደል ፡ ይገባል» እንደተባለው ፡ የመቸገር ፤የመድረሻ ፡ ማጣት፡ ሌላ ፡ ምርጫ ፡ ስለሌለኝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ፍርሃት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፤ ግራ ፡ ይገባኝ ፡ ነበር ፤ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የአሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ልጅ፡ ነበርኩ ። ይሁንና ፡ ልጅነቴ ፡ በጣም ፡ ስለረዳኝ ፡ እግሬ ፡ ባደረሰኝ ፡ ሥፍራ ፡ ያየኝ ፡ ሁሉ ፡ በርኅራኄ፡ ተቀብሎኛል ። በዕለት ፡ ምግብና፡በመ ሳሰለው ፡ የሚበልጠውን ፡ ጊዜ ፡ አልተቸገርኩም ።

እንዲያውም ፡ ምቾትና ፡ ድሎት ፡ ባገኘሁበት ፡ በአንድ ፡ ሥፍራ ፡ ተወስኜ ፡ መኖር ፡ አስብና ፡ አመሌን ፡ አሳምሬ ፡ ስቀመጥ ፤ የሰዎች ፡ ጠባይ ፡ ተለዋዋጭነት ፤ እንደመልካቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ እየሆነብኝ ፡ የሰውን ፡ ጠባይ ፡ ለማወቅ ፡ ባለመቻሌ ፤ የተሻለ ፡ ያገኘሁ ፡ እየመሰ ለኝ ፤ ኑሮዬን ፡ በአንድ ፡ ሀገር ፡ ሳልወስን ፤ እስከ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ዕድ ሜዬ ፡ የዓለምን ፡ ግማሽ ፡ ዞርኩ ።

ሰው ፡ በቋንቋ ፤ በባህል ፡ በመልክ ፤ ከመለያየቱ ፡ በቀር ፡ በጠባዩ፡ ግን ፤ አንዱ ፡ ከሌላው ፤ ሌላው ፡ ከሌላው ፡ የባሰ ፤ ፍጥረት ፡ ዓለምን ፡ የሚያስጠላ ፡ ሆኖ ፡ አገኘሁት ።

አዬ ፡ ለካስ ፡ ሞኝ ፡ ነህና ፡ ወንድሜ ፤ ሰው ፡ በመልክ ፡ በቋንቋ ፤ በባህል ፤ ቢለያይ ፤ የተቀዳው ፡ ከአንድ ፡ ምንጭ ፡ ስለሆነ ፤ አንዱ ፡ ካንዱ ፤ ሌላው ፡ ከሌላው ፡ ምን ፡ የተሻለ ፡ ለውጥ ፡ የሚገኝ ፡ መስሎህ ፡ ነው ? ከሀገር ፡ ወደ ፡ ሀገር ፡ የተዘዋወርከው ፡ አልኩት ።

አዬ ፤ ባለማወቄ ፡ ነው ፤ ይህን ፡ ያህል ፡ መንከራተት ፡ የደረሰብኝ። ሰው ፡ በሆነው ፡ በራሱ ፡ መልክ ፡ እየተቸገረ ፤ ለችግሩ ፡ መፍትሔ ፡ ሳያገኝ ፡ የሚኖር ፡ መሆኑን ፡ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ተረድቻለሁ ።

ዓለምን ፡ ከወሰንዋ ፡ እስከ ፡ ወሰንዋ ፡ ዞሬ ፡ ባላይም፤ በኢጋማሽዋ፡ ያየሁትን ፡ ያላየሁት ፡ እንደማይለውጠው ፡ አምኜ ፤ ራሴን ፡ የማስጠጋ በት ፡ ስመርጥ ፤ ሰው ፡ በብዛት ፡ ከሚገኝበት ፡ ይልቅ ፤ በጫካ ፡ ውስጥ፡ የሚኖሩ ፡ አዕዋፍና ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ፍጥረታትን ፡ ድምፅ ፡ እየሰማሁ ፡ መኖርን ፡ መርጬ ፤ እግሬ ፡ ወደ ፡ አደረሰኝ ፡ ስጓዝ ፡ አሁን ፡ ከምንኜ ድበት ፡ ገዳም ፡ ደረስኩ ።

ሰው ፡ ነኝና ፡ ለጊዜው ፡ መፍራቴ ፡ አልቀረም ። ሆኖም ፡ ሁሉን ፡ ዐይቼ ፡ ማማረጫ ፡ ስለሌለኝ ፡ በዚሁ ፡ ሐሳቤ ፡ ጸናሁ ። በበለጠም ፡



ያጸናኝ ፤ ቢረዱዋቸው ፡ የሚመረቁ ፤ ባይረዱዋቸውም ፡ ከሰው ፡ ርዳታ፡ የማይፈልጉና ፡ የማይጠይቁ ፡ በመኖራቸው ፤ የራሴ ፡ መንፈስ ፡ እንደ መራኝ፡ የማገለግላቸውና፡ የምረዳቸው፡ ስለአገኘሁ፡ የመንፈስ፡ ደስታ ፡ እየተሰማኝ ፡ እነሆ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ኖርኩ ። ወደፊትም ፡ እኖር ፡ ይሆናል ። ግን ፡ ማን ፡ ያውቃል ፡ ብሎ ፡ ታሪኩን ፡ እንደጨረሰ ፡ ወደ ፡ ገዳሙ ፡ ከሚያደርሰው ፡ ጫካ ፡ ደረስን ።

የጫካው ፡ ሁኔታና ፡ በውስጡ ፡ ስለሚሰማው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ድምፅ፡ ለኔና ፡ ለመልከተኛው ፡ አዲስ ፡ ባይሆንም ፤ ለፀሐይና ፡ ለልጆቻችን ፡ አዲስ ፡ ሆኖባቸው ፤ ግራና ፡ ቀኝ ፡ በማየትና ፡ በማዳመጥ፤ ወደፊታቸው፡ በሔዱ ፡ መጠን ፤ የጫካው ፡ ከባድነትና ፡ አስፈሪነት ፡ እየተባባሰ ፡ በመሄዱ ፡ ጉድ ፡ ነው ፤ ለካስ ፡ ሰው ፡ ከቆረጠ ፡ የማይሠራውና ፡ የማይ ችለው ፡ ነገር ፡ የለም ።

ይህ ፡ ጫካ ፡ የተፈጠረው ፡ ለአራዊትና ፡ ለአዕዋፍ ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ እንዲኖርበት ፡ አይደለም ። ግን ፡ ሰዎች ፡ በብዛት ፡ ከሚኖሩበት ፡ ተጐ ራብተው ፡ ከሚኖሩ ፤ በጫካ ፡ ውስጥ ፡ ከአራዊትና ፡ ከአዕዋፍ ፡ ጋር ፡ መኖር ፡ መርጠው ፤ መኖሪያ ፡ አደረጉት ።እረ ፡ ወንድሜ ፡ ለመሆኑ ፤ አውሬው ፡ አያስፈራም ? በተራመድን ፡ መጠን ፤ ከጫካው ፡ ወጣ ፡ብሎ፡ አውሬ ፡ ቢጣላን ፡ በምን ፡ እንከላከላለን ፡ እያልኩ ፡ ፈራሁ ። አንተም፡ የሰጠኸን ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ የለም ። የሚተናኮል ፡ አውሬ ፡ ባለመኖሩ ፡ ነው ? ብላ ፡ ጠየቀች ፡ ፀሐይ ፡ ሰውነቷ ፡ እየሠጋ ።

በዚህ ፡ ጫካ ፡ አውሬ ፡ የለም ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ፤ ይሁንና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አውሬዎች ፡ ሲኖሩ ፤ ሰው ፡ ሲያዩ ፡ ከመሸሽ ፡ በቀር፤ ሰውን፡ አይጣሉም ። ብሎ ፡ መልእክተኛው ፡ መልስ ፡ ቢሰጥም ፤ ጫካው ፡ በነ ፋስ ፡ ኃይል ፡ በተወዛወዘ ፡ መጠን ፤ አውሬ ፡ የመጣ ፡ እየመሰላቸው ፡ እነፀሐይ ፡ መደናገጣቸው ፡ አልቀረም ።

ያም፡ ሆነ፡ ይህ ፤ ጫካ፡ ለጫካ፡ ተጉዘን ፡ የፀሐይ ፡ እናት ፡ ካሉበት፡ ደረስን ። እናትና ፡ ልጅ ፡ በተያዩ ፡ ጊዜ ፡ አንገት ፡ ለአንገት ፡ ተያይ ዘው ፡ እየተሳሳሙ ፡ ተላቀሱ ። በተለይ ፡ ፀሐይ ፡ በእናትዋ ፡ የሰውነት ፡ መለዋወጥ ፡ በጣም ፡ ኀዘን ፡ ተሰምትዋት ፤ ለቅሶዋ ፡ አላቋርጥ ፡ አለ ። ሆኖም ፡ ሁሉም ፡ እንደማያልፍ ፡ የለምና ፤ ፀሐይ ፡ ለቅሶውን፡ ተወት፡ አድርጋ ፡ ሁሉም ፡ ሲረጋጉ ፤ በዚያ ፡ ገዳም ፡ ከመንገድ ፡ ለገባ ፡ እንግዳ የሚደረግለት ፡ ግብዣ ፡ ቀርቦልን ፡ በመልካም ፡ አኳኋን ፡ ተጋበዝን ።

ከግብግቦ ፡ በኋላ ፡ በፀሐይ ፡ እናት ፡ መሪነት፡ አካባቢውን ፡ ሁሉ፡ ጐበኘን ። ቦታው ፡ ከሚያስገኘው ፡ የመንፈስ ፡ ደስታ ፡ የተነሣ ፤ ልቧ፡ ተማረከና ፤ እስካሁን ፡ ባለ ፡ ሕይወታዊ ፡ ኑሮዋችን ፡ ያልተሰማኝ ፡ ውስጣዊ ፡ የመንፈስ ፡ ደስታ ፡ ይሰማኛል ። እናንተስ ፡ ምን ፡ ይሰማችኋል ? ብላ ፡ ፀሐይ ፡ ጥያቄ ፡አቀረበችልኝ ።

በሁላችንም ፡ ዘንድ ፡ ያለውን ፡ ተናገርሽ ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ በሚኖርበት ፡ ዓለማዊ ፡ ኑሮ ፤ ይህን ፡ ያህል ፡ የመንፈስ ፡ ደስታ ፡ ቢያገኝማ ፤ በተስፋ ፡ የሚጠብቀውን ፡ ሌላውን ፡ ዓለም ፡ ወርሶ ፡ በደስታ ፡ ለመኖር ፡ ራሱን ፡ አይፈትንም ፡ ነበር ።

በዚህ ፡ የሚገኘው ፡ የመንፈስ ፡ ደስታ ፤ ከዚህ ፡ ወጣ ፡ ብለን ፡ ስንሔድ ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ የሚቆየው ፤ እስከተወሰነ ፡ ርቀት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ብዬ፡ መልስ ፡ ሰጠኋት ።

ከጉብኝታችን ፡ መልስ ፤ ፀሐይ ፡ ከእናትዋ ፡ ጋር ፡ ናፍቆትዋን ፡ ለመወጣት ፤ ባለማቋረጥ ፡ ሻያ ፡ ዐራት ፡ ሰዓት ፡ ሲነጋገሩ፤ ዕንቅልፍና፡ ድካም ፡ አልተሰማትም ፤ እኔን ፡ ድካም ፡ ሲጫነኝ ፡ ዐይታ ፡ የእማማ ፡ ናፍቆት ፡ አልከፈልልኝ ፡ ብሎ ፡ እንደሆነ ፡ አላውቅም ፤ ድካምና ፡ ዕንቅልፍ ፡ ርቀውኝ ፡ የሚሰማኝ ፡ ብርታትና ፡ ደስታ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ አለችኝ ።

ላንቺ ፡ የሚሰማሽ ፡ ሁሉ ፡ ለኛም ፡ ይሰማናል ። ይኸውም፡ ሰውን፡ ከሰው ፡ በመለየት ፡ ሳይሆን ፤ ዕድል ፡ ገጥሞት ፡ ይህን ፡ ቦታ ፡ የረገጠ ፤ ላንቺ ፡ የተሰማሽ ፡ ደስታና ፡ ብርታት ፡ ይሰማዋል ፡ ብዬ ፡ ስሜቴን ፡ አረጋገጥኩላት ።

ስለ ፡ ዓለማዊ ፡ ኑሮ ፡ አንሥተን ፡ በምንጨዋወትበት ፡ ጊዜ ፡ የፀሐይ ፡ እናት ፡ የንግግሩን ፡ መሥመር ፡ በድንገት ፡ ለውጠው ፡ የሚከተለውን ፡ የምክር ፡ ቃል ፡ ሰጡን ፡ «ልጆቼ ፡ ያሁኑ ፡ ግንኙነታችን ፡ የመጨረሻ ፡ ስለሆነ ፤ የመጨረሻ ፡ ቃል ፡ በምንለዋወጥበት ፡ ባሁኑ ፡ሰዓት፡ ልነግራችሁ ፡ የምወደው ፤ ለግል ፡ ደስታ ፡ ብላችሁ ፡ ራሳችሁን ፡ በመውደድ ፤ በሰው ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ እንዳትሠሩ ፡ ነው ።

በአካባቢያችሁና ፤ በምትኖሩበት ፡ ሀገር ፡ ችግረኛውና ፡ ደኃው ፡ ከበዛ ፡ ሠርቶ ፡ ራሱን ፡ በራሱ ፡ እንዲረዳ ፡ አድርጉ ፡ እንጂ ፤ የራሳችሁን ፡ ድሎትና ፡ ደስታ ፡ ብቻ ፡ እያያችሁ ፡ ለመኖር ፡ አትፈልጉ ። ይህ፡



ፍጐላት ፡ ከንቱ ፡ ፍላጐት ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ በናንተ ፡ ድሎትና ፡ ደስታ ፡ ልቡ ፡ የነደደ ፤ እርሱ ፡ ባመነበት ፡ ነገ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ የሚወስደው ፡ እርምጃ ፤ ከረዥም ፡ ጊዜ ፡ ትዕግሥት ፡ በኋላ ፡ ገንፍሎ ፡ የወጣ ፡ስለሆነ ፤ ለአድራጊቱ ፡ ሁሉ ፡ ይቅርታ ፡ አይኖረውም ።

ምድር ፤ በምድር ፡ ላሉ ፡ ሁሉ ፡ እኩል ፡ በረከትዋን ፡ ትሰጣለች ፤ ሀገርም፡ በሀገርዋ፡ ላይ፡ ለተወለዱ፡ ሁሉ ፡ ሀገር ፡ ስለሆነች ፡ ጉዳትዋ ፡ ለተወለዱት ፡ ትክክል ፡ እንደሚደርስ ፤ ጥቅምዋም ፡ በዚሁ ፡ መጠን ፡ ትክክል ፡ መድረስና ፡ መዳረስ ፡ አለበት ።

እማማ ፤ ነገርሺን ፡ አትርሺና ፡ «ያሁኑ ፡ ግንኙነታችን ፡ የመጨረሻ ፡ ነው ፡ ያልሽው ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ የማንገናኝበት ፡ ምክንያት፡ ምንድነው ? ፡ በሞት ፡ አትቅደሚኝ ፡ እንጂ ፤ ከቀድምኩሽ፡ ለኔ ፡ ዕድል፡ ነው ።

ለግል ፡ ደስታ ፡ ብላችሁ ፡ የራሳችሁን ፡ ድሎትና ፡ ደስታ ፡ የሚሰጠውን ፡ ብቻ ፡ በማስፋፋት ፡ ሌላውን ፡ በሚሊዮን ፡ የሚቈጠረውን ፡ ብትረሱ ፤ አኗኗራችሁ ፡ የመንፈስ ፡ ነፃነት ፡ የሌለው ፡ የሐሳብና ፡ የጭንቅ ፡ ኑሮ ፡ ይሆናል ።

ኧረ ፡ ለመሆኑ ፤ እዚህ ፡ አለኸበት ፡ ቦታ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ አኗኗር ፡ መኖሩን ፡ ማን ፡ ነግሮሽ ፡ ነው ፡ መምሪያ ፡ የሚሆን ፡ ጠቅላላ ፡ ሐሳብ ፡ የተናገርሽው ? ደግሞስ ፡ ሀገር ፡ የሁሉም ፡ ተወላጅ ፡ ብትሆን፤ ሁሉም ፡ በግንባሩ ፡ ሠርቶ ፡ ባገኘው ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ቢያደርግ ፡ማን፡ ከለከለው ?

እንግዲህ ፡ በመሥራት ፡ ፈንታ ፡ ጊዜውን ፡ በከንቱ ፡ እያባከነ ፡ የሀገርና ፡ የወገን ፡ ሸክም ፡ ለሚሆነው ፡ ምን ፡ መድኃኒት ፡ አለ ፡ ብላ፡ ፀሐይ ፡ በጣልቃ ፡ ገብነት ፡ ጠየቀች ።

ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ገለጣቸውን ፡ በመቀጠል ፤ አዬ ፡ ልጄ ፤ መቼ፡ እንዲህ ፡ ይሆንና ፤ ጊዜ ፡ ያው ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ አይለወጥም ። ይነጋል ፤ ይመሻል ፤ በጋና ፡ ክረምት ፤ ብርሃንና ፡ ጨለማ ፡ ጊዜያቸውን ፡ ጠብቀው ፡ ይለዋወጣሉ ። ሰውም ፡ እንደዚሁ ፡ የሚለዋወጥበት ፡ ጊዜ ፡ ስላለ ፤ እንደ ፡ ሰው ፡ አስተሳሰብና ፡ አስተያየት ፡ ለመራመድ ፡ መሞከር ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ እንዲህ ፡ ነበር ፤ በነበር ፡ ይሂድ ፤ ወይም ፡ በነበር ፡ ይቆይ ፡ ማለት ፡ በዛሬው ፡ አስተሳሰብ ፡ ሥፍራና ፡ ተቀባይ ፡ የሌለው ፡ አስተሳሰብ ፡ መሆኑን ፡ ማወቅ ፡ ይጠቅማል ።

ወደ ፡ ታሪክ ፡ ዓይናችንን ፡ ጣል ፡ ብናደርግ ፤ «አሪት ፡ እንኳን ፡ በሐዲስ ፡ ተሻሽሏል ። አሪት ፡ በሐዲስ ፡ ባይሻሻል » ፡ በሰዎች ፡ መካከልና ፡ በሰዎች ፡ አስተዳደር ፡ ዛሬ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ችግርና ፡ ሁከት ፡ ይፈጠር ፡ ነበር !

ሰዎች ፡ ሠርተው ፡ በግንባራቸው ፡ ወዝ ፡ ራሳቸውን፡ እንዲረዱ፡ የፍጥረት ፡ ግዴታቸው ፡ ነው ። ሆኖም ፡ ከዚህ ፡ መልካም ፡ መንገድ፡ ለሚወጣ ፡ አስገዳጅ ፡ ሥልጣን ፡ መኖር ፡ አለበት ።

ለዚህ ፡ ነው ፡ አንዱ ፡ መሪ ፡ ሌላው ፡ ተመሪ ፤ አንዱ ፡ አስተማሪ፡ ብዙዎች ፡ ተማሪዎች ፡ ሆነው ፤ በተዋረድ ፡ ሰዎች ፡ እንዲኖሩ ፡ የተፈጥሮ ፡ ግዴታ ፡ የሆነው ፡ ብለው ፡ በማስረዳት ፡ ምክራዊ ፡ አስተያየታቸውን ፡ ከአካፈሉን ፡ በኋላ ፡ ምርቃን ፡ ተቀብለንና ፡ ተሰናብተን በሰላም ፡ ወደቤታችን ፡ ተመለስን ።

# አመረረ ፡ ሆዴ ፡

እንግዲህስ ፡ ይብቃኝ ፤ ይብቃኝ ፡ ይህ ፡ ዓለም ፤
ወደ ፡ ገዳም ፡ ሔጄ ፡ ደግሞ ፡ እዚያ ፡ ልድከም ፤
በገዳም ፡ ማገልገል ፡ ከፍተኛው ፡ ጥቅም ።

ራስን ፡ ረስቶ ፡ ለሌላው ፡ መታዘዝ ፤
አለው ፡ ታላቅ ፡ ዋጋ ፡ ማፍሰስ ፡ ላብና ፡ ወዝ ።

በሕይወቴ ፡ ሙሉ ፡ የሠራሁት ፡ ሥራ ፤
ቢሠፈር ፡ ቢቈጠር ፡ በሒሳብ ፡ ምርመራ ።

እጅግ ፡ ነው ፡ መጠኑ ፡ ካልረዱኝ ፡ ሥላሴ ፤
ታዘብኩት ፡ ራሴን ፤ ፈረድኩኝ ፡ በነፍሴ ፤
ሳገለግል ፡ ኖርኩኝ ፡ ራሴ ፡ ለራሴ ።

የታዘዘው ፡ ትእዛዝ ፡ የተጻፈው ፡ ቃል ፤
አብልጦ ፡ ከራስም ፡ ወገን ፡ ማገልገል ።

ይልቅ ፡ ከወገንስ ፡ ራስ ፡ ተወደደ ፤
ብቻ ፡ ለራስ ፡ ማሰብ ፡ እጅግ ፡ ተለመደ ፤
ፍቅር ፡ መተሳሰብ ፡ አገር ፡ ጥሎ ፡ ሄደ ።



ከባድ ፡ አካል ፡ ራስ ፡ ይሸከማል ፡ ብዙ ፤
ይመራመር ፡ ያስብ ፡ ይፈጸም ፡ ትዕዛዙ ።

የሚቃወም ፡ ትዕዛዝ ፡ ወንጀለኛ ፡ ይጥፋ ፤
በመላው ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ ሰላም ፡ እንዲሰፋ ።

እኖራለሁ ፡ እኔስ ፡ ጫካውን ፡ ለብሼ ፤
ዘወር ፡ ብዬም ፡ አላይ ፡ ዓለምን ፡ መልሼ ።

ዓለም ፡ ዓለም ፡ እያልኩ ፡ ስወዳት ፡ በጣም ፤
በመውጣት ፡ በመውረድ ፡ አገኘኝ ፡ ድካም ።

አይቀር ፡ ከደከምኩኝ ፡ ከተንገላታሁ ፤
ለመርዳት ፡ ሌሎችን ፡ እፈልጋለሁ ።

ሰውን ፡ ሰው ፡ ሊረዳው ፡ ካለው ፡ ፍላጐት ፤
ርግፍ ፡ አድርጐ ፡ ትቶ ፡ የራስን ፡ ምኞት ፤
ለሀገር ፤ ለወገን ፡ ከልብ ፡ መሥራት ።

ምኞትና ፡ ሐሳብ ፡ አብረው ፡ ይኖራሉ ፤
በሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ ይመካከራሉ ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ አልሆነም ፡ ሥጋ ፡ አሸናፊ ፡ ነው ፤
የሚመራው ፡ ሁሉም ፡ በሥጋ ፡ ፈቃድ ፡ ነው ።

ተገዛሁ ፡ እስካሁን ፡ ለሥጋ ፡ ፈቃዴ ፤
በቃኝ ፡ እንግዲህስ ፡ አመረረ ፡ ሆዴ ።

ክፍል ፡ ፰ ፡

# የቤት ፡ ሰብ ፡ ውይይት ፡

ከፀሐይ ፡ ጋር ፡ ባለን ፡ ኑሮ ፡ «ሚስትህ ፡ በቤት ፡ እልፍኝ ፡ ውስጥ ፡ እንደሚያፈራ ፡ ወይን ፡ ናት ። ልጆችህም ፡ በማዕድህ ፡ ዙሪያ ፡ እንደ ፡ ወይራ ፡ ቡቃያ ፡ ናቸው» ፡ ተብሎ ፡ ከተነገረላቸው ፡ ቤተሰቦች፡ አንዱ፡ መሆናችን ፡ ተሰማን ። ፀሐይ ፡ እንደገናም ፡ ፀነሰች ።

መውለድ ፡ ያቋረጥኩ ፡ መስሎኝ ፡ ነበር ፤ በሞት ፡ የተለዩን ፡ እናትህን ፤ በአኗኗር ፡ የራቀች ፡ እናቴን ፡ ላስታውሳቸው ፡ ነው ። ርግዝ ናው ፡ ሳይሰማኝ ፤ ምጡ ፡ ደርሶ ፡ በመውለዷ ፡ ርግዝናና ፡ ምጥ ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ረስቼው ፤ ጭንቁ ፡ ትዝ ፡ ሳይለኝ ፡ ቆይቼ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ እንጃ ፡ ባባሁ ። ሆዴም ፡ ፈራ ፤ ማንስ ፡ ያበረታታኛል ። ቆይቶ ፡ የመጣ ፡ ስለሆነ ፤ ለሕይወቴ ፡ ጭምር ፡ ነው ፡ የአሠጋኝ ፡ ስላለች ፡ ፀሐይ ፤ ከው ፡ ብዬ ፡ ደነገጥኩ ።

ቢሆንም ፡ እንዳይታወቅ ፡ ፈልጌ ፤ መናገርም ፡ ተሳነኝና ፡ ከት ካዜ ፡ ጋር ፡ ዝምታ ፡ አበዛሁ ።

መልስ ፡ ባለማግኘቷ ፡ ምነው ፡ መልስ ፡ ነፈግኸኝ ፤ በፊትህም ፡ ላይ ፡ ድንጋጤ ፡ ይታያል ። እኔ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ አስታውሼ ፡ ሆዴ ፡ እየ ባባ ፡ ድንጋጤ ፡ ሲሰማኝ ፤ አንተም ፡ ከኔ ፡ የባሰ ፡ ደነገጥክ ፡ እንዴ ፡ መክብብ ፡ ብላ ፡ እንደገና ፡ ጠየቀችኝ ።

ማሰብና ፡ መደንገጥ ፡ የሥጋ ፡ ባሕርይ ፡ ሆኖ ! አይቀርም ፡ ሁን ፡ ያለው ፡ ይሆናል ። ያላለውም ፡ አይሆን ። የርግዝናሽን ፡ ዜና ፡ ስትነግ ሪኝ ፡ በደስታ ፡ ፈንታ ፡ ቅር ፡ ያለኝ ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ የመጀመሪያና ፡ የመጨረሻ ፡ ሁኔታ ፡ ሕሊናዬን ፡ ስለመታው ፡ ነው ፡ ያዘንኩት፡ እንጂ ፡ በልጅ ፡ በኩል ፡ ያሉን ፡ ይበቃሉ ። ሰው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ዞሩ ፡ እንደ ምድር ፡ አሸዋ ፡ ቢበዛ ፡ ጥቅሙ ፡ ምንድነው? በመውጣት ፡ በመውረድ ፡ ይኖርና ፡ ከድካሙ ፡ የሚያርፈው ፡ ሞትን ፡ ነው ፤ ደግሞም ፡ ማንም ፡ ከዚህ ፡ አያመልጥም ። በብዛት ፡ የሰበሰበውን ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ ሳያይ ፤ አንዱ ፡ በአንዱ ፡ ዛሬ ፡ ይሸኛል ። ሌላው ፡ ደግሞ፡ በሌላው ፡ ነገ ፡ እየ

ተሸኘ ፣ ዓለም ፡ የመጣውን ፡ የምትሸኝ ፣ ያልመጣውን ፡ የምትቀበል፣ የወረት ፡ ዓለም ፡ ናት ።

ዓለም ፣ የሰውን ፡ ጠባይ ፡ ዐውቃ ፡ በወረት ፡ ሰውን፡ ስትለዋውጥ፡ ሰው ፡ ግን ፡ የዓለምን ፡ ጠባይ ፡ ሳያውቅ ፡ ይኖራል ። ባለማወቁማ ፡ ነው ፣ ራሱን ፡ ብቻ ፡ እየወደደ ፡ የወረተኛዋን ፡ ዓለም ፡ በረከት ፣ ደስታና ፡ ብልጽግና ፡ ብቻዬን ፡ ልያዝ ፡ እያለ ፣ ርስ ፡ በርሱ ፡ አጥፊና ፡ ጠፊ ፡ ሲሆን ፣ ዓለም ፡ ግን ፡ እየሳቀች ፣ ያሰለቻትን ፡ ስትሸኝ ፣ ያላወቃትን ፡ ትቀበላለች ።

ሐሳብህን ፡ አትርሳና ፡ ይህ ፡ አስተሳሰብ ፡ ከአዕምሮህ፡ ሊመነጭ፡ የቻለው ፡ በምንና ፡ ከምን ፡ የተነሣ ፡ ነው ፡ ብላ ፡ ፀሐይ ፡ ጠየቀችኝ ።

ጥያቄሽ ፡ መልካም ፡ ነው ፣ ይህ ፡ አስተሳሰብ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ወደፊትም ፡ የሚኖር ፡ ነው ። በሰዎች ፡ ላይ ፡ አንዳንድ ፡ ነገር ፡ ባየሁ፡ ጊዜ፡ እየተሰማኝ ፡ በበለጠ ፡ እስታውሰዋለሁ ። እንዲያውም ፣ ሳይከዳኝ ፡ እያነጋገረኝ ፡ የሚኖር ፡ ጓደኛዬ ፡ ነው ።

የልጅ ፡ አበባ ፡ ባላየሁበት ፡ ጊዜ ፡ የነበረኝ ፡ ስሜትና ፡ ልጅ ፡ ከወለድን ፡ በኋላ ፣ ያለኝ ፡ አስተያየት ፡ የተለያየ ፡ ሆንዋል ። ርግጥ ፡ ነው ፣ ልጅ ፡ ሳንወልድ ፡ በልጅ ፡ ላይ ፡ ይደርስ ፡ የነበረው ፡ ማናቸውም፡ ነገር፡ቁስሉ ፡ እምብዛም ፡ አይሰማኝም ፡ ነበር ። ከወለድኩ ፡ በኋላ ፡ ስለ ልጆች ፡ ስሰማ ፡ ሰውነቴ ፡ ይሰቀቃል ።

ጉዳዩን ፡ በቁም ፡ ነገር ፡ አስተሳሰብ ፡ ስንመለከተው ፣ ልጅ ፡ መውለድ ፡ በርግጥ ፡ ጥሩ ፡ ነው ። ባንድ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ማንም ፡ የሚያውቀው ፡ መቀጫ ፡ ነው ። « አባትና ፡ እናትህን ፡ አክብር » የተባለውን ፡ ሕግ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለማስከበር ፡ ጥንታዊው ፡ የልጆች ፡ አስተዳደግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ነበረው ። ዛሬ ፡ ግን ፡ የአስተዳደጉ ፡ ጠባይ ፡ ከጊዜው ፡ ሁኔታ ፡ ጋር ፡ ሲለወጥ ፣ አባቶች ፣ በልጆች ፡ ተደፈሩ ። ልጅ ፡ በአባትና ፡ በእናት ፡ ላይ ፡ አፉን ፡ ከፈተ ። እጁን ፡ ሰነዘረ ። ከአባትና ፡ ከእናት ፡ ይልቅ ፡ የገንዘብ ፡ ፍቅር ፡ በልጅ ፡ ላይ ፡ አድሮ ፣ አባትና ፡ እናት ፡ በገንዘብ ፡ ተለውጠው ፣ ከሕይወታቸው ፡ ጥፋታቸው ፡ ተመረጠ ። ይህ ፡ በዘመናችን ፡ ሲፈጸም ፡ ዐየን ። ወደፊት ፡ የሚሆነውንስ ፡ ማን፡ ያውቃል ? ስል ፣

ምን ፡ ማለትህ ፡ ነው ? ከአንተ ፡ የማልጠብቀውን ፡ ሰማሁ ። አለችና ፣ የልጆች ፡ መልካም ፡ አስተዳደግ ፡ የሚመሠረተው ፡ በወላጆች ፡



ቍጥጥር ፡ ነው ። ጥንትም ፡ ቢሆን ፣ ጥብቅ ፡ ቍጥጥር፡በማድረግ ፣ የልጆችን ፡ መልካም ፡ አስተዳደግ ፡ የገነቡ ፡ ወላጆች ፡ ናቸው ። አሁንስ ፡ ወላጆች ፡ ስለልጆቻቸው ፡ አስተዳደግ ፡ መልካም ፡ መሠረት ፡ ቢጥሉ ፣ ወይም ፡ ያባቶችን ፡ ቢከተሉ ፡ ማን ፡ ከለከላቸውና ፡ ነው ? የዛሬውን ፡ ስድ ፡ የጥንቱን ፡ ጥብቅ ፣ እያደረግህ ፡ የምትናገረው ፡ አለችኝ ፡ ፀሐይ ።

ለምሳሌ ፡ በልጆቻችን ፡ ላይ ፡ ጥብቅ ፡ ቍጥጥር ፡ ብናደርግ ፣ አካባቢው ፡ ካልተባበረበት ፡ የኛ ብርቱ ፡ ቍጥጥር ፡ ብቻ ፡ ችግሩን፡ ሊያስወግደው ፡ አይችልም ፣ ብዬ ፡ በሐሳቤ ፡ ያቀድኩትን ፡ ሳልቀጥል ፣ ልጃችን ፡ በመካከላችን ፡ ተቀምጦ ፡ ያዳምጥ ፡ ስለነበር ፣ የልጆች ፡ አስተሳሰብ ፡ በምን ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ እንደሆነ ፡ ለካስ ፡ ገና ፡ አልተገነዘባችሁም ፡ ብሎ ፡ በንግግራችን ፡ ጣልቃ ፡ ሲገባ ፣ ከመደነቅ ፡ ጋር ፡ ደንግጠን ፡ ፀጥ ፡ አልን ። ልጁም ፡ ንግግሩን ፡ ሳያቋርጥ ፣ የምትሰሙኝ ፡ ከሆነ ፣ ልጆች ፡ የሚሉትን ፡ ልንገራችሁ ፡ ብሎ ፡ ያወርደው ፡ ጀመር ።

የጥንት ፡ ልጆችና ፡ የዛሬ ፡ ልጆች ፡ አስተዳደግ ፡ ሊመዛዘን ፡ አይችልም ። ኻያኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የዕውቀት ፡ ( የቴክኖሎጂ ) ዘመን፡ ስለሆነ ፣ የዛሬ ፡ ልጆች ፡ አስተሳሰብ ፡ ከዕድሚያቸው ፡ ጋር ፡ ሳይነፃፀር ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ያስታውላሉ ።

ሀገራቸው ፡ ያለችበትን ፡ ከሌላው ፡ ጋር ፡ ሲያስተያዩ ፣ ሀገራቸው፡ ካደጉት ፡ አገሮች ፡ እንዷ ፡ ሆና ፡ እንድትቈጠር ፡ እንኳ ፣ ወደኋላ ፡ ቀርተዋል ፣ ከሚባሉት ፡ ጋር ፡ ብትቈጠር ፡ አይወዱም ።

ለምን ፡ ወደኋላ ፡ እንደቀረች ፡ ይመራመራሉ ። ከመመራመራቸው ፡ የተነሣ ፣ ጉድለት ፡ መስለው ፡ የሚታዩ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታዎች ፡ በፊታቸው ፡ ቀርበው ፡ ያስጨንቃቸዋል ። ለምን ፡ ይህ ፡ እንዲህ ፡ ሆነ ፡ ብለው ፡ ለማወቅ ፡ ሲፈልጉ ፣ ምን ፡ አገባችሁ ፡ ልጆች ፡ ናችሁ ፡ ይባላሉ ።

የሀገር ፡ ጉዳይ ፣ ኃላፊነትና ፡ ፍቅርዋ ፡ በልጆችዋ ፡ ላይ ፡ ሊመሠረት ፡ የሚገባው ፡ በልጅነት ፡ አዕምሮ ፡ ከቀለም ፡ ትምህርት ፡ ጋር ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ ብለው ፡ ቢናገሩም ፡ ተቀባይ ፡ የላቸውም ።

ልዩ ፡ ልዩ ፡ መጻሕፍት ፡ በማንበባቸው ፡ የማያውቁትን ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ያውቃሉ ። በጆሮአቸው ፡ ይሰማሉ ። በዓይናቸው ፡ ያያሉ ።

ማወቅ ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ። ባወቁት ፡ ሥርቶ ፡ ለመጠቀምና ፡ ለመጥቀም ፡ ካልተቻለ ፤ ከማወቅ ፡ አለማወቅ ፡ የሚመረጥበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ።

እንግዲህ ፡ ይህ ፡ ዓይነቱ ፡ አስተሳሰብ ፡ በጥንት ፡ ልጆች ፡ አዕምሮ ፡ አይኖርም ፡ ይሆናል ። እንደዛሬ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በየቀበሌያቸው ፡ በብዛት ፡ ኖሮ ፡ የመማር ፡ ዕድል ፡ በዘመናቸው ፡ አላገኙም ፡ ይሆናል ። መጻሕፍት ፡ የማንበብ ፡ ዕድላቸው ፡ ጠባብ ፡ ሆኖ ፡ የዓለምን ፡ መነሣትና ፡ መውደቅ ፤ ዕለት ፡ በዕለት ፡ እየተከታተሉ ፡ አልሰሙም ፡ ይሆናል ። በዓይናቸውም ፡ ያዩት ፡ አልነበረም ። ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ የጥንት ፡ ልጆች ፡ አስተዳደግና ፡ የዛሬ ፡ ልጆች ፡ አስተዳደግ ፡ እየተነጣጠረ ፡ የዛሬ ፡ ባለጊዎች ፤ የጥንት ፡ ጨዋዎች ፡ እየተባለ ፡ ሊነገር ፡ የማይገባ ፡ ነው ።

የዘመኑ ፡ ልጆች ፡ አስተዳደግ ፡ ዘመኑ ፡ ከሚጠብቀው ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ነው ። ገና ፡ በሕፃንነት ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ ለመጫወቻ ፡ ተብሎ ፡ የሚሰጠው ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ትምህርታዊ ፡ አስተያየት ፡ የሚሰጣቸው ፡ ስለሆነ ፤ ከዚህ ፡ ዕድሜ ፡ ጀምረው ፡ ለማወቅ ፡ የሚፈልጉት ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ በፊታቸው ፡ አለ ።

ለምሳሌ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የመጫወቻ ፡ መሣሪያዎች ፡ ሲሰጥ ፡ እንደምን ፡ ሆነው ፡ እንደተሠሩ ፡ ለማወቅ ፡ ይደክማሉ ። ፈታተው ፡ ብትንትን ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ መልሰው ፡ እንደገና ፡ ለመገጣጠም ፡ ይሞክራሉ።

ይህን ፡ ይዞ ፡ ያደገ ፡ ልጅ ፡ በትምህርት ፡ ገበታ ፡ ቀርቦ ፡ ትምህርት ፡ ሲከታተል ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መጻሕፍት ፡ ሲያነብ ፡ ሲሰማና ፡ ሲያይ፤ የሌሎቹንና ፡ የራሱን ፡ እያስተያየ ፡ ለምን ፡ ይህ ፡ ሆነ ፤ ለምን ፡ ይህ ፡ አልተደረገም ፡ ማለት ፡ የማይቀር ፡ ነው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የሆነውን ፡ እንደሆነ ፤ ሊሆን ፡ ሲገባ ፤ ያልሆነው ፡ በምንና ፡ በምን ፡ ችግር ፡ እንዳልሆነ ፤ በማስረዳት ፤ ለዘመኑ ፡ ጥያቄ ፡ መልስ ፡ መስጠት ፡ የሚቻለው ፡ በዚህ ፡ መንገድ ፡ እንጂ ፤ ልጆች ፡ ናቸው ። ምን ፡ አገባቸው ፡ ብሎ ፡ ማለት ፡ ነገሩን ፡ በበለጠ ፡ ያባብሰዋል ፡ እያሉ ፡ ነው ፡ ልጆቹ ፡ በበኩላቸው ፡ የሚያስቡት ፡ አለን ።

ያልጠበቅነውን ፡ ከልጃችን ፡ በመስማታችን ፡ ተገረምን ። ልጁ ፡ የገባህ ፡ አይመስለኝም ። የጨዋ ፡ ተረት ፡ ልንገርህ ፤ አለችና ፡ ፀሐይ ፡ « ከበሮ ፡ በሰው ፡ እጅ ፡ ያምራል ፤ ሲይዙት ፡ ይደናገራል » ይባላል ።



ይህ ፡ መሆን ፡ ሲገባ ፡ ለምን ፡ ይህ ፡ ሆነ ? ማለት ፡ የሚከፋ፡ አልነበርም፡ ዛሬ ፡ ተች ፤ ነቃፊና ፡ ተቆርቋሪ ፡ የነበረ ፤ ነገ ፡ የቦታው ፡ ወራሽ ፡ ሆኖ ፡ ከወንበሩ ፡ ላይ ፡ ገብ ፡ ሲል ፤ እንኳን ፡ የተሻለ ፡ ሊሠራ ፡ የነበረውን ፡ እንዳልነበር ፡ ያደርጋል ።

ልጁ ፡ ከተሠራ ፡ መሻሻል ፡ እንኳን ፡ ሰው ፤ እንስሶችስ ፡ ይጠሉታል ? የዘመኑ ፡ ዕድገትና ፡ የመሻሻል ፡ ኑሮ ፤ በሰው ፡ ብቻ ፡ ሳይወሰን ፤ ለእንስሶችና ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ አውሬዎች ፡ ጭምር ፡ ጠቅሟል ።

እንዲያውም ፡ በአንዳንድ ፡ ሀገር ፡ የሚታየው ፡ የእንስሳትና ፡ የአውሬዎች ፡ የኑሮ ፡ ይዞታ ፤ በአንዳንድ ፡ ሀገር ፡ ከሚታየው ፡ የሕዝብ ፡ አኗኗር ፡ የበለጠ ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ። « የሰው ፡ ወርቅ ፡ አያደምቅ » እንደሚባለው ፤ በሰው ፡ ላይ ፡ አምሮ ፡ የምናየው ፤ በታምራት ፡ ሳይሠሩ፡ ሰዎች ፡ ሳይንቀሳቀሱ ፡ ተባብረው ፡ የሠሩት ፡ የሥራ ፡ ፍሬያቸው ፡ ነው ።

ያም ፡ አለ ፡ ያ ፤ እኛ ፡ መሻሻልን ፡ ስንፈልግ ፤ ፍላጐታችንን ፡ የምንፈጽመው ፡ በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ አይደለም ። አባቶች ፡ ከልማድ ፡ ያገኙት፡ ትምህርት ፡ ከሊቃውንት ፡ ትምህርት ፡ ቤት፡ ተመርቆ ፡ ከወጣ ፡ ተማሪ፡ ስለማያንስ ፡ ሁለቱንም ፡ ወገኖች ፡ አስማምቶ ፡ መሥራት ፡ ያስፈልጋል ፡ አለች ፡ ፀሐይ ።

ልጁ ፡ ለእናቱ ፡ መልስ ፡ ሊሰጥ ፡ ሲዘጋጅ ፤ ልጁ ፡ ያንተና ፡ የኛ ፡ መከራከር ፡ ለበሽታው ፡ መድኃኒት ፡ የማይሰጥ ፤ ማንኛችን ፡ ትክክለኛ ፡ መንገድ ፡ እንደያዝን ፡ በዳኝነት ፡ መልክ ፡ የሚያመዛዝን ፡ በሌለበት ፡ በባዶ ፡ ሜዳ ፡ ብንነጋገር ፡ ዋጋ ፡ ስለሌለው ፤ ተወት ፡ እናድርገውና ፡ አንተም ፡ ከእኅቶችህ ፡ ጋር ፡ ሂድ ፡ ተጫወት ፡ ብዬ ፡ ስላሰናበትኩት ፤ ከመካከላችን ፡ ተነሥቶ ፡ ሄደ ።

የአባቱን ፡ ትዕዛዝ ፡ ለመፈጸም ፡ ያህል ፡ ልጁ ፡ ከመካከላችን ፡ ተነሥቶ፡ ይሂድ ፡ እንጂ ፤ አካሄዱ ፡ በቅሬታና ፡ በትካዜ ፡ መሆኑን ፡ እናቱ ፡ ተገንዝባ ፤ ይህን ፡ ልጅ ፡ አሳዘንከው ፡ መሰል ፡ ተክዞ ፡ ሄደ ፡ አለችኝ ።

ከርሱ ፡ ጋር ፡ የበለጠ ፡ ክርክር ፡ አድርገን ፡ በአነጋገሩ ፡ ጠንካራነት ፡ የበለጠ ፡ ከሚከፋን ፡ አሁን ፡ ከፍቶት ፡ ቢሄድ ፡ ይሻላል ፡ አልኳት ። ቀጥዬም ፡ በልጆችና ፡ በወላጆች ፡ መካከል ፡ ምን ፡ ያህል ፡ የአስተሳሰብ ፡ መለያየት ፡ እንዳለ ፡ አስተዋልሽ ? ይህን ፡ ተወት ፡ እናድር

ገውና ፡ ለነገሩ ፡ መነሻ ፡ ወደሆነው ፡ እንመለስ ፡ በማለት ፡ የዚህን ፡ ጉዳይ ፡ ዘጋሁት ።

ፀሐይ፡ ብዬ፡ ስጠራሽ፡ ሰውነቴ፡ በደስታ፡ ይረካል።በመካከላችን፡ የተገኙት፡ ልጆች፡ ይባረኩ፡ እንጂ፤ ይበቁናል። ሆኖም፡ሌላም፡ ከሰጠን፡ ፈቃድህ ፡ ይሁን በማለት ፡ እንቀበለው ፡ ፅንስ ፡ እንደያዝሽ ፡ ማንም ፡ ሳያውቅ ፡ አንቺው ፡ ገለጥሽው ፤ እናቴና ፡ እናትሽ ፡ እያበረታቱሽ ፡ በም ጥሽ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ በቅርብ ፡ ሆነው ፡ በአሳብ ፡ ይረዱሽ ፡ ስለነበር ፡ ይህ ፡ እየታወሰሽ ፡ ሆድሽ ፡ እንደሚባባ ፡ ይሰማኛል ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ ለሰው ፡ ሞግዚት ፡ ሆኖ ፡ የሚኖረው ፡ ለምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ይመስልሻል ? እንዲያውም ፡ ነቢዩ ፡ « በሰው ፡ ከመታመን ፡ በእግዚአብሔር፡ መታመን፡ » እንደሚገባ፡ የተናገረውን ፡ ማስታወስ ፡ አለብን ፡ አልኳት ።

ውዴ ፤ እንዴት ፡ ሰው ፡ በሰው ፡ ይታመናል ፡ ለጊዜው ፡ እየመ ሰለው ፡ በሰው ፡ እየታመነ ፤ ምኞት ፡ ወይም ፡ ፍላጐት ፡ ሲፈጸም ፤ ዕድሜ ፡ ለእገሌ ፡ ይላል ። ያሰበው ፡ ሲፈጸም ፡ ያመሰገነውን ፡ ያህል ፡ ያሰበውም ፡ ሲሰናከል ፡ ጥላቻው ፡ እንደዚሁ ፡ የበረታ ፡ ይሆናል ። ግን፡ ማናቸውም ፡ ሥራ ፡ የሚገለጠው ፡ በሰው ፡ ስለሆነ ፤ ሰው ፡ ለደግም ፡ ሆነ ፡ ለክፉ ፡ መሣሪያ ፡ ነው ።

ስለሰው ፡ ኑሮ ፡ የሚመራመሩ ፤ ከራሳቸው ፡ ደስታ ፡ ይልቅ ፤ ስለ ጠቅላላው ፡ የሰው ፡ ኑሮ ፡ የሚያደርጉት ፡ ትግል ፡ ቢከሽፍም ፤ የዓላ ማቸው ፡ ተከታይ ፡ ይነሣና ፡ ዓላማቸው ፡ ይፈጸማል ። በዓላማቸው ፡ ተቀስፈው ፤ የዓላማቸውን ፡ ውጤት ፡ ያላዩ ፡ በመንፈስ ፡ ያያሉ ።

ውዴ ፡ የልጆች ፡ አስተሳሰብ ፡ በምን ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ መሆ ኑን ፡ ልጃችን ፡ ሲነግረን ፤ አስተሳሰባቸው ፡ ከዚህ ፡ የተለየ ፡ አለመሆ ኑን ፡ ታስተውስ ፡ የለም ፡ አለችኝ ።

የሐሳብ ፡ አቀራረብሽ ፡ መንፈሴን ፡ ስለማረከው፡ አዳመጥኩሽ ፡ እንጂ ፤ በንግግርሽ ፡ መካከል ፡ ጣልቃ ፡ እየገባሁ ፡ ባነጋገርሽ ፡ እወድ ፡ ነበር ።

ባለፈው ፡ ውይይታችን ፡ የጠቅላላውን ፡ የልጆች ፡ አስተሳሰብ ፡ ልጃችን ፡ ሲገልጥልን ፡ ከርሱ ፡ እንደበት ፡ በመስማታችን ፡ ቅር ፡ መሰ ኘታችንን ፡ ታስታውሻለሽ ።



ባንቺ ፡ የአሳብ ፡ አገላለጥ ፡ ደግሞ ፤ ከዚያ ፡ ያልተለያየ ፡ በመስ ማቴ ፡ ምን ፡ ለወጠሽ ፡ ብዬ ፡ ገረመኝ ፤ እንጨት ፡ ነዶ ፡ ነዶ ፡ ፍም ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፤ በአመድ ፡ ሲያዳፍኑት ፡ ፍሙ ፡ አይጠፋም ። ገለጥ ፡ ሲያደርጉት ፡ ፍሙ ፡ እንዳለ ፡ ይገኛል ። እንደዚሁም ፡ በብዙ ዎች ፡ እየተደገፈ ፡ የሚነሳሳን ፤ ለጊዜው ፡ በዚያም ፤ በዚህም ፡ እያሉ ፡ ቢያዳፍኑት ፤ በፍሙ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ እሳት ፡ አይጠፋም ። ጠፍቶ ፡ እን ዲቀር ፡ ከተፈለገ ፡ ኅብረተሰቡ ፡ አምኖ ፡ የሚቀበለው ፤ የኅብረተሰቡን፡ ጠቅላላ ፡ ደኅንነት ፡ የሚሸፍንና ፤ መልካም፡ ፈቃድ ፡ ያለው ፡ ትውልድ፡ የሚተካ ፡ ሥራ ፡ ሊሠራ ፡ ይገባል ።

ትውልድ ፡ ለመተካት ፡ የሚያበቃ ፡ ሥራ ፡ ሰው ፡ በሕይወቱ ፡ካላ ቆየ ፤ ትውልድ ፡ አልፎ ፡ ትውልድ ፡ ቢተካም ፤ ተተኪው ፡ ትውልድ ፤ በሌላው ፡ የጠላውን ፡ ካልተወና ፡ በሥራ ፡ ካልገለጠ ፤ ሰው ፡ ሄዶ ፡ ሰው ፡ ቢተካ ፤ ሰው ፡ ሰው ፡ በመሆኑ ፤ በሚሠራ ፡ ወይም ፡ በሠራው ፡ መደነቅ ፡ መገረምም ፤ ማዘንም ፡ የለበትም ። ምንጩ ፡ ያው ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ ሥራው ፡ ሁሉ ፡ ያው ፡ የሰው ፡ ሥራ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ሳስረዳት ፡ እንቅልፍ ፡ ስለገረዘዛት ፡ ለነገሩ ፡ እልባት ፡ ሳናደርግለት፡ ወደመኝታ ፡ ክፍላችን ፡ አመራን ።

የኔን ፡ እንቅልፍ ፡ ወስዳው ፡ እንደሆነ ፡ እንጃ ፤ ፀሐይ ፡ ከጕን ፡ ጐኗ ፡ ሳትገላበጥ ፡ ነጋላት ። በዚያ ፡ ሌሊት ፡ እንቅልፍ ፡ አልይዘኝ ፡ አለ ፡ የሕፃንነት ፡ ዘመኔን ፡ አሳልፌ ፤ ማስተዋል ፡ ከጀመርኩ ፡ አሁን ድረስ ፡ የሠራሁትንና ፡ የሰማሁትን ፤ ያየሁትንም ፤ እመመርመር ፡ ገባሁ ።

በኃይላቸው ፡ ኃያላን ፡ ነን ፤ በዕውቀታቸው ፡ ዐዋቆች ፡ ነን ፤ በሀብ ታቸው ፡ ሀብታሞች ፡ ነን ፤ በክብራቸው ፡ ከብረናል ፤ ይሉ ፡ የነበሩ ፡ ስም ፡ ከመልክ ፡ ዐውቃቸው ፡ የነበሩት ፡ ትናንት ፡ ያየኋቸው ፡ ዛሬ ፡ ወዴት ፡ አሉ ፤

ትናንት ፡ ያየኋቸውና ፡ የማውቃቸው ፡ ወዴት ፡ ሄዱ ፡ ብዬ ፡ ሳስ ብ ፡ ተመሳሳይ ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው ፡ ተተክተው ፤ ዕድሜዬ ፡ ተራዝሞ፤ ያለምንም ፡ ለውጥ ፡ ይህን ፡ ሳይ ፤ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ዘመን ፡ ከተቆ ጠረ ፡ ጀምሮ ፡ ሰንቱ ፡ አልፎ ፡ ስንቱ ፡ ተተካ !

በኃላፊና ፡ በተተኪ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ ስመረምር ፤ ዘመናት ፡ እየተፈራረቁ ፡ ዓለም ፡ የደኅንነትና ፡ የግፍ ፡ መፈጸሚያ ፤ አውድማ ፡ ሆናለች ።

አራቱ ፡ ወንጌላውያን ፡ በየዓመቱ ፡ ሲለዋወጡ ፤ የሰው ፡ ልጅ ፤ ዘመኑን ፡ የሰላም ፤ የጤናና ፡ የደስታ፡ ዘመን ፡ እንዲሆንለት ፡ ምኞቱን፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታ ፡ ይገልጣል ።

የዘመናትን ፡ ሰላም ፤ ጤናና፡ ደስታ ፡ የሰው፡ ልጅ፡ የሚፈልገው ፤ በዘመኑ ፡ የሚደርሰውን ፡ ጥፋት ፤ ዘመኑ ፡ ያመጣበት ፡ እየመሰለው ፡ ቢቸግረው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ዘመናት ፡ በበኩላቸው ፡ ቢጠየቁ ፡ የሚማረሩት ፡ በሰው ፡ ልጆች ፡ ይሆናል ።

ዘመናት፡ በአሥራ ፡ ሁለት ፡ ወራት ፡ ተከፍለው ፤ በሦስት ፡ መቶ፡ ስድሳ ፡ አምስት ፡ ቀናት ፡ ተቀምረው ፡ ጠባያቸውን ፡ ሳይለቁ ፤ ይፈራረቃሉ ። የሰው ልጆች ፡ የታዩት ፡ ሲጠፉ ፡ ያልታዩት ፡ ቢተኩም ፤ ጠባያቸው ፡ ተለዋዋጭ ፡ በመሆኑ ፡ የዘመናት ፡ ታሪክ ፡ እንደመምጣታቸው ፡ እየተቀበለ ፡ ይመለከታቸዋል ፡ እያልኩ ፡ ከአሳቤ ፡ ጋር ፡ ስነጋገር ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ሆነ ፤ ፀሐይም ፡ ነቃች ፤ እንቅልፍ ፡አጥቼ፡ ማደሬን ፡ ገለጥኩላት ።

ለምን ፡ ፍቅሬ ፡ እንቅልፍ ፡ አጣህ ፤ እስከዚህ ፡ እንቅልፍ ፡ የሚያሳጣ ምን ፡ ነገር ፡ ቢያገኝህ ፡ ነው ፡ ብላ ፡ ብትጠይቀኝ ፤ እያንዳንዱ ፡ ራሱን፡ በራሱ ፡ ካላታለለ ፤ የሚታሰብ ፡ መች ፡ ይጠፋል ።

ይህን ፡ ስል ፡ ካንቺ ፡ ጋር ፡ ባለኝ ፡ ኑሮ ፡ የራሴን ፡ ደስታ ፡ ረስቼ፡ በአካባቢዬ ፡ ያለውና ፡ የማየው ፡ በሐሳቤ ፡ ሲመጣ ፤ በሐሳብ ፡ ሰመመን ፡ አካሌ ፡ ይዝላል ፤ መናገር ፡ ያቅተኛል ። መተንፈስ ፡ ይጨንቀኛል ። ሐሳብ ፡ ውስጥ ፡ ውስጡን ፡ እየበላ ፡ ስለቦረቦረኝ ፡ ውስጤ ፡ ተከፍቶ ፡ ቢታይ ፤ ምንም ፡ የቀረኝ ፡ የለም ፤ ሁሉም ፡ ተበላልቷል ፡ አልኳት ።

እንዴ ፡ አስተሳሰብህ ፡ ሁሉ ፡ ወዴት ፡ ሄደ ። ወደአላሰብኩትና፡ ወደ ፡ ማልጠብቀው ፡ አቅጣጫ ፡ ሄደ ፤ ስትል፡ ሥጋቷን፡ ገለጠችልኝ ።

የለም ፤ ከተነጋገርን ፡ እውነቱን ፡ እንነጋገር ፤ እስከመቼ ፡ ዋሽተን ፤ ወይም ፡ ራሳችንን ፡ አታልለን ፡ እንኖራለን ። ሸበት ፡ አውጥተናል ። ቀንድ ፡ እስከናወጣ ፡ እንጠብቅ ፡ ማለትሽ ፡ ነው ። ዕድሜያችንም ፡ ለሰው ፡ ከተወሰነው ፡ ዕድሜ ፡ ከአጋማሹ ፡ አልፍዋል ። በዚህ፡ ዓለም ፡ ስንኖር ፡ ለውድ ፡ ሀገራችን ፡ ምን ፡ እንደሠራን ፡ ብንጠየቅ ፡ ምን ፡ እንመልሳለን ።

ገለጣው ፤ ከማንም ፡ ሳይመጣ ፡ ከራሳችን ፡ መጥቶ ፡ ሁሉንም ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ብንነጋገር ፡ ለበሽታው ፡ መድኃኒት ፡ ልናገኝ ፡ እንችላለን ። ይህን ፡ የምናስብ ፡ ከሆነ ፤ የያንዳንዳችን ፡ ደስታ ፡ ስለብዙዎች፡ መለወጥ ፡ እንዳለበት ፡ አምነን ፤ ከሚያስፈልገን ፡ በላይ ፡ የተንዛዛው፤ ለሌሎች ፡ እንዲደርስ ፡ አሳልፈን ፡ እንስጥ ።

እስቲ ፡ አስተሳሰባችን ፡ ከከተማው ፡ ወጣ ፡ ይበል ፤ በቍጥር ፡ በዛ ፡ ብለው ፡ የሚገኙትን ፡ እስቲ ፡ እናስባቸው ። እንዴት ፡ ነው ፡ አኗኗራቸው ። ከተማ ፡ የሚያገኘውን ፡ ቢያገኙ ፡ አይወዱም ፤ ከተሜን ፡ መምሰል ፡ አይችሉም ። ታዲያ ፡ እንደዚህ ፡ እናያቸዋለን ?

የባላገሩንና ፡ የከተማውን ፡ ሰው ፡ ኑሮ ፡ በቅን ፡ አስተያየት ፡ የተመለከተ ፡ ደራሲ ፡ «ጠንቀኛው ፡ መልከኛ» ፡ በሚል ፡ ርእስ ፡ ከደረሰው ፡ መጽሐፍ ፡ የሚከተለውን ፡ እነበብኩላት ።

«ወላጆቹ፡ ርስቱን ፡ ከወዴት ፡ እንዳገኙት ፤ እንዴት፡ እንደመጣ፡ የማያውቅ ፡ በውርስ ፡ አገኘሁ ፡ የሚል ፤ የከተሜ ፡ አውደልዳይ ፡ ነበር፤ አዝመራ ፡ በተሰበሰበበት ፡ ወቅት ፡ ሥራ ፡ የሌለው ፡ የከተሜ ፡ አውደልዳይ ፤ ለማስወቃት ፡ ርስቱ ፡ ወደሚገኝበት ፡ ሄደ ።

ከተሜ ፡ ወደባላገር ፡ ሲሄድ ፡ በባላገር ፡ ለሚኖሩ ፡ ሊሰጥ ፤ ወይም ሊወስድ ፡ የሚገባውን ፡ ሳይዝ ፤ እጅና ፡ እግሩን ፡ ይዞ ፡ ሄደ ። ካራሾቹ፡ የተሻለ ፡ አኗኗር ፡ ባለው ፡ ቤት ፡ ማረፊያውን፡ አስጐዝጉዞ ፡ ተቀመጠ፡ ልዩ ፡ አክብሮት ፡ በመስጠት ፡ መኝታቸውን ፡ ለቀቁለት ። ከሌሎቹ ፡ መስተንግዶ ፡ እየመጣ ፡ ተሞሸረ ።

ውሎ ፡ ከማደር ፤ ፈቃዱ ፡ ቢነግግበት ፤ መኝታውን ፡ በማንጠፍ ምግቡን ፡ በማቅረብ ፡ በምታገለግለው ፡ በቤቱ ፡ አባወራ ፡ ሚስት ፡ ላይ ፡ ፈቃዱን ፡ ለመፈጸም ፡ ከጀለ ። ሁለትና ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ያህል ፤ የቤቱ ፡ ባለቤት ፡ ከቤቱ ፡ የሚለይበትን ፡ ሰበብ ፡ ፈለገ ። ዘዴው ፡ ተገኘና ፤ ረስቶት ፡ የመጣውን፡ ዕቃ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ሄዶ፡ እንዲያመጣለት፡ ላከው ።

በመልካም ፡ ፈቃድና ፡ በቀና ፡ አስተያየት ፡ እሺ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ሲሄድ ፤ ባለቤቱን ፡ በፍቅር ፡ አሸንፋት ። የቤቱ ፡ አባወራ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ በከተማ ፡ ሰንብቶ ፡ በአራተኛው ፡ ቀን፡ ወደቤቱ፡ መጣ፤



9*

የከተሜ ፡ አውደልዳይ ፤ ፍቅር ፡ ስለያዘው ፤ እንደገና ፡ ወደከተማ ፡ መልሶ ፡ ሊልከው ፡ ወደደ ። የዋሁ ፡ ገበሬ ፡ ምንም ፡ ሳይጠረጥር ፡ እሽ ብሎ ፡ ሄደ ። በከተማ ፡ የሚቆይበት ፡ ሌላ ፡ ሰበብ ፡ ባለመኖሩ ፤ በሁለተኛው ፡ ቀን ፡ ተመለሰ ። ስንኳን ፡ የከተሜው ፡ አውደልዳይ ፤ የልጆቹ እናትና ፡ ብዙ ፡ ዓመታት ፡ አብራው ፡ የኖረች ፡ ሚስቱ ፡ ቶሎ ፡ መመለሱን ፡ አልወደደችም ። ሆኖም ፡ የዋሁ ፡ ገበሬ ፤ በውጪ ፡ ሥራውን፡ ሲከታተል ፤ የከተሜ ፡ አውደልዳይ ፡ ከቤት ፡ አልወጣ ፡ ብሎ ፡ ጉዝጉዝ ፡ ቁጭ ፡ አለ ።

ከሰው ፡ ተደብቆ ፡ የሚሠራ ፡ ሥራ ፤ ዕድሜው ፡ አጭር ፡ ስለሆነ፤ የከተሜ ፡ አውደልዳይ ፤ ከጢሰኛው ፡ ሚስት ፡ ጋር ፡ የሚሠራውን ፡ ሥራ ፡ የጢሰኛው ፡ የመጀመሪያ ፡ ልጁ ፡ በአጋጣሚ ፡ ዐየ ። ልጁ ፡ ብልህ ፡ ኖሮ ፤ ያየውን ፡ ሳያወራ ፤ እንደገና ፡ ሲከታተል ፡ በሁለቱ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ በትክክል ፡ ዐወቀ ።

ለአባቱ ፡ ነገረው ። አባቱ ፡ ይህን ፡ ከሰማ ፡ በኋላ ፤ ለከተሜ ፡ አውደልዳይ ፡ ይሰጠው ፡ የነበረውን ፡ አክብሮት ፡ ነፈገው ። ከአባቱም ፡ ልጁ ፡ የባሰ ፡ ሆኖ ፡ በዓይኖቹ ፡ እየገረመመ ፡ ጥላቻውን ፡ አሳየው ። ጮሌው ፡ የከተማ ፡ አውደልዳይ ፡ ሥራው ፡ እንደታወቀ ፡ ገባውና ፤ ሳልዋረድ ፡ ላምልጥ ፡ ብሎ ፤ አዝመራውን ፡ ተቈጣጥሮ ፡ በወግ፡ ሳይካፈል ፡ ወደቤቱ ፡ ተመለሰ ።

«የወደደና፡ ያበደ፡ አንድ ፡ ነው»፡ እንደተባለው፤ የከተሜው፡አውደልዳይ ፤ የጢሰኛው ፡ ሚስት ፡ ፍቅር ፡ ከፊቱ ፡ እየተደቀነ ፡ ትዝታዋ፡ ሰላም ፡ ስለነሣው ፤ ተመልሶ ፡ መሄድ ፡ ሲፈልግ ፤ የጢሰኛውንና ፡ የልጁን ፡ ዓይን ፡ ማየት ፡ ፈራ ።

ራሱን ፡ በራሱ ፡ ሲያነጋግር ፤ «ደፋርና ፡ ጢስ ፡ መውጫ ፡ አያጣም» ፡ እንደተባለው ፡ በድፍረት ፡ ብሄድ ፤ ያ ፡ ሰይጣን ፡ ልጅ ፡ አባቱን ፡ ገፋፍቶ ፡ ይደበድቡኝ ፡ ይሆን ? ሴትዮዋ ፡ ወዳኛለች ። ከመውደድዋ ፡ የተነሣ ፡ እኔን ፡ አሳልፋ ፡ ከምትሰጥ ፤ ስለኔ ፡ ባሏንና ፡ ልጁዋን ፡ አሳልፋ ፡ ትሰጥ ፡ ይሆናል ። ታዲያ ፡ የርስዋ ፡ አስተሳሰብ ፡ ይህ፡ ከሆነ ፤ ምን ፡ ያስፈራኛል ። እነርሱ ፡ ወደሥራ ፡ በሄዱበት ፡ ጊዜ ፡ ሹልክ ፡ ብዬ ፡ ብገባና ፤ በሚመጡበት ፡ ጊዜ ፡ ከሴት ፡ ብልሀት ፡ አይጠፋምና ፡ ልትደብቀኝ ፡ ትችላለች ። በዚሁ ፡ ልሞክር ፡ ብሎ ፡ እንደወሰነ ፡ እንቅልፍ ፡ ሽልብ ፡ አደረገው ።



ፍቅር ፡ አስገድዶት ፡ ለመሄድ ፡ ይቁረጥ ፡ እንጂ ፤ በሐሳቡ ፡ ውስጥ ፡ ፍርሐት ፡ በመውጣትና ፡ በመውረድ ፤ ያስጨንቀው ፡ ስለነበር ፤ የቀን ፡ ጭንቁ ፡ ሕልም ፡ ሆኖ ፤ በዚያች ፡ በእንቅላፋባቸው ፡ ደቂቃዎች ፤ ማን ፡ እንዳሠረው ፡ ሳያውቅ ፡ እጆቹ ፡ በሰንሰለት ፡ ታሥረው፡ ምን ፡ ባጠፋሁ ፡ ታሠርሁ ፡ እያለ ፡ ብቻውን ፡ ሲናገር ፤ ቀጥቃጮቹ ፡ እንደምድር ፡ አሸዋ ፡ የበዛ ፡ ጥቁረታቸው ፡ አስፈሪ፡ የመልክ ፡ አወራረዳቸውና ፡ ቅርፃ ቸው ፡ ከሰው ፡ ፍጥረት ፡ የተለየ፡ ከበው ፤ የሠራኸው፡ ሥራ ፡ ከግንባርህ ፡ ላይ ፡ ተጽፎ ፡ እነሆ ፡ ይነበባል ። በጉልህ ፡ ፊደል ፡ በግንባርህ ፡ ላይ ፡ የተጻፈውን ፡ ቀና ፡ ብለህ ፡ ለማንበብ ፡ ባለመቻልህ፡ በምድራዊ ፡ ዓለም ፡ የሠራኻቸው ፡ ሥራዎች ፡ ምንና ፡ ምን፡ እንደሆኑ፡ አላወቅኻቸውም ። በውነቱ ፡ ብታውቃቸው ፡ ወይም ፡ በጉልህ ፡ ፊደል ፡ ግንባርህ ፡ ላይ ፡ የተጻፈውን ፡ ቀና ፡ ብለህ ፡ ብታነብ ፤ በራስህ፡ ላይ ፡ ራስህ ፡ ትፈርድ ፡ ነበር ።

በአንተ ፡ ምክንያት ፡ የስንት ፡ ሰዎች ፡ ቤት ፡ ተፈታ ? በአንተ ፡ ምክንያት ፡ የስንት ፡ ሰዎች ፡ ሕይወት ፡ አለፈ ? በአንተ ፡ ምክንያት ፡ ስንት ፡ ሰዎች ፡ ከማዕረጋቸውና ፡ ከብክራቸው ፡ ተዋረዱ ? በአንተ ፡ ምክንያት ፡ ስንት ፡ ሰዎች ፡ ከሥራቸውና ፡ ከንብረታቸው ፡ ተፈናቀለው ፤ ልጆቻቸው ፡ ከችግር ፡ ላይ ፡ ወድቀው ፡ የዕለት ፡ ምግብና ፡ ልብስ ፡ አጡ ፤ ለስንት ፡ ሰዎች ፡ ዕድል ፡ የብረት ፡ መጋረጃ፡ ሆንክ ? ስንቱን ፡ ዘርዝረን ፡ እንንገርህ ። ቀና ፡ ብለህ ፡ ባታየው ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ብታየውማ ፡ በሕይወትህ ፡ ዘመን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ሆነህ፡ የሠራኸው፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ በግንባርህ ፡ ላይ ፡ ተጽፎ ፡ ይነበባል ።

ካንተ ፡ መፈጠር ፡ በእናታቸው ፡ ማሕፀን ፡ እንዳሉ፡ ወየ፡ ሆነው ፡ የቀሩት ፡ ይመረጣሉ ። በል ፡ ሥራህን ፡ ዘርዝረን ፡ ከነገርንህ ፤ ለዘለዓለማዊ ፡ መኖሪያ ፡ የተመደበልህ ፡ ሥፍራ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ተቀመጥ ፡ ብለውት ፡ እንደታሠረ ፡ ጥለውት ፡ ሄዱ ። ቀና ፡ ቢል ፡ ታስሮ ፡ ብቻውን፡ ከመቀመጡ ፡ በቀር ፤ በብዛት ፡ ከበውት ፡ የነበሩት ፡ እጅግ ፡ አስፈሪዎች ፡ የሉም ። በነርሱ ፡ ላይ ፡ ይታይ ፡ የነበረው ፡ አሠቃቂና፡አስፈሪ፡ አካል ፡ ከፊቱ ፡ ሲወገድ ፤ ያለበት ፡ ሥፍራ ፡ ሁኔታው ፡ ተለውጦ ፤ አስፈሪና ፡ አስጨናቂ ፡ ሆኖ ፡ አገኘው ። ምን ፡ ጥለውብኝ ፡ ሄዱ ፡ እያለ ፡ ሲጨነቅ ፤ ቀደም ፡ ብለው ፡ ከበውት ፡ ከነበሩት ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆኑ ፡ ሌሎች ፤ ያንተ ፡ የዘለዓለም ፡ ጓደኞች ፡ ስለሆን፡ ከዛሬ፡ ጀምሮ ፡ አንተና፡ እኛ ፡ ሳንለያይ ፡ አብረን ፡ እንኖራለን ።

ታስታውስ ፣ እንደሆን ፤ በዚያች ፣ ምድራዊ ፣ ዓለም ፣ አንዱን ፣ ከአንዱ ፣ እንድታማታ ፣ የምናደፋፍርህና ፣ የምናስጨክንህ ፣ እኛ ፣ ስለሆን ፤ በቀን ፣ ቀርቶ ፣ በደቂቃ ፣ ስንኳ ፣ የሠራኸቸውን ፣ ሁሉ ፣ በሕይወት ፣ ታሪክህ ፣ መጽሐፍ ፣ ላይ ፣ እንመዘግብ ፣ ነበር ። እነሆ ፣ የሕይወት ፣ ታሪክ ፣ የሚመዘገብበት ፣ ትልቁ ፣ መዝገብ ፣ ከመጀመሪያው ፣ ገጽ ፣ እስከመጨረሻው ፣ ገጽ ፣ ድረስ ፤ በእኛ ፣ የእጅ ፣ ጽሕፈት ፣ ተጽፎ ፤ እያነበብንልህ ፣ ከኛ ፣ ጋር ፣ ለዘለዓለም ፣ እንድትኖር ፣ ስትመጣ ፣ የምንቀበልህ ፣ በታላቅ ፣ ደስታ ፣ ነው ፤ ብሎት ፣ ከፊቱ ፣ ሲጠፉ ፣ ከእንቅልፉ ፣ ነቃና ፤ « እክህደከ ፣ ጸርየ ፣ ሰይጣን » ምንድነው ፤ ሕልም ፣ ነው ፣ ቅዠት ፤ ምንድነው ፣ ሕልምነው ፣ ቅዠት ? እያለ ፣ በድንጋጤ ፣ ከተናገረ ፣ በኋላ « አሁንም ፣ እክህደከ ፣ ጸርየ ፣ ሰይጣን » ብሎ ፣ ተነሣ ።

ሆኖም ፣ በጣም ፣ ስለደነገጠና ፤ ፍርሐት ፣ በሰውነቱ ፣ ውስጥ ፣ ስለገባ ፣ ልቡ ፣ በኃይል ፣ እየመታ ፤ ወባ ፣ እንደያዘው ፣ ተንቀጠቀጠ ። ያየው ፣ ሁሉ ፣ ከፊቱ ፣ እየተደቀነ ፣ አስጨነቀው ። ምን ፣ ላድርግ ፤ ይህ ፣ ነገር ፣ ሕልም ፣ ነው ፣ ወይስ ፣ ቅዠት ፣ ነው ፣ በማንኛው ፣ ልውሰደው ፣ ፍችውስ ፣ ምንድነው ። ማወቅ ፣ አለብኝ ፣ አለና ፣ ሕልም ፣ ፈች ፣ ሲጠያየቅ ፣ በግብር ፣ ከሚመስሉት ፣ አንዱን ፣ ጓደኛውን ፣ በቅርብ ፣ አገኘና ወንድሜ ፣ ሳስታውሰው ፣ የሚያስቀቅኝ ፣ ሕልም ፣ አልለው ፣ ቅዠት ፣ ሲያውቃየኝ ፣ አደረ ። ፍችውን ፣ ለማወቅ ፣ ስለምፈልግ ፤ ሕልም ፣ ፈች ፣ የምታውቀው ፣ ወይም ፣ የሰማኸው ፣ ቢኖር ፣ ንገረኝ ፣ አለው።

እዬዬ ፤ ሰው ወደፊት ፣ ይሄዳል ፣ እንጂ ፣ እንዴት ፣ ወደኋላ ፣ ይመለሳል ። ምኑን ፣ ነው ፣ እባክህን ፣ ሕልም ፣ የምትለው። ቅዠት ፣ ነው ፣ ብለህ ፣ ብትተወው ፣ የሚቀረውን ፣ ቁም ፣ ነገር ፣ ብለህ ፣ ትይዘው ፣ ብሎ፣ መለሰለት ።

ወንድሜ ፤ « ያልተያዘ ፣ ግልግል ፣ ያውቃል ፣ » እየተባለ ፣ የሚተረተውን ፣ ታውቃለህ ፣ አታውቅም ፤ ያየሁትን ፣ ሳስታውሰው ፤ መላ ፣ ሰውነቴ ይጨነቃል ፣ ከፊቴም፣ አልጠፋ ፣ አለ ። አንተ ፣ እንዳልከው ፣ « ሕልም ፣ እልም ፣ » ብዬ ፣ ልንቀው ፣ ስፈልግ ፤ ያየሁት ፣ ከፊቴ ፣ መጥቶ ፣ ድቅን ፣ ይልና ፣ ያስታውሰኛል ። ከዚህ ፣ የተነሣ ፣ አሳሰበኝና ፤ በሕልም ፣ ፈች ፣ ፍችውን ፣ ላውቅ ፣ ወደድሁ ፤ ብሎ ፣ መልስ ፣ ሰጠው ።

ጭንቀትም፣ ሆነ ፣ ፍርሐት፣ በሰው፣ ላይ ፣ የሚመጣውን፣ በማሰብ፣ ነው ፤ ባታስብ ፣ ይህ ፣ ሁሉ ፣ አይደርስብህም ፣ነበር ። ይሁንና ፣ ሕልም፣ ፈቺ ፣ ስሙን ፣ ከነሞያው ፣ ይዘዋል ፣ እየተባሉ ፣ የሚነገርላቸው ፣ አቶ ፣



ዮሴፍ ፣ በአቅራቢያችን ፣ አሉ ፣ ይባላል ፤ ሒደህ ፣ ጠይቃቸው ፣ አለው።

ምስጋናውን ፣ አቅርቦ ፣ ሄደና ፤ ተጠያይቆ ፣ ከቤታቸው ፣ ደረሰ ፣ ሊነግርለት ፣ የገባው ፣ ልጅ ፣ እስኪመለስ ፣ ቸኩሎ፣ በር ፣ በሩን ፣ እያየ ፣ ተቅበጠበጠ ። ሆኖም ፣ ግባ ፣ ተባለና ፣ ገባ ። አቶ ፣ ዮሴፍ ፣ ለዓይን ፣ የሚከብዱ ፤ የደስ ፣ ደስ ፣ ያላቸው ፣ አረጋዊ ፣ በመሆናቸው ፤ ሲያያቸው፣ ደንገጥ ፣ አለና ፣ ቆመ ። ተቀመጥ ፣ ብለው ፣ ቢጋብዙትም ፣ ለመቀመጥ፣ አልደፍር ፣ አለ ።

ሳይቀመጥ ፣ የሄደበትን ፣ ለመናገር ፣ ሲጀምር ፤ አቤቱታ ፣ የምሰማ የከፍሉ ፣ ገኘር ፣ አይደለሁም ። የምረዳህ ፣ ካለ ፣ ተቀምጠህ ፣ ንገረኝ ፣ አሉትና ፣ ተቀምጦ ፣ ንግግሩን ፣ ቀጠለ ።

በአንዱ ፣ ውስጣዊ ፣ ሰውነት ፣ ውስጥ ፣ ያለን ፣ ችግር ፣ ክብደቱን ፣ ወይም ፣ ጭንቀቱን ፣ ለሁለተኛ ፣ ሰው ፣ አሳልፎ ፣ የሚያዋየው ፣ የተቀነሰለት ፣ እየመሰለው ፣ ነው ። የኔ ፣ ችግር ፣ ግን ፤ እኔን ፣ ለመሰለ፣ በሺህ፣ ለሚቈጠር ፣ ባወራውም ፤ ከሰውነቴ ፣ ውስጥ፣ ስለማይወጣ ፣ ፍችውን፣ የሚነግረኝ ፣ ስፈልግ ፣ ከርስዎ ፣ ደረስኩ ።

ከዕለታት ፣ አንድ ፣ ቀን ፣ ለደቂቃዎች ፣ በእንቅልፍ ፣ ውስጥ ፣ ባለሁበት ፣ ወቅት ፤ ሕልም ፣ አለምኩ ፣ ብሎ ፣ ቀደም ፣ ብሎ ፣ የተነገረውን ፣ ነገራቸው ፤ እንደዚህ ፣ ያለው ፣ ሕልም ፣ ነው ፣ ወይስ ፣ ቅዠት ፣ ነው ? በኔ ፣ ግምት ፣ ቅዠት ፣ እንጂ ፣ ሕልም ፣ ነው ፣ አልልም ፣ ይሁንና ፣ ፍችው ፣ ስላልገባኝ ፣ ፍችውን ፣ እንዲነገሩልኝ፣ መጣሁ ፣ አላቸው ።

አረጋዊው ፣ በትካዜ ፣ ተውጠው ፤ ዓይን ፣ ዓይኑን፣ ተመለከቱት። በዚህን ፣ ጊዜ ፣ የከተሜ ፣ አውደልዳይ፣ የበለጠ፣ ደነገጠ። እንደደነገጠ፣ አረጋዊው ፣ ባወቁ ፣ ጊዜ ፤ ልጄ ፣ ያየኸው ፣ እውነተኛ ፣ ሕልም፣ እንጂ፣ ቅዠት ፣ አለመሆኑን ፣ ዕወቀው ፣ ሰው ፣ ልቡ ፣ እያወቀ ፣ ራሱን ፣ ለማታለል ፣ እንዳላወቀ ፣ ሆኖ ፣ መናገሩ ፣ ልማድ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ እውነተኛ፣ ሕልም ፣ ትርጉም ፣ ወይም ፣ ፍች ፣ አያሻውም ፤ ራሱ ፣ በራሱ፣ ይፈታል።

እረ ፣ ለመሆኑ ፣ በምን ፣ ሥራ ፣ ላይ ፣ ነበርክ ? ብለው ፣ ጠየቁት ። ቅውልዴ ፣ ከትልቅ ፣ ቤተሰብ ፣ ሆኖ ፣ ወገኖቼ ፣ ብዙ ፣ ናቸው ። ወላጆቼ ፣ ሞተዋል ። ከትልቅ ፣ ቤት ፣ ሰብ ፣ በመገኘቴ ፣ በከፍተኛ ፣ የአስተዳደር ፣ ሥራ ፣ ላይ ፣ ነበርሁ ። በጠባይ ፣ ደካማነት ፤ ከዚያ ፣ ክብር ፣ ካለው ፣ ሥራ ፣ ወጥቼ ፣ ከወላጆች ፣ በውርስ ፣ ባገኘሁት ፣ ልዩ ፣ ልዩ ፣ ገቢ ፣ እተዳደራለሁ ፣ አላቸው ።

በከፍተኛ ፡ ያስተዳደር ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የነበርከው ፡ በጠባይህና ፡ በዕውቀትህ ፤ ለሕዝብ ፡ አስተዳደር ፡ ትጠቅማለህ ፤ ተብለህ ፡ ነው ፡ የተመረጥከው ፤ ወይስ ፡ የእነገሌ ፡ ቤተሰብ ፡ ነው ፡ በመባል ፡ ብቻ ፡ ተመርጠህ ፡ ነው ፡ በከፍተኛ፡ የሕዝብ ፡ አስተዳደር ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የነበርከ ፡ ብለው ፡ እንደገና ፡ ጠየቁት ፡ አረጋዊው ።

ጌታዬ ፡ ጠባዬም ፡ ሆነ ፡ ዕውቀቴ ፡ ለዚህ ፡ ይሆናል ፡ በማለት ፡ ሳይሆን ፤ ትውልዴ ፡ እንደምድር ፡ አሸዋ ፡ በመብዛቱ ፤ ያስመረጠኝ ፡ ይህ ፡ ብቻ ፡ ነው ። መራጮች ፡ በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ መርጠው ፤ ከፍተኛ ፡ የአስተዳደር ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ቢያውሉኝም ፤ ከወላጆች ፡ በውርስ ፡ ያገኘሁትን ፡ ንብረት ፤ ካወቅሁበት ፡ እንኳን ፡ ለኔ ፤ ለሌላም ፡ የሚተርፍ ፡ በመሆኑ ፡ ምን ፡ አደከመኝ ፡ ብዬ ፡ ሥራውን ፡ ተውኩት ። ልቤን ፡ እያስጨነቀ ፡ ፀጥታ ፡ የነሳኝ ፡ ሕልም ፡ የማልለው ፡ ወይም ፡ ቅዠት ፤ ያስጨነቀኝ ፡ ፍችውን ፡ እንዲነግሩኝ ፡ ብዙ ፡ ማይል ፡ አቋርጬ ፡ መጣሁ ፡ ሕልም ፡ እንጂ ፡ ቅዠት ፡ አለመሆኑን ፡ ሲገልጹልኝ ፡ ፍችውን ፡ አላብራሩልኝ ፡ አላቸው ፡ የከተሚ ፡ አውደልዳይ ።

ልጄ ፡ አሉት ፡ አረጋዊው ። ሕልምህ ፡ ፍች ፡ የማያስፈልገው ፡ ራሱ ፡ የተፈታ ፡ ነው ። በምን ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንደነበርክ፡ የጠየቅሁና፡ ሥልጣን ፡ ላይ ፡ በነበርክበት ፡ ወቅት ፤ «ሰው ፡ ሆይ ፡ ሞኝ ፡ ተላሌ ፡» እንደተባለው ፡ የማያልፍ ፡ መስሎህ ፤ ሥልጣንህን ፡ መሣሪያ ፡ አድርገህ ፤ ምን ፡ ያህል ፡ በደልና ፡ ክፋት ፡ ብትሠራ፡ ይሆን፡ ስንኳን፡ ላየው ፡ ለሰማው ፡ አስፈሪ ፡ የሆነውን ፡ በሕልም ፡ ያሳየህ ፤ ወይም ፡ የነገረህ ፡ የሕልም ፡ ፈች ፡ እንዳትሻ ፡ እንደምድር ፡ አሸዋ ፡ የበዙ ፡ እጅግ ፡ አስፈሪ ፡ የሆኑት ፡ ነግረውሃል ። ይሁንና ፡ ለእግዚአብሔር፡ የሚሳነው ፡ ስለሌለ ፤ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እዘን ፡ ይቅር ፡ እንዲልህ ። ልብህን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሰጥተህ ፡ ካላዘንክ ፤ ወዮልህ ፡ የሁለት ፡ ዓለም ፡ ስደተኛ ፡ ሆንክ ።

አረጋዊው ፤ ንግግራቸውን ፡ ሳይጨርሱ ፡ ጌታዬ ፤ ምን ፡ ማለት ፡ ነው ፤ የሁለት ፡ ዓለም ፡ ስደተኛ ፡ መሆን ? ብሎ፡ ጠየቃቸው ፡ የከተሚ፡ አውደልዳይ ።

ልጄ ፡ ለምን ፡ ትቸኩላለህ ፡ «የቸኮለ ፡ አፍስሶ ፡ ለቀመ ፡ » የተባለውን ፡ አልሰማህምን ? የሁለት ፡ ዓለም ፡ ስደተኛ ፡ የሆንከው ፤ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ በልደት ፡ ከተገኘህ ፡ አሁን ፡ ድረስ ፡ ሥጋዊ ፡ ፈቃድህን ፡ በማሳደድ ፡ ያገኘሃቸው ፡ ደስታዎች ፡ ብዙዎች፡ ይሆኑ ፡ ይሆናል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የሰሞኑ ፡ ጭንቀትህ ፤ ያንን ፡ ያሳልፍከውን ፡ እንዳልነበረ፡ አድርጐ ፡ ከፊትህ ፡ አላጠፋውም ። ደስታ ፡ ዘለቄታ፡ ሲኖረው፡ ነው ፡ እንጂ ፤ አሁን ፡ ታይቶ ፡ አሁን ፡ ከጠፋ ፡ ምን ፡ ደስታ ፡ ይባላል።

የሰሞኑ ፡ ጭንቀት ፡ ብቻ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ አግኝተኸው ፡ የነበረውን ፡ ደስታ ፡ ሁሉ ፡ እንዳልነበር ፡ እንዳደረገው ፡ ልቦናህ ፡ ያውቃል ። ስለዚህ ፡ ነው ፤ ጠለቅ ፡ አድርገው ፡ ያስተዋሉ ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ደስታ ፡ አልማርካቸው ፡ ብሎ ፡ ሕይወታቸውን ፤ ለእግዚአብሔር፡ መንግሥት፡ ለውድ ፡ ሀገራቸውና፡ ለወገናቸው ፡ ደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ እያደረጉ ፤ የሥራ ፡ ታሪክ ፡ አቆይተው ፤ ከሕይወታቸው ፡ በኋላ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ የሚጠብቃቸውን ፡ የክብር ፡ አክሊል ፡ የሚወርሱት ።

ሕልምህ ፡ ዐውቆ ፡ የተፈታ ፡ ፈች ፡ የማያስፈልገው ፡ እውነተኛ ፡ ሕልም ፡ መሆኑን ፡ ቀደም ፡ አድርጌ ፡ ነግሬሃለሁ ። በዚህ፡ ዓለም ፡ የምትኖርባት ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ያጠረች ፡ ሆናለች ። ግን ፡ ሞት ፡ የፍጥረት ፡ ዓለም ፡ ግዴታ ፡ ስለሆነ ፤ አሁን ፡ ብትሞት ፤ መቶ ፡ ዓመት፡ ቆይተህም፡ ብትሞት ፤ ላንተ ፡ ያው ፡ ነው ። ፈንታህን ፡ ተወጣኸው። የፍጥረት ፡ ዓለም ፡ ግዴታ ፡ የሆነውን ፡ ሞት ፡ መሞት ፡ አያሳዝንም ። ዕረፍት ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፤ ሞት ፡ አይባልምና ፤

ልጄ ፡ ይህችን ፡ ዓለም ፡ አንተ ፡ ብትወዳት ፡ ርስዋ፡ ከድታሃለች። ጠባይዋ ፡ ደግሞ ፡ ወረተኛ ፡ ስለሆነ ፤ አንተን ፡ ከድታ ፡ ከሌላ ፡ ጋር ፡ ትዘፍናለች ። ልጄ ፤ ብዙዎች ፡ ሆነው ፡ ራስ ፡ ራስህን ፡ እየደበደቡ ፡ ስትነቃ ፡ እጆችህ ፡ በሰንሰለት ፡ ታሥረው ፤ ከበው ፡ ያንጋግሩህ፡ የነበሩት ፡ የሰይጣን ፡ ሠራዊቶች ፡ ናቸው ፡ ብለው ፡ ነገሩት ።

ለደቂቃዎች ፡ ዝም፡ አለና ፡ ጭንቀቴ ፡ የተቀነሰ፡ መስሎኝ፤ መጥቼ ፤ ጭንቀቴን ፡ በበለጠ ፡ የሚያባብስ ፡ መልስ ፡ አገኘሁ ። እንግዲህ ፡ ልሂድ ፡ ብሎ ፡ አረጋዊውን ፡ ተሰናብቶ ፡ ተመለሰ ።

በጉዞው ፡ ላይም ፡ እንዳለ ፡ ቅዠት ፡ ነው ፡ ያልኩትን ፤ አረጋዊው ፡ እውነተኛ ፡ ሕልም ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ፈቱት ፤ ሳይሳሳቱ ፡ አልቀሩም ። ይህ ፡ ቅዠት ፡ እንጂ ፡ ሕልም ፡ አይደለም ። ከኔ ፡ ቅዠት ፡ የአረጋዊው ፡ ቅዠት ፡ ይባስ ። ያም ፡ ሆነ ፡ ያ ፤ በወሬ ፡ መፈታት ፡ አይገባኝም ። ይህ ፡ እንደወሬ ፡ የሚቈጠር ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ በቁም ፡ ነገር ፡ አስ

ተሳሰብ ፣ የሚታሰብበት ፣ አይደለም ። ከአረጋዊ ፣ አነጋገር ፣ ይልቅ ፤ ያ ፣ ከልብ ፣ የሚያስብልኝ ፣ «ባልንጀራዬ ፤ ሕልም፣ እልም»፣ ብለህ ፣ ተወው ፤ ይህ ፣ ሕልም ፣ አይደለም ፣ ቅዠት ፣ ነው ፣ ብሎ ፣ ያለኝን ፣ ብከተል ፣ የተሻለ ፣ ሲሆን ፤ ይህን ፣ ያህል ፣ መንገድ ፣ ተወዝውዤ፣ ተስፋ፣ የሚያስቆርጥ ፣ ቃል ፣ የሰማሁት ፣ በኔ ፣ ስሕተት ፣ ነው ።

ሕልም ፣ የሚያልሙና ፤ በሕልማቸው ፣ እምነው ፣ የሚያሳምኑ ፣ በጥዋት ፣ በማታ ፣ በጸሎት ፣ ከእግዚአብሔር፣ ጋር፣ የሚነጋገሩ፣ ናቸው። እንዲህ ፣ ያለውን ፣ ምክሬው ፣ አላውቅም ። ታዲያ ፣ እንዴት ፣ ለኔ ፣ ይህን ፣ ግልጥ ፣ ያለ ፣ ሕልም ፣ ያሳየኛል ፣ ብዬ ፣ አመንኩ ። በእውነቱ፣ ተሳስቻለሁ ። አሁንም ፣ ይህን ፣ ከንቱ ፣ የሆነ ፣ አስተሳሰብ ፣ ከአዕምሮዬ ፣ ሳውጣውና ፤ የአሰብኩትን ፣ ልፈጽም ፣ አለ ።

ቆራጡ ፣ የከተሜ ፣ አውደልዳይ ፣ ርስቱ ፣ ወደሚገኝበት ፣ ሄደ ። ሁሉም ፣ ወደ ፣ ሥራ ፣ በተሰማሩበት ፣ ወቅት ፣ ደርሶ ፤ ወደ፣ ጢሰኛው፣ ቤት ፣ ጐራ ፣ ቢል ፣ በፍቅርዋ ፣ የጣለችውን ፣ የጢሰኛውን ፣ ሚስት ፣ ብቻዋን ፣ አገኛት ። ቀጠሮ ፣ የለንም ፤ ቀጠሮዋችን ፣ የጸድቃን፣ ቀጠሮ፣ ሆኖ ፤ ብቻሽን ፣ ስላገኘሁሽ ፣ ደስ ፣ አለኝ ፣ አላት ።

ርስዋ ፣ ግን ፣ ይህን ፣ ደስታ ፣ ነው ፣ አልልም ። ባለቤቴና ፣ ልጄ ፣ ተጣልተውኝ ፣ ከርመዋል ። ጭቅጭቁ ፣ በረድ ፣ ብሎ ፣ ሲረሳሳ፣ ሲል፣ ያንተ ፣ መምጣት ፣ ነገሩን ፣ እንደገና ፣ ያድሰዋል ። የምመክርህ፣ በቶሎ፣ ወደ፣ ቤትህ ፣ ብትመለስ ፣ ነው ፣ አለችው ።

ከሴት ፣ ብልሃት ፣ አይጠፋም ፣ እንደተባለው ፤ በብልሃትሽ ፣ ትደብቂኛለሽ ፣ ብዬ ፣ ነበር ፤ በፍቅርሽ ፣ ኮርቼ ፣ ነው ፣ የመጣሁ ። ግን ፣ በአሁኑ ፣ አነጋገርሽ ፣ የተለወጥሽ ፣ መሰለኝ ፣ ብሎ ፣ መልስ ፣ ሰጣት ።

እባክህን ፣ አንተ ፣ ለተናገርከውና ፣ እኔም ፣ ለምናገረው ፣ ስንመላለስ ፣ ባለቤቴ ፣ ቢመጣ ፤ ላንተም ፣ ሆነ ፣ ለኔ፣ ስለማይጠቅመን፣ ዘወር፣ በል ፣ አለችው ።

የከተሜ ፣ አውደልዳይ ፣ ተቆጣ ። እኩርፎ ፣ ወጣ ፣ አለና፣ ባለቤቱ፣ እስኪመጣ ፣ በአንድ ፣ ሠዋራ ፣ ሥፍራ ፣ ቆየ ። ባለቤቱ ፣ ሲገባ፣ ከውጭ፣ የመጣ ፣ መስሎ ፤ እንዴት ፣ ዋላችሁ ፣ ብሎ ፣ ከተፍ ፣ አለ ። በዚህን ፣ ጊዜ ፣ የባለቤቱ ፣ ሚስት ፣ ደነገጠች ። ባለቤቱ ፣ ግን ፣ እንደቀድሞው፣ ደንገጥ ፣ ብሎ ፣ ያደርግለት ፣ የነበረውን ፣ ትሕትናዊ ፣ አቀባበል፣ ቀንሶ፣ ተቀበለው ።



ወደዚያው ፣ ምሳ ፣ ቀረበና ፤ ይሉኝታ ፣ ቢሉ ፣ የከተሜ ፣ አውደልዳይ ፤ እጁን ፣ ወደ ፣ ማዕዱ ፣ ዘረጋ ። ያለምንም ፣ ንግግር ፣ ወይም ፣ ጨዋታ ፣ ምሳ ፣ ከበሉ ፣ በኋላ ፤ የከተሜን፣ አውደልዳይ፣ ለምን፣ ጉዳይ፣ እንደመጣና ፣ መቼ ፣ እንደሚመለስ ፣ ባለቤቱ ፣ ጠየቀው ። ሌላ ፣ ምክንያት ፣ ስለሌለው ፣ ከተሰበሰበው ፣ ከዘመኑ ፣ የሚደርሰውን ፣ እህል ፣ በገንዘብ ፣ ለውጦ ፣ ለመሔድ ፣ እንደመጣ ፣ ነገረው ።

ጢሰኛው ፣ እንኳን ፣ በቤቱ ፣ ሊቀመጥ ፤ በመንገድ ፣ ዓይኑን ፣ ማየት ፣ የማይፈልገው ፣ ሰው ፤ በቤቱ ፣ ስለተቀመጠ ፣ ደስ ፣ ሳይለው ፣ በይሉኝታ ፣ ብቻ ፣ ዝም ፣ አለ ። ወደማታ ፣ ጊዜ ፣ ልጆቹ ፣ ከውጭ ፣ ሲገቡ ፤ በተለይ ፣ ትልቁ ፣ ልጅ ፣ የከተማውን ፣ አውደልዳይ፣ ባየ ፣ ጊዜ፣ ተቆጣ ። ደሙ ፣ ፈላ ። እናቱንም ፣ አባቱንም ፣ ገላመጠ ። ምግብም ፣ ቢቀርብለት ፣ አልዋጠው ፣ አለ ። በቤቱ ፣ ውስጥ ፣ ፈታ ፣ ያለ፣ ጨዋታ፣ ሳይኖር ፣ አመሹ ። ለከተሜው ፣ አውደልዳይ ፣ ካሁን ፣ ቀደም ፣ ያድርበት ፣ የነበረው ፣ መኝታ ፣ ተነፍጎ ፣ በውጭ ፣ መኝታ ፣ ተዘጋጀለት ። በዚያው ፣ አደረ ። ወንዶቹ ፣ ወደ ፣ ሥራ ፣ ሲሄዱ ፣ የከተሜ ፣ አውደልዳይ ፣ ስለ ፣ ደከመኝ ፣ ዐረፍ ፣ ብዬ ፣ ልዋል ፣ ብሎ ፣ ተኛ ።

የከተሜ ፣ አውደልዳይ ፤ ያለርሱ ፣ ብልጥና ፣ ብልህ ፣ እንደሌለ ፣ ራሱን ፣ አታሎ ፤ አባወራው ፣ ወደ ፣ ሥራ፣ በሄዱበት፣ ሰዓት፣ የቤትዋን ፣ እመቤት፣ለማግኘት ፣ ሙከራውን ፣ ሲቀጥል፤ የቤትዋ ፣ እመቤት ፣ ባልዋና ፣ ትልቁ ፣ ልጅዋ ፣ በከተሜው ፣ አውደልዳይ ፣ ላይ ፣ ያላቸውን ፣ ጥላቻ ፣ የሚገልጹበትን ፣ ምክንያት ፣ እንደሚሹ ፣ ስለምታውቅ ፤ እባክህን ፣ አንተም ፣ ሕይወትህን ፣ ከምታጣ ፤ ለኔም ፣ ንብረት ፣ ጥፋት ፣ ከምትሆን ፣ ወደ ፣ ቤትህ ፣ ተመለስ ። ስንኳን ፣ ሰው ፣ እንስሳት ፣ የሚጠላቸውን ፣ ያውቃሉ ። ባለቤቴና ፣ ልጄ ፣ ከቶ ፣ ዓይንህን ፣ ማየት ፣ አልፈለጉም ፣ አለችው ።

የከተሜ ፣ አውደልዳይ ፣ ተስፋ ፣ ቆርጦ ፣ ወደአደረበት፣ ታዛ ፣ጐራ፣ ብሎ ፣ እንደ ፣ ተቀመጠ ፣ አባትና ፣ ልጅ ፣ መጡ ። በዚህን ፣ ጊዜ ፣ ደነገጠ ። ለትንሽ ፣ አመለጥኩ። ሳነጋግራት፣ ቢደርሱ፣ እንደ፣ እባብ ፣ ራሴን፣ ቀጥቅጠው ፣ ይገድሉኝ ፣ ነበር ፣ አለ ።

ድምፃቸውን ፣ ሲሰማ፣ ወጣ ። ሰላምታም፣ በሚገባ ፣ አልሰጡትም። እንዲያውም ፣ ብዙ ፣ ጊዜ ፣ የምታርፈው ፣ ከኔ ፣ ቤት ፣ ነው ።

እኔም ፡ ሆንኩ ፡ ሌሎቹ ፡ በመሬትህ ፡ ላይ ፡ በጢሰኝነት ፡ ሠፍረን ፡ እር ሰን ፡ እናካፍላለን ። በምትመጣበት ፡ ጊዜ ፡ ተቀባይነቱ ፡ የኔ ፡ ብቻ ፡ መሆን ፡ ስለሌለበት ፡ ሌሎቹ ፡ ይድረሳቸው ፡ አለው ።

የከተሜ ፡ አውደልዳይ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ሌሎች ፡ ሄዶ ፡ በዚያ ፡ ተጐዝጉዞለት ፡ ሆኖም ፡ ያስለመደውን፡ ቤት ፡ ለምን ፡ እንደተወ ፡ ሌሎች ፡ ማወቅ ፡ ፈልገው ፡ ቢጠያየቁ ፡ ለጊዜው ፡ ፍንጭ ፡ አጡ ። የከተሜ ፡ አውደልዳይ ፡ ከመገርመምና፡ ከመገልመጥ፡ ድኖ ፡ መሬቱ ፡ ያፈራውን ፡ በማስወቃት ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፤ ያች ፡ ያማገ ጣት ፡ የጢሰኛው ፡ ሚስት ፡ ፍቅር ፡ ልቡን ፡ ስለሰወረው ፤ ተደብቆ ፡ ወደ ፡ ቤትዋ ፡ ሔደ ። ባልዋና ፡ ልጅዋ፡ በዓይን፡ ቁራኛ፡ ይከታተሉት፡ ስለነበር ፤ ከነበረበት ፡ ፈልገው ፡ ሲያጡት ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ሄዱ ። እንደ ፡ ደረሱ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ከመግባታቸው ፡ በፊት ፡ በደፈጣ፡ ሆነው፡ ሲያዳምጡ ፤ የመላእክትንና ፡ የቅዱሳንን ፡ ስም ፡ እየጠራ፤ ሐሳብዋን ፡ አዳክሞ ፡ ለማቸነፍ ፡ ሲያወተውት ፤ ሴትዋ ፡ በጠንካራ ፡ መንፈስ ፡ ተቃ ውሞዋን ፡ ስትገልጥ ፡ ሰሙ ።

የከተሜ ፡ አውደልዳይ ፡ ሲወተውት ፤ ርስዋም ፡ ግትር ፡ በሆነ ፡ ሐሳብዋ ፡ ላይ ፡ ጸንታ ፡ መልስ ፡ ስትሰጥ ፤ በመካከል ፡ አባትና ፡ ልጅ፡ በደም ፡ ፍላት ፡ ተገፋፍተው ፡ ገብተው ፡ እንደደረሱ ፡ በዱላ ፡ ራስ፡ ራሱን ፡ እንደ ፡ እባብ ፡ ቀጠቀጡት ። ልቡን ፡ በሰበረው ፡ የፍቅር ፡ በሽታ ፡ መነሻ ፡ የከተሜው ፡ አውደልዳይ ፡ ሕይወቱን ፡ሠዋ ። ልጅና ፡ አባት ፡ ሬሳውን ፡ አውጥተው ፡ ከከብቶች ፡ ማደሪያ ፡ በረት ፡ ቀበሩት ።

ሄድኩ ፡ ሳይል ፡ በመጥፋቱ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ የሄደ ፡ መስሎዋቸው፡ ተጠያየቁ ። ትናንት ፡ ነበር ፡ አይተነዋል ። ዛሬ ፡ ወዴት ፡ እንደሄደ ፡ አላየነውም ፡ እየተባባሉ ፡ ተነጋገሩ ። የርሱ ፡ አመጣጡም ፡ ሆነ ፡ አካ ሄዱ ፡ አይታወቅም ። ይመጣል ፡ ሳንል ፡ መጥቶ ፡ እናየዋለን ። ይሄዳል፡ ሳንል ፡ መሄዱን ፡ እንሰማለን ። ይህ ፡ የተለመደ ፡ ሲሆን ፤ ስለመሄ ዱና ፡ ስለአለመሄዱ ፡ ምን ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ተገኝቶ ፡ ነው ፡ የተጠያየ ቃችሁት ፡ አላቸው ፡ ገዳይ ።

አይ ፡ በአጋጣሚ ፡ ተነጋገርን ፡ እንጂ ፤ በፈለገው ፡ ጊዜ ፡ የሚመ ጣና ፡ በፈለገው ፡ ጊዜ ፡ የሚሄድ ፡ ፈላጊና ፡ ጠያቂ ፡ ስለሌለው ፤ አወ



ዳደቁ ፡ ሳያምር ፡ የትም ፡ የት ፡ እንደሆነ ፡ ሳይታወቅ ፡ ይቀራል ። ያም፡ እዚያ ፡ ነው ፤ ያም ፡ እዚያ ፡ ነው ፡ ሲል ፤ የት ፡ እንዳለ ፡ ወይም ፡ የት ፡ እንደወደቀ ፡ ሳይታወቅ ፡ ይቀራል ፡ ብለው ፡ ተነጋገሩ ።

«ሥራ ፡ ለሠሪው ፤ እሾህ ፡ ለአጣሪው ፡ » እንደተባለው ፡ የአበው፡ አነጋገር ፤ ባልና ፡ ሚስት ፡ ከነልጆቻቸው ፡ ያፈሰሱት ፡ ደም፡ የሕሊና፡ ወቀሳና ፡ ፀፀት ፡ በአዕምሮዋቸው ፡ ላይ ፡ ተክሎ ፤ የመንፈስ ፡ ርጋታና፡ ፀጥታ ፡ ነሳቸው ። እንዲያውም ፡ ልጃቸው ፤ እንደ ፡ ቤት ፡ ክርስ ቲያን ፡ ተሳላሚ ፤ በጥዋት ፡ በማታ ፡ መቃብሩ ፡ ወደሚገኝበት፡ በረት፡ ጐራ ፡ እያለ ፡ በትካዜ ፡ መመልከት ፡ ልማድ ፡ አደረገ ። ሰውም ፡ ወደ ቤታቸው ፡ ሲመጣ ፤ ወይም ፡ በቤታቸው ፡ አጠገብ ፡ ሲተላለፍ ፤ እድ ራጐታችን ፡ ተሰማ ፡ እያሉ ፡ ሥጋቱ ፡ ሰላም ፡ ነሣቸው ።

የከተሜ ፡ አውደልዳይ ፡ መጥፋት ፡ በቤተሰቡና ፡ በግብረ ፡ አበ ሮቹ ፡ ማንንም ፡ አላስደነገጠም ። በየቡና ፡ ቤቱና ፡ በየመጠጥ ፡ ቤቱ ፡ ሲልከሰከስ ፡ አንዱ ፡ ማጅራቱን ፡ ብሎት ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ለጥቂት ፡ ቀናት ፡ የቡና ፡ መጠጫ ፡ ወሬ ፡ አድርገውት ፡ በመጨረሻ ፡ ተረሳ ።

ይሁንና ፡ በደም ፡ ፍላት ፡ ወይም ፡ በግል ፡ ጥቅም ፡ በተመሠረተ፡ ሐሳብ ፡ የተፈጸመ ፡ በደል ፤ ለጊዜው ፡ ቢያስደስትም ፡ ዘለቄታ ፡ የለ ውም ። የከተሜ ፡ አውደልዳይን ፡ የገደሉት ፡ ቤተሰቦች ፡ ሁለት፡ ዓመት፡ ያህል ፡ እየባነኑ ፡ የሰላምና ፡ የፀጥታ ፡ እንቅልፍ ፡ አጡ ።

ይልቁንም ፡ መቃብሩ ፡ በከብቶች ፡ በረት ፡ ውስጥ ፡ በመሆኑ ፡ ከብቶቻቸውን ፡ ባስገቡና ፡ ባስወጡ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፤ እየተሸማቀቁ ፡ ሰላ ማቸው ፡ ታወከ ። ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ ሀገሩን ፡ ለቀው ፡ ገና ፡ በመቅናት ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ አለ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ተሰደው ፡ ሄዱ ።

እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ከአያትና ፡ ከአባት ፤ ጀምሮ ፡ እስካሁን ፡ ከኖሩ በት ፤ ይልቁንም ፡ ተወልደው ፡ ካደጉበት ፡ ቀበሌ ፡ ተሰደው ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ የሄዱት፡ ለምን፡ ይሆን ? ፡ የሚለው ፡ መጠይቅ፤ እየተስፋፋ፤ ካንዱ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ እየተዛመተ ፡ ሄደ ።

ወሬ ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ ሳይቀር ፤ መጠየቁ ፡ ጠለቅ ፡ ወደ ፡ አለው ፡ ምርመራ ፡ ተራምዶ ፤ ጉዳዩ ፡ የሚመለከታቸውም ፡ ሆነ ፡ የማይመለከ ታቸው ፡ በነገሩ ፡ ተጠበቡበት ። በአካባቢው ፡ ነዋሪ ፡ የሆነው፡ ሕዝብ፡ በየምክንያቱ ፡ ሲገናኝ ፡ በአቶ ፡ ይታገድ ፡ መሰደድ ፡ መጠያየቁን ፡ እያ

ስፋፋ ፡ ሄደ ። አቶ ፡ ይታገድ ፡ በሚያውቀውና ፡ በማያውቀው ፡ በቅር ብና ፡ በሩቅ ፡ ባለው ፡ ሕዝብ ፡ አዕምሮ ፡ ተቀርጾ ፡ ሲወሳ ፤ የከተሜ ፡ አውደልዳይ ፡ ጠፍቶ ፡ መቅረትና ፡ መረሳት ፡ አብሮ ፡ ይወሳ ፡ ጀመር።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ የአደባባይ ፡ ሰው ፤ ይታገድ ፡ ይኖርበት ፡ የነበረው ፡ ቀበሌ ፡ ቢመረመር ፤ የተሰደደበት፡ ምሥጢር፡ ይታወቅ ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ እንደዘበት፡ ሐሳቡን ፡ ጣል ፡ አደረገና ፡ ብዙ ዎች ፤ ለካስ ፡ ይህም ፡ አለ ፤ እውነት ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ፡ ተባባሉ ።

ይህ ፡ እንደዘበት ፡ የተነገረ ፡ ቃል ፤ ካንዱ ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ እየተላ ለፈ ፡ ሲደርስ ፤ ከቀበሌው ፡ ሹም ፡ ጆሮ ፡ ደረሰ ። የቀበሌው ፡ ሹም ፡ ነገሩን ፡ በጥብቅ ፡ ተከታተለ ። የከተሜ ፡ አውደልዳይ ፡ እንደመጣና ፡ መጥቶ ፡ ወዴት ፡ ያርፍ ፡ እንደነበረ ፤ እንዴት ፡ መጥቶ ፡ እንዴት ፡ እንደሄደ ፤ ጠቅላላውን ፡ የነገሩን ፡ አካባቢ ፡ ካጠና ፡ በኋላ ፤ ለፀጥታ ፡ ሠራተኞች ፡ አስታወቀ ።

የፀጥታ ፡ ሠራተኞቹ ፡ እየተከታተሉ ፡ መረጃ ፡ ሰበሰቡ። ባገኙት፡ ፍንጭ ፡ አቶ ፡ ይታገድ ፡ የመንግሥት ፡ የሆነ ፡ ነፃ፡ መሬት ፡ በማልማት፡ ላይ ፡ መሆኑን ፡ በመረጃ ፡ ደረሱበት ።

የፀጥታ ፡ ሠራተኞች ፡ ለመሆናቸው ፡ ምንም ፡ መታወቂያ ፡ ሳይ ሰጡ ፡ አቶ ፡ ይታገድ ፡ በአለበት ፡ ሀገር ፡ እየተዘዋወሩ ፤ በፈሊጥ ፡ እን ጋገር ፡ ከአቶ ፡ ይታገድ ፡ ልጅ ፡ አንዳንድ ፡ ማስረጃ ፡ ማግኘት ፡ ቻሉ። ማናቸውንም ፡ በዝርዝር ፡ ለማወቅ ፤ ከአቶ ፡ ይታገድ ፡ ልጅ ፡ ጋር ፡ ያላ ቸውን ፡ ወዳጅነት ፡ በበለጠ ፡ አጠንከሩ ። የልጅ ፡ አዕምሮና፡ የልጅ፡ አስተሳሰብ ፡ ያው ፡ ልጅ ፡ ስለሆነ ፤ የከተሜው ፡ አውደልዳይ ፡ ምን ፡ እንዳደረገ ፤ ርሱ ፡ ከአባቱ ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ ምን ፡ እንዳደረጉት ፤ አንድ ፡ ቅንጣት ፡ ሳያስቀር ፡ ከመናገሩም፡በላይ ፤ የተቀበረበትን ፡ ልዩ ፡ ሥፍራ፡ በመለየት ፡ ነገራቸው ። ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሲናገር ፡ ድምፁን ፡ ቀረጹት ።

ከመካከላቸው ፡ አንዱ ፡ ዋናው ፡ ወደሚገኝበት፡ ሄዶ ፤ የሆነውን፡ ሁሉ ፡ የሚገልጽ ፡ መግለጫ ፡ ካቀረበ ፡ በኋላ ፤ የከተሜ፡ አውደልዳይ፡ አስከሬን ፡ ወደተጣለበት ፡ ሥፍራ ፡ አንድ ፡ ጓድ ፡ ተላከ ።

የአቶ ፡ ይታገድ ፡ ልጅ ፡ የሰጠው ፡ መምሪያ ፤ የተጣራ፡ በመሆኑ፡ ያለድካም ፡ የከተሜ ፡ አውደልዳይ ፡ አስከሬን ፡ ተገኘ ። አስከሬኑ ፡ ከተ ቀበረበት ፡ ሳይወጣ ፤ አቶ ፡ ይታገድ ፡ ልጁና ፡ ሚስቱ ፡ በጥብቅ ፡ ተመ ርምረው ፡ ያደረጉትን ፡ ሁሉ ፡ አምነው ፡ የተቀበረበትን ፡ መሩ ።



አቶ ፡ ይታገድም ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ ቆየ » ብሎ ፡ ደራሲው ፡ ይህን ፡ ታሪካዊ ፡ ድራማ ፡ መጻፉን ፡ አስረዳኋት ።

በሰማችው ፡ ተደንቃ ፤ ሰው ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ የሚሠራው ፡ ሥራ ፡ እንደጠባዩ ፡ ታሪክ ፡ እየሆነ ፡ ይነገራል ፤ አለችና ፡ ፀሐይ ፤ እስከዚህ ፡ በሰፊው ፡ የተነጋገርነው ፤ በኔ ፡ ርግዝና ፡ ሆኖ ፤ በርግዝናዬ ፡ ወራት ፤ እናትህ ፡ «ኮከቤ ፡» እያሉ ፡ እንደ ፡ ዓይን ፡ ብሌናቸው ፡ ይጠብቁኝና ፤ ከወለድኩም ፡ በኋላ ፡ እየተንከባከቡ ፡ ያርሱኝ ፡ ስለነበር ፤ እናቴና ፡ እናትህ ፡ ያደርጉልኝ ፡ የነበረው ፡ አጠባበቅ ፡ ትዝታው ፡ ከፊቴ ፡ በመ ደቀኑ ፡ ነበር ፡ ብላ ፡ ወደዕለት ፡ ሥራችን ፡ ተሠማራን ።

# ታ ሪ ክ ፡

መወያየት ፡ መልካም ፡ መነጋገር ፡ ጥሩ ፤
ለመሥራት ፡ ተባብሮ ፡ ይኸ ፡ ነው ፡ ምሥጢሩ ።
በሥራ ፡ በሐሳብ ፡ ከተባበርንማ ፤
የፍቅር ፡ ያንድነት ፡ የክብራችን ፡ አርማ ፤
እየጠነከረ ፡ ይኖራል ፡ በግርማ ።
ኃይል ፡ ነው ፡ አንድነት ፤ የብረት ፡ ማሠሪያ ፤
ይቁም ፡ ዓላማችን ፡ ይሁን ፡ መጀመሪያ ።
ሰፋ ፡ ትዳራችን ፡ ሀብታችን ፡ ጻበረ ፤
ስንጀምረው ፡ ገና ፡ ምንም ፡ አልነበረ ።
የተገናኘነው ፡ ሁለታችን ፡ ነበርን ፤
በልጅ ፡ ልጆቻችን ፡ ደመቀ ፡ ቤታችን ።
የዘመኑ ፡ ልጆች ፡ እጅግ ፡ ተፋጠኑ ፤
ለማስቀደም ፡ አባት ፡ ይቅርታ ፡ ለመኑ ።
ገንዘብና ፡ ንብረት ፡ ማስከበሩ ፡ ቀረ ፤
ይልቁንም ፡ ይብስ ፡ ጥላቻን ፡ ፈጠረ ።
ብዙው ፡ ባዶ ፡ እጁን ፡ ነው ፡ የሚያገበግበው ፤
ያለውን ፡ አብዝቶ ፡ ማየት ፡ ነው ፡ የጠላው ።
ቢበዛ ፤ ቢበዛ ፡ እጅግ ፡ ቢትረፈረፍ ፤
ከራስ ፡ በላይ ፡ አልፎ ፡ ለማንም ፡ ሰው ፡ አይተርፍ ።

ከሠራን ፡ ይልቁን ፡ ከደከምን ፡ አይቀር ፤
በምንሠራው ፡ ሥራ ፡ እናትርፍ ፡ ፍቅር ።

መከበር ፡ መዋደድ ፤ የሚገኝ ፡ በሥራ ፤
ይጠንክር ፡ ኃይላችን ፡ ሁሉንም ፡ እንምራ ።

ምንም ፡ ቢትረፈረፍ ፡ ቢሞላ ፡ ቢፈስ ፤
ከአንድ ፡ እንጀራ ፡ በላይ ፡ አይሻም ፡ ራስ ።

የሀብት ፡ መስፋፋት ፤ የሀብት ፡ ብዛት ፤
ከዓይን ፡ ተስፋ ፡ በቀር ፡ የለው ፡ ትሩፋት ፤
ዓለም ፡ አጋፋሪ ፡ ጋባዣችን ፡ ሞት ።

ያልደከመ ፡ ሁሉ ፡ ይወርሳል ፡ ንብረት ፤
ቢሸጥ ፡ ቢለውጠው ፡ የለውም ፡ ጭንቀት ።

ይብዛ ፡ ንብረታችን ፡ ይስፋ ፡ ይባረክ ፤
ሠርተንበት ፡ ሥራ ፤ እናቆይ ፡ ታሪክ ።



ክ ፍ ል ፡ ፱ ፡

# መ ር ዶ ፡

ምጡን ፡ እንደፈራችው ፡ ሳይሆን ፡ ፀሐይ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወለደ ችና ፡ ስሙን ፡ አስረሴ ፡ አለችው ። ገና ፡ ከመወለዱ ፡ ለምን ፡ አስረሴ ፡ አልሽው ?

አዬ ፤ ከአንደበቴ ፡ ለመስማት ፡ እንጂ ፤ ነገሩ ፡ ሳይገባህ ፡ ቀርቶ ፡ አይደለም ። ስንኳን ፡ በርግዝናዬ ፡ ወቅት ፤ ከዚያም ፡ በፊት ፡ በርግዝ ናዬም ፡ ወራት ፡ ቢሆን ፡ እናትህና ፡ እናቴ ፤ ትዝታቸው ፡ በፊቴ ፡ እየ መጣ ፡ አስታውሳቸው ፡ ነበር ። በተለይ ፡ በርግዝናዬ ፡ ወራት ፤ ያደር ጉልኝ ፡ የነበረውን ፡ ማበረታታት ፤ በምግብና ፡ በዕረፍት ፡ እንድጠ በቅ ፡ ስለሚከባከቡኝ ፤ ምጡን ፡ ሳላውቀው ፤ እወልድ ፡ ስለነበር ፡ በእ ሁኑ ፡ ጊዜ ፤ ይህን ፡ አጠባበቅ ፡ ሳጣ ፤ ፍርሃት ፡ በልቤ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ፡ መንፈሴን ፡ ያናውጸው ፡ ነበር ።

ያ ፡ ሁሉ ፡ በቀላል ፡ አልፎ ፡ ደኅና ፡ በመገላገሌ ፤ ያ ፡ የጭንቀት ፡ ጊዜ ፡ አልፎ ፡ በሁለታችን ፡ መካከል ፡ የተገኘውን ፤ ይህን ፡ ፍሬ፡ ዐይቼ፡ የበለጠ ፡ ለመርሳት ፡ በመቻሌ ፤ አስረሴ ፡ ብዬ ፡ ስም ፡ አወጣሁለት ። መልካም ፡ አይመስልህም ?

በአወጣችው ፡ ስም ፡ ተስማማሁና ፤ በፍቅር ፡ የተመሠረተውን ፡ ሰላማዊ ፡ ኑሮዋችንን ፡ እያስፋፋን ፡ ሄድን ። ከሰውነቷ ፡ ተከፍሎ ፡ የወጣውን ፡ መዓዛው ፡ ተወዳጅ ፡ የሆነውን ፡ ሕፃን ፡ አቅፋ ፤ ዕንቅልፍ፡ ውስጥ ፡ ባለችበት ፤ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፤ በመደጋገም ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ሕልም ፡ አልማ ፡ ኖሮ ፤ ከዕንቅልፍ ፡ ስትነቃ ፤ ባየችው ፡ ሕልም ፡ ደነገጠችና ፤ ከዕንቅልፏ ፡ ቀስቅሳ ፡ ያየችውን ፡ እንዲህ ፡ ስትል ፡ ነገረችኝ ።

እናቴ ፡ በሕይወት ፡ በነበረችበት ፡ ዘመን ፡ ምክሯን ፡ ታካፍለኝ ፡ እንደነበረው ፡ ሁሉ ፡ «በሰው ፡ እጅ ፡ የተሠራ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ለማመን፡ ፈጽሞ ፡ የማይቻል ፤ ለንጣቱ ፡ ወደረኛ ፡ የሌለው ፡ ልብስ ፡ ለብሳ ፡ በአጠገቤ ፡ ቆማለች ። ቀና ፡ ብዬ ፡ ስመለከታት ፤ አይዞሽ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤

እኔና ፡ አንቺ ፡ የምንገናኘው ፡ በመንፈስ ፡ እንጂ ፡ በሕይወታዊ ፡ ሥጋ ፡ አይደለም ፡ ብላ ፡ ስትጀምር ፤ እርስዋ ፡ መሆኗን ፡ በርግጥ ፡ ሳውቅ ፡ በናፍቆት ፡ ተመስጦ ፡ ሆኜ ፡ ልስማት ፡ ስቃጣ ፡ ተይ ፤ ለአባትሽና ፡ ለኔ ፤ አንድ ፡ ልጃችን ፡ አንቺ ፡ ብቻ ፡ ስትሆኝ ፤ አባትሽ ፡ ዐይቶ ፡ ሳይጠግብሽ ፡ በሞት ፡ ቀድሞኝ ፡ ሄደ ። ለአቅመ ፡ ሔዋን ፡ ደርሰሽ ፡ ለእናትና ፡ ለአባቱ ፡ አንድ ፡ የሆነ ፡ መከብብን ፡ አግብተሽ ፤ እናንተ ፡ በዝታችኋል ።

በሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ ከተለየሁ ፡ ቆይቻለሁ ። ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ያገኘ ሁት ፡ ደስታ ፡ ሁለት ፡ ነው ። አንቺን ፡ የመሰለ ፡ የተባረከ ፡ ልጅ ፡ ማግ ኘቴና ፡ ማየቴ ፤ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ሞቴ፡ በኖርሁበት ፡ ገዳም ፤ ከኔ፡ የበለጠ፡ ደካማ ፡ ለሆኑት ፡ የሰጠሁት፡ አገልግሎት ፡ ነው ። የቀረው፡ ግን ፡ ከንቱ፡ ነው ።

ልጄ ፡ መቼም ፡ አንቺ ፡ የተባረክሽ ፡ ነሽና ፤ ዕድልሽ ፡ ዕድሌን ፡ እንዲከተል ፡ እመኛለሁ ። ይህን ፡ ስል ፡ ራሳቸውን ፡ ያልቻሉ ፡ ልጆ ችሽን ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ አፍስሰሽ ፤ ገዳም ፡ እንድትገቢ ፡ ማለቴ ፡ አይደ ለም ።

ከታወቀበት ፤ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ቤት ፡ ንብረት ፡ ይዞ ፡ የሚኖር ፤ በገዳም ፡ ዘግተው ፤ በበረሃ ፡ ተሰደው ፡ ከሚኖሩ ፡ የበለጠ ፡ ሥራ ፡ ይሠ ራል ። ሰውነትን ፡ የተቀደሰ ፡ መሥዋዕት ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ ማቅረ ብም ፡ ይቈጠራል ። ሌሎች ፡ በአንቺ ፡ ላይ ፤ ምንም ፡ ቢናገሩ ፡ አንቺ ፡ ግን ፡ ስለሌላው ፡ በቀጥታም ፡ ሆነ ፡ በተዘዋዋሪ ፡ አትናገሪ ።

ልጄ ፤ ይህ ፡ ያልተናቀ ፡ ምን ፡ ይናቃል ፤ የደግ ፡ ተቃራኒ ፡ ክፉ ፤ የክፉ ፡ ተቃራኒ ፡ ደግ ፡ ስለሆነ ፤ ክፉን ፡ በደግ ፡ እንጂ ፡ ክፉን ፡ በክፉ ፡ ለመመለስ ፤ ከቶ ፡ በሕይወት ፡ ዘመንሽ ፡ ሁሉ ፡ እንዳትሞክሪው ፡ አደ ራሽን ።

ይህን ፡ ሁሉ ፡ ለመቋቋም ፡ ሰውነትን ፡ የተቀደሰ ፡ መሥዋዕት ፡ አድርጎ ፡ ማቅረብ ፡ ስለሚጠይቅ ፤ አስተውይ ። ይህን፡ ዓለም ፡ በዚህ፡ ድል ፡ ካደረግሽ ፤ ሌላው ፡ ሁሉ ፡ ከዚህ ፡ ግርጌ፡ ስለሆነ ፤ ታቸንፊያለሽ፡ ሰው ፡ አትናቂ ፤ የፈጠረው ፡ እግዚአብሔር ፡ አልናቀውምና ። የፍጥረ ትን ፡ አመጣጥ ፡ ስትመረምሪ ፤ የሰው ፡ አመጣጥና ፡ አካሔድ ፡ የተመ ሠረቱት ፡ በአንድ ፡ ዓይነት ፡ መንገድ ፡ ነው ።



በሕይወታዊ ፡ ኑሮ ፤ ሰው ፡ ከሰው ፡ የተለየ ፡ ወይም ፡ የተሻለ ፡ መስሎ ፡ ይታያል ። ልጄ ፡ ሆይ ፤ አይምሰልሽ ፤ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ከንቱ ፡ ድለላ ፡ ነው ። እስቲ ፡ ልጠይቅሽ ፤ ከአንድ ፡ እንጀራ ፡ የበለጠ ፡ የሚ መገብና ፤ ከአንድ ፡ ልብስ ፡ የበለጠ ፡ የሚለብስ ፡ ማን ፡ አለ ? ይህን ፡ ስጠይቅሽ ፡ ሳጥን ፡ በማጣበብ ፡ የተቀመጠውን ፡ አይደለም ። ሳጥን ፡ ያጣበበውማ ፤ የዓይን ፡ ማረፊያ ፡ ተስፋ ፡ እንጂ ፤ ሰውማ ፡ ምን፡ ጊዜም፡ ቢሆን ፡ ከአንድ ፡ አያልፍም ።

ራስሽን ፡ የተሻለ ፡ ዐዋቂ ፤ ሌላውን ፡ ግን ፡ ዐላዋቂ ፡ አድርገሽ ፡ ለመገመት ፡ አትሞክሪ ። በተፈጥሮ ፡ ለሰው ፡ ዕውቀት፡ ተሰጥቶታልና፡ አያውቅም ፡ አይባልም ።

ሰው ፡ ከተፈጠረ ፡ ጀምሮ ፡ አስተያየቱና ፡ አስተሳሰቡ፡ ከጊዜው፡ ጋር ፡ እየተለወጠና ፡ እያደገ ፡ ሄዷል ። ለአቅመ ፡ አዳም ፡ ያልደረሱ ፡ ልጆች ፡ ከወላጆቻቸው ፡ የበለጠ ፡ የማስተዋል ፡ ኃይል ፡ እንዳላቸው ፡ ለማሳወቅ ፡ ይሞክራሉ ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ የአባቶች ፡ ሥራ ፡ በልጆች፡ የልጆችም ፡ ሥራ ፡ በአባቶች ፡ አይወደድም ። በሐሳብና ፡ በአስተሳሰ ብም ፡ ይራቀቃሉ ።

ልጄ ፡ ሆይ ፤ ከዚህ ፡ ላይ ፡ ዐዋቂ ፡ ማንኛው ፡ ይመስልሻል ? የል ጆች ፡ አስተሳሰብ ፡ ልጆች ፡ ናቸው ፡ ተብሎ ፡ ሳይናቅ ፤ በእውነተኛ ፡ የአእምሮ ፡ መነጽር ፡ መርምሮ ፡ ጥሩና ፡ ግርዱን ፡ መለየት ፡ ይገባል ። ወላጆችም ፡ ከያዙትና ፡ ከሚከተሉት ፡ ሊለወጥ ፡ ወይም ፡ ሊሻሻል ፡ የሚገባ ፡ ስለሚኖር ፤ እንደዚሁ ፡ መርምሮ ፤ ለይቶ ፡ ማወቅ ፡ ያስፈ ልጋል ።

ልጄ ፡ ሆይ ፤ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ምሳሌ ፡ የነገርኩሽ ፤ የልጆች ፡ እናት፡ ስለሆንሽ ፤ ያንቺና ፡ የልጆችሽ ፡ አስተሳሰብ ፡ በማይገናኝበት፡ ወቅት፡ በምክሬ ፡ ለመጠቀም ፡ እንድትሞክሪ ፡ ነው ። የዛሬ ፡ ልጆች፡ አካላዊ፡ አቅዋማቸው ፡ ከዕድሜያቸው ፡ ጋር ፡ ሳይነጣጠር ፤ ጐልተው ፡ እንደ ሚታዩ ፡ ሁሉ ፤ አእምሮዋቸውም ፡ በዚሁ ፡ መጠን ፡ ቀድሞ ፡ ስለሚያ ስብ ፤ ዕድሜያቸውን ፡ በመቍጠር ፡ አትናቂያቸው ።

ልጄ ፡ ሆይ ፤ ክብርና ፡ ሀብት ፡ የሚያስከብርበት ፡ ጊዜ ፡ አልፎ ፤ ያልበደሉት ፡ ባላጋራ ፡ የሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ ይመጣል ። አስተውይ ፤ ክብርም ፡ ሆነ ፡ ሀብት ፡ በቀላል ፡ ለማግኘት ፡ የምትችይም ፡ ቢሆን ፤

ክብርና ፡ ሀብት ፡ ማስከበሩ ፡ ቀርቶ ፤ ጠላት፡ የሚገዛ ፡ ከሆነ ፤ ለእንቺ፡ አይጠቅምሽምና ፡ ከሰው ፡ ዓይን ፡ ላይ ፡ የሚጥል ፡ ክብርና ፡ ሀብት ፡ ከማግኘት ፡ ራቅ ፡ በይ ።

ጊዜና ፡ ሰዎች ፡ የሚያመጡት ፡ አስተሳሰብ ፤ ሰው ፡ ሰው፡ ነውና፡ ሀገርም ፡ የጋራ ፡ ሀገር ፡ ናትና ፤ ጉዳትዋ ፡ የጋራ ፡ እንደመሆኑ ፤ ጥቅ ምዋም ፡ የጋራ ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ የሚለው ፡ አስተሳሰብ ፤ ከጊዜው ፡ ጋር ፡ እያደገ ፡ ይሄዳል ።

ይህን ፡ አስተሳሰብ ፡ ለማጥናት ፤ ሥራ ፡ የማይወድ ፡ ትውልድ ፤ በሀገርዋ ፡ ውስጥ ፡ እንዳይበቅል ፡ መጣር፡ የኅብረተሰቡ፡ ሁሉ ፡ ግዴታ፡ ነው ። ሆኖም ፡ የማንም ፡ የኑሮ ፡ ደረጃ ፡ በተወሰነ ፡ አቅዋም ፡ ላይ ፡ ከቆመ ፤ የሰዎች ፡ አስተሳሰብ ፡ በየግለሰቡ ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፤ በኅብረተ ሰቡ ፡ ላይ ፡ ከሆነ ፤ አንዱ ፡ በአንዱ ፡ ላይ ፡ የሚያሳየውን፡ ክፉ ፡ ጥላቻ፡ ከአስተሳሰቡ ፡ ውጭ ፡ አውጥቶ ፡ እንደሚጥል ፡ ተስፋ ፡ የሚያደርጉ ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ።

ልጄ ፡ ሆይ ፤ እንግዲህ ፡ በምክሬ ፡ ለመጠቀም፡ ምክሬ ፤ ምክሬን፡ ተቀብለሽ ፡ ጊዜና ፡ ሰዎች ፡ የሚያመጡት ፡ አስተሳሰብ፡ ደርሶ ፤ሰዎች፡ የሚይዙትን ፡ መላ ፡ ቅጡን ፡ ባጡ ፡ ጊዜ ፡ ታስታውሽኛለሽ ፤ በይ ፡ እን ዴኔ ፡ እስክትሆኚ ፡ በመንፈስ ፡ ካንቺ ፡ ጋር ፡ ነኝ ፡ ብላ » ለመሄድ ፡ ስት ነሣ ፡ ልሰማት ፡ እየጓጓሁ ፡ ስከተላት ፤ ሳልሰማትና ፡ ሳልዳስሳት ፡ ከዕ ንቅልፌ ፡ ባንኜ ፡ ቀሰቀሰሁህ ፡ አለች ፡ ፀሐይ ።

ድንጋጤዋን ፡ ከፊትዋ ፡ ለማጥፋት ፤ በዓይኑ ፡ ሥጋ፡ ለመተያየት፡ የተራራቀ ፡ ቤተሰብ ፡ በሕልም ፡ ይታያያል ። አንቺም ፡ እናትሽን ፡ በመ ናፈቅሽ ፡ በሕልም ፡ ስታያቸው ፤ በእናትነታቸው ፡ ምክራቸውን ፡ አበ ረከቱሽ ፡ በማለት ፡ ላጽናናት ፡ ሞከርኩ ።

እኔን ፡ ለማጽናናት ፡ ያሀል ፡ ተናገርክ ፡ እንጂ ፤ እናቴ ፡ እንደሆ ነች ፡ የሞቶች ፡ ይመስለኛል ፡ «እኔና ፡ አንቺ ፤ በመንፈስ ፡ እንጂ ፤ በሕ ይወት ፡ ሥጋ ፡ አንገናኝም ፡ ማለት ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ይመስልኻል ? አለ ችበት ፡ ሄደን ፡ ባየናት ፡ ጊዜ ፤ ስንብታችን ፡ የመጨረሻ ፡ ስንብት ፡ እንደሆነ ፡ እንደነገረችኝ ፡ ታስታውስ ፡ የለም ። ሆዴ ፡ ባባ ፤ እማማ ፡ ሞታለች ፤ ብላ ፤ በሚያምሩት ፡ ዓይኖቿ ፡ ዕንባዋ ፡ ዥረር ፡ ብሎ ፡ ወረደ ።



ላስተዋት ፡ ብቃጣ ፤ ሆዴ ! ተወኝ ፡ ርሜን ፡ ላውጣ ፤ እያለች ፡ ልቅሶ ፡ በማብዛቷ ፡ ማጽናናቱን ፡ ትቼ ፡ እኔም ፡ የልቅሶዋ ፡ ተካፋይ ፡ ሆንኩ ፤ ሁለታችንም ፡ እየያችንን ፡ ያዝን ። አቶ ፡ አይተንፍሱ ፡ የተባ ለው ፡ ጉረቤታችን ፡ ድንገት ፡ ቢደርስ ፤ ፀሐይ ፡ እየተንኈራደደች ፡ ስታለቅስ ፡ እኔ ፡ ለማስጣል ፡ ስጋብዝ ፡ በማየቱ ፡ ቅጡ ፡ ጠፍቶት ፡ ቆሞ ፡ ቀረ ።

ከተረጋጋን ፡ በኋላ ፡ ምን ፡ ሆናችሁ ፤ ማን ፡ ሞተ ፡ ልጆች፡ ደኅና፡ አይደሉም ፡ ወይ ? እያለ ፡ ቢጠይቅም ፤ መልስ ፡ ባለማግኘቱ ፤ ሁለታ ችንንም ፡ አስቀምጦ ፤ ልቅሶዋችንን ፡ እንድናቆም ፡ አድርጎ ፤ ምክንያ ቱን ፡ ጠየቀኝ ።

የፀሐይን ፡ ሕልምና ፡ በዚሁ ፡ መነሻ ፡ ብታለቅስ፤ ሕልም ፡ እልም፡ ነው ፤ ዋጋ ፡ አትስጪው ፡ ብላት ፤ እናቴ ፡ ሞታለች ፡ እርሜን ፡ ማው ጣት ፡ አለብኝ ፡ ተወኝ ፡ ብላ ፡ ለቅሶዋን ፡ በመቀጠልዋ ፤ እናቴና ፡ እና ትዋ ፤ ለኛ ፡ ግርማ ፡ ሞገሳችን ፡ እንደነበሩ ፤ ያንድን ፡ ቤተሰብ ፡ መል ካም ፡ አቅዋም ፡ ሞት ፡ ምን ፡ ያሀል ፡ እንደሚያራቁተው ፤ ባድማው ንም ፡ ምን ፡ ያሀል ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ እንደሚያደርግ፡ አስታውሼ ፤ እኔም፡ አለቀስኩ ፡ አልኩት ።

ጉድ ፡ ነው ፡ እኮ ፡ እባካችሁ ! ሕልም ፡ ዐየሁ ፡ ብሎ ፤ ሕልምን ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ ይለቀሳል ። እኔ ፡ እንዳየሁ ፡ ሌላ ፡ ባያይ ፡ እወዳ ለሁ ። ሁሉም ፡ ከልኩ ፡ አያልፍም ። ጊዜውን ፡ ጠብቆ ፡ ይመጣል ። በሉ ፡ ወደየዕለት ፡ ተግባራችሁ ፡ ተሰማሩ ፡ ብሎ ፡ አይተንፍሱ ፡ ገሥ ጾን ፡ ሄደ ።

ፀሐይ ፡ አልቅሳ ፡ ያልወጣላት ፡ ስለሆነ ፤ የኀዘንዋ ፡ ስሜት ፡ በፊ ትዋ ፡ ይነበባል ። በዚህም ፡ ሁኔታ ፡ ተቸገርኩ፤ ትካዜንና፡ ኀዘንን ፡ አዘ ውትራ ፡ ያዘች ። የሚያረሳሳም ፡ ጭውውት ፡ ቢነሣም ፤ በልብዋ ፡ ውስጥ ፡ የተተከለው ፡ ኀዘን ፡ አልነቀል ፡ አለ ።

ገሥግሼ ፡ ሄጄ ፡ የናትዋን ፡ መኖርና ፡ አለመኖር ፡ ላረጋግጥ ፤ ከሞ ቱም ፡ ርማችንን ፡ እናወጣለን ። መሞታቸው ፡ ከተረጋገጠ ፡ ራሰዋን ፡ በራስዋ ፡ ታጽናናለች ፡ ብዬ ፡ ከወሰንኩ ፡ በኋላ ፤ ይህንኑ ፡ ሐሳቤን ፡ አካፈልኳት ። ርስዋም ፡ በሐሳቡ ፡ ስትተባበር ፤ አብራኝ ፡ ብትሄድ ፡ ወደደች ። ሆኖም ፡ እኔ ፡ እንድሄድ ፡ ተስማማን ።

ረጋ ፡ ብላ ፡ ካሰበች ፡ በኋላ ፡ የኅዳር ፡ ሚካኤል ፡ ከአራት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ይከበራል ። የወዳጆችንን ፡ የቅዱስ ፡ ሚካኤልን ፡ በዓል ፡ እከብረሀ ፡ ብትሄድ ፡ ይሻል ፡ ይመስለኛል ፡ አለችኝ ። ያንቺ ፡ ኀዘን ፤ ትካዜና ፡ ሆደባሻነት ፤ የማይጠገበው ፡ ፈገግታሽና ፡ ጭውውትሽ ፡ በመቀነሱ ፤ ከሥፍራው ፡ ድረስ ፡ ሄጄ ፡ እናትሽን ፡ ላይ ፡ ወደድሁ ። ሐሳቤን ፡ በዚህ ፡ ላይ ፡ ስለአደረግሁ ፡ የኅዳር ፡ ሚካኤልን ፡ በዓል ፡ ፈጽሞ ፡ ረስቼዋለሁ። ስለአስታወስሽኝ፡ አመሰግናለሁ። ስለዚህ፡ በዓሉን፡ ከዋልኩ፡ በኋላ ፡ እሄዳለሁ ፡ ብያት ፡ በዚሁ ፡ ቆረጥን ።

የኅዳር ፡ ሚካኤልን ፡ በዓለ ፡ ንግሥ ፡ ስናከብር ፡ አንድ ፡ አሳቻ ፡ ሰው ፡ ደብዳቤ ፡ ሰጠኝ ። ደብዳቤውን ፡ ተቀብዬ ፡ ከማንበቤ ፡ በፊት ፤ ያመጣውን ፡ ሰው ፡ ለማየት ፡ ቀና ፡ ብል ፡ ከፊቴ ፡ የለም ። ምን ፡ ዓይነት ፡ ሰው ፡ ነው ፤ ይህስ ፡ ደብዳቤ ፡ ከወዴት ፡ የመጣ ፡ ነው ፡ ብዬ ፤ አንቮሎፑን ፡ ከፍቼ ፡ ባነበው ፤ ቅድስትዋ ፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ በሞት ፡ ጥለውት ፡ ከሄዱ ፡ እነሆ ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ በላይ ፡ ሆንዋል ። የቅድስና ፡ ሥራቸውን ፡ በጥሩ ፡ ሁኔታ ፡ አጠናቅቀዋል ። ለልማድ ፡ ወይም ፡ ለወግ ፤ ልጃቸው ፡ እርምዋን ፡ እንድታወጣ ፡ ይነገራት . . . ። ፊርማ ፡ የገዳሙ ፡ አበምኔት ፡ ይላል ።

የወይዘሮ ፡ ዘነበችን ፡ ሞት ፡ ወረቀቱ ፡ ቢናገርም፡ የሰጠኝ ፡ ሰው፡ ጠፋ ። ማን ፡ ሰጠኝ ፡ ብዬ ፡ አወራለሁ ፡ እያልኩ ፡ በትካዜ ፡ ሳስብ ፡ ወረቀቱን ፡ ስቀበል ፡ በእጠገቤ ፡ የነበሩት ፤ የደረሰህ ፡ ደብዳቤ ፡ ምን ፡ ይላል ፤ ከአነበብከው ፡ ጀምሮ ፡ ደንግጠኻል ። የሰጠህን ፡ ሰው ፡ በትክክል ፡ ሳናየው ፡ ጠፋ ። ወረቀቱ ፡ ምን ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ ይዞ ፡ ቢሆን ፡ ነው ፡ የደነገጥከ ? ብለው ፡ ጠየቁኝ ።

አይ ፡ ምንም ፡ አይደለ ፤ በዚህ ፡ ዓለም ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ የለም ፤ የተደረገና ፡ ሲደረግ ፡ የኖረ ፡ ወደፊትም ፡ የሚደረግ ፡ ነው ፡ አልኩና ፡ ትቼአቸው ፡ ከአጠገባቸው ፡ መሰስ ፡ አልኩ ።

ሰዎቹም ፤ ምን ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ብለው ፤ በመገረም ፡ ተያዩ ። የምሥጢሬ ፡ ተካፋይ ፡ የሆነውን ፡ እቶ ፡ አይተንፍሱን ፡ ፈልጌ ፡ ወረቀቱን ፡ አነበብኩለት ። የሰጠኝ ፡ ሰው ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ ከፊቴ ፡ በመጥፋቱና ፡ አንዳንድ ፡ ነገር ፡ ልጠይቀው ፡ ዕድል ፡ ባለማግኘቴ ፤ የተሰማኝን ፡ ቅሬታ ፡ ገለጥኩለት ።



ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ሞተዋል ። ሰጭው ፡ ያልታወቀ ፡ ወረቀት ፡ ደረሰኝ ፡ ብሎ ፡ መናገር ፤ በአንተና ፡ በፀሐይ ፡ መካከል ፡ መጠራጠርን ፡ አይፈጥርም ። በሁለታችሁ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ መተማመን ፤ ፍቅርና ፡ መተሳሰብ ፡ ለኅብረተሰቡ ፡ መልካም፡ ምሳሌ፡ ሆኖ ፡ ስለሚነገር ፤ እስተያየትዋን ፡ አይለውጠውም ።

ማን ፡ ምንም ፡ ቢጠነቀቁ ፡ ሰው ፡ ከሰው ፡ ጀርባ ፡ የማይወርደው፡ ራሱን ፡ እየወደደ ፡ ነው ። ዋጋ ፡ አትስጠው ። የሆነ ፡ ሆኖ ፤ ወረቀቱ ፡ ከማንም ፡ ይድረስህ ፤ የወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ዜና ፡ ዕረፍት ፡ ለፀሐይ ፡ ይነገርና ፡ እርምዋን ፡ ታውጣ ። የመንፈስ ፡ ፀጥታ ፡ ለማግኘት ፤ መካነ ፡ መቃብራቸውን ፡ ሄዳችሁ ፡ እዩ ፡ ብሎ ፡ መከረኝ ። ከልብ ፡ ወዳጄ ፡ ከአቶ ፡ አይተንፍሱ ፡ የቀረበውን ፡ አስተያየት ፤ ሳላመነታ፡ ተቀብዬ፡ የቅርብ ፡ ጐረቤት ፤ የሩቅ ፡ ዘመድ ፡ ተጠርቶ ፡ የወይዘሮ ፡ ዘነበች፡ ዜና፡ ዕረፍት ፡ ለፀሐይ ፡ ተነገረ ።

ቢሆንም ፡ ጥርጣሬው ፡ ወደ ፡ እውነት ፡ ተለውጦ ፤ የቅርብ ፡ ጐረቤት ፤ የሩቅ ፡ ዘመድ ፡ በተሰበሰበበት ፡ እርምዋን ፡ ካወጣች ፡ በኋላ ፤ «ስለናቴ ፡ ሞት ፡ አልቅሼ ፡ ያስለቀስኳቸሁ ፤ በኔና ፡ በናቴ ፡ መካከል ፡ የነበረው ፡ ፍቅር ፤ ትዝ ፡ እያለኝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ እንደ ፡ እውነቱ፡ ከሆነ፡ ለእናቴ ፡ ሞት ፡ አልቅሼ ፤ እናንተንም ፡ ሳስለቅስ፡ አይገባኝም ። ከዚህ፡ ዓለም ፡ ኑሮ ፡ ተለይታ ፡ የገዳም ፡ ሰው ፡ ስትሆን ፤ ተላቅሰን ፡ ተለያይተናል ። የዛሬው ፡ እንዲያው ፡ ነው ። የማይቀረውን ፡ ሞት፡ ስትቀበል፡ ከቅዱሳት ፡ አንስት ፡ አንድዋ ፡ ሆና ፡ በመገኘትዋ ፡ ኀዘኔን ፡ በደስታ ፡ ለውጨዋለሁና፤ ከአሁን ፡ ጀምሮ ፡ ስለርስዋ ፡ ለቅሶ ፡ የለም። » ብላ ፡ ተናገረች ፡ ፀሐይ ።

ማን ፡ እንዳመጣው ፡ ያልታወቀ ፡ ወረቀት ፡ መሠረት፡ አድርገን፡ አልቅሰናል ። አንዱ ፡ እስመስሎ ፡ የጻፈው ፡ ይሆን ፡ ማለታችን ፡ አልቀረም ። ስለዚህ ፡ ከመጠራጠር ፡ ለመንፃት ፡ መካነ፡ መቃብራቸውን፡ ዐይተንና ፡ የዕረፍታቸውን ፡ ዜና ፡ አጣርተን ፡ እንድንመጣ ፡ መክብብና ፡ እኔ ፡ እንሂድ ፡ አለ ፡ እቶ ፡ አይተንፍሱ ።

እማማ ፡ ሞታለች ። ምንም ፡ ጥርጥር ፡ የለውም ፤ የተረጋገጠ ፡ ነው ። ይሁንና ፡ ኅዳር ፡ ሚካኤልን ፡ ውሎ ፡ ሊሄድ ፡ መክብብ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ሳለ ፡ ወረቀት ፡ ደረሰ ። ወረቀቱን ፡ የሰጠው ፡ ሳይታወቅ ፡ ጠፋ ።

ሁኔታውን ፣ ብቻ ፣ ለማወቅ ፣ እንደሆነ ፣ እንጂ ፤ እማማ ፣ እንደሆነች ፣ ሞታለች ፣ አለች ፣ ፀሐይ ። በሕልሟ ፣ ዐይታው ፣ የነበረውን ፣ በማመኗ ።

ኅብረተሰቡ ፣ የሚያከብራቸው ፣ አንድ ፣ አረጋዊ ፣ ለቅሶ ፣ ለመድረስ ፣ መጥተው ፣ ስለነበረ ፤ ታሪካዊ ፣ ሥራ ፣ በማየታቸው ፣ ተደንቀው ፤ ከማን ፣ ጋር ፣ ነው ፣ የምትፈታተኑት ፣ ፀሐይ ፣ ደግ ፣ አስተውላለች ። በእናትዋ ፣ ሞት ፣ ሳትጠራጠር ፣ መሞታቸውን ፣ አረጋግጣ ፣ እርምዋን ፣ ካወጣች ፣ በኋላ ፤ ለቅሶ ፣ እንዲቆም ፣ አድርጋለች ።

ማንኛውም ፣ ነገር ፣ እንደቍስል ፣ እያመረቀዘ ፤ የመንፈስ ፣ ፀጥታን ፣ እየነሳ ፣ በሽታ ፣ የሚሆነው ፤ ተቀባይ ፣ ሲያገኝ፣ ነው ። ተቀባይ፣ ከሌለው ፣ ሁሉም ፣ በጠባዩ ፣ ይወድቃል ። ወደፊት ፣ መጠራጠራችን፣ አይቀርምና ፤ ከጥርጣሬ ፣ የመጣ ፣ አስተሳሰብ ፣ ነው ። ይህ ፣ ከሰው ፣ ባሕርይ ፣ የሚቀዳ ፣ ነው ። ሁላችንም ፣ ባለንበት ፣ አሁን ፣ የተሠራው ታምራት ፣ ጥርጣሬን ፣ ፈጽሞ ፣ የሚያስወግድ ፣ ነውና ፤ ስለወይዘሮ ፣ ዘነበች ፣ የሚደረገው ፣ ማንኛውም ፣ ትዝታ ፣ ኀዘንና ፣ ለቅሶ ፣ ይብቃ ፣ ብለው ፣ እምርረው ፣ ተናገሩ ። ይህ ፣ ከሆነም ፣ በኋላ ፤ በመካከላችን ፣ ያለው ፣ መተሳሰብ ፣ ጊዜ ፣ የማይለውጠው ፤ እውነተኛው ፣ ፍጹም ፣ ፍቅር ፣ ስለሆነ ፣ በመተሳሰብ ፣ የጋራ ፣ ኑሮዋችን ፣ እየጠበቀ ፣ ሄደ ። በከተማ ፣ ከሚኖሩት ፣ ልጆቻችን ፣ ሁለቱ ፣ ከባሕር ፣ ማዶ፣ ተሻግረው፣ ይማራሉ ። ሴት ፣ ልጃችን ፣ ትምህርትዋን ፣ ጨርሳ፣ የምትመለስበትን፣ ጊዜ ፣ የሚያበስር ፣ ወረቀት ፣ ደረሰን ።

ስትመጣ ፣ የምታርፍበትን ፣ ማዘጋጀት ፣ ያዝን ። በምትገባበት ፣ ወቅት ፣ በከተማ፣ተገኝቼ ፣ እንድቀበላት ፣ ደብዳቤ ፣ ጻፍን ። መልስ፣ሳናገኝ ፣ ከተማ ፣ ገብታ ፤ በትምህርት ፣ ዓለም ፣ በቆየችበት ፣ ጊዜ ፣ ካፈራቻቸው ፣ ጓደኞችዋ ፣ ጋር ፣ ዓለሟን ፣ ትቀዳ ፣ ኖርዋል ። ከነገ ፣ ዛሬ ፣ ትመጣለች ፣ እያልን ፣ በመናፈቅ ፣ የምንጠባበቃት ፣ ልጃችን፣ ሳታየን፣ ከአሥር ፣ ቀን ፣ በላይ ፣ ቆየች ።

« የወለደ ፣ ያልጸደቀ ፣ » እንደሚባለው ፣ ልጃቸው ፣ ቡርክት ፤ ከውጭ ፣ ሀገር ፣ ከመጣች ፣ ከአሥር ፣ ቀን ፣ በላይ ፣ ሆኗል ፤ እንዴት ፣ ጨካኝ ፣ ናት ፣ አባትና ፣ እናትዋን እስካሁን ፣ ሳታይ ? እየተባለ ፣ የሚነገረው ፣ ሐሜት ፣ እጆሮአችን ፣ ገባ ። ክቶ ፣ አይደረግም ፣ አለች ፣ ፀሐይ፤ እኔ ፣ ግን ፣ ለምን ፣ አይደረግም ? ይደረግ ፣ ይሆናል ፣ አልኩ ። ማዘኔን ፣



ፀሐይ ፣ አወቀችና ፣ ምን ፣ አለ ፤ ደኅና ፣ ትሁን ፣ እንጂ ፤ ውላ ፣ አድራ ፣ ትመጣለች ፣ አለችኝ ።

እንዲያውም ፣ ሰሞኑን ፣ ስለርስዋ ፣ ልናደርገው ፣ የነበረውን ፣ መስናዶ ፣ ተውነው ። ከሰማን ፣ ከአምስት ፣ ቀን ፣ በኋላ ፣ መጣች። የወለደ፣ ሆድ ፣ አይጨክንምና ፣ ባየናት ፣ ጊዜ ፣ ከመናፈቃችን ፣ የተነሣ ፣ እንገትዋ ፣ ላይ ፣ ተጠምጥመን ፣ እያለቀስን ፣ ሳምናት ። የርስዋ ፣ ናፍቆት ፣ ግን ፣ የቀዘቀዘ ፣ ስለነበረ ፤ የጋለ ፣ የናፍቆት ፣ ስሜት ፣ አላሳየችንም ። ዓይን፣ዓይንዋን፣እያየን ፣ ገና ፣ ናፍቆታችንን ሳንወጣው ፣ ወደ ፣ ከተማ ፣ መመለስ ፣ እንዳለባት ፣ ለእናትዋ ፣ ነገረች ። በዚህን ፣ ጊዜ ፣ ፀሐይ ፣ በጣም ፣ አዝና ፣ ናፍቆትሽ ፣ አልወጣልንም ። እንዲያውም ፣ ከውጪ ፣ ከመጣሽ ፣ አሥራ ፣ አምስት ፣ ቀን ፣ እንደሆነሽ ፣ ሰምተን ፣ አዝነን ፣ ነበር ። ዓይንሽን ፣ በዓይናችን ፣ ባየን ፣ ጊዜ ፣ ኀዘናችንን ፣ በደስታ ፣ ለውጠን ፣ ረሳነው ። በሰው ፣ ሀገር ፣ መቆየት ፣ ጨካኝ፣ ያደርጋል ። የተማርሽውስ ፣ ትምህርት ፣ ቤተሰብ ፣ ያስጠላል ? እኛም ፣ ሆነ ፣ ወንድሞችሽና ፣ እኅቶችሽ ፣ መቼ ፣ ናፍቆታችን ፣ ተከፈለልን ። እንዴት ፣ በሦስት ፣ ቀን ፣ ውስጥ ፣ ከኛ ፣ ተለይተሽ ፣ ትሄጃለሽ ? ደግሞስ ፣ ሄደሽ ፣ ወዴት ፣ ነው ፣ የምታርፊው ? ገና ፣ ሥራ ፣ አልያዝሽ ፤ እንደምንስ ፣ ትኖሪያለሽ ? አለቻት ፤ በማዘንም ፣ በመገረምም ።

ይሁን ፣ እንጂ ፣ የፀሐይ ፣ ማወትወት ፣ የወይዘሪት ፣ ቡርክትን ፣ አስተሳሰብ ፣ ክቶ ፣ ሊለውጠው ፣ አልቻለም ። ቡርክት ፣ የሚታያት ፣ በከተማ ፣ ያልዋትና ፣ የሚጠብቅዋት ፣ ጓደኞችዋ ፣ በየሳምንቱ ፣ ዓርብ ፣ ማታ ፤ ዳንኪራ ፣ ስትረግጥ ፣ የምታድርበት ፣ መደሰቻ ፣ (ናይት ፣ ክለብ) ስለሆነ ፤ የእናትዋን ፣ አነጋገር ፣ ዋጋ ፣ አልሠጠችውም ። በእናትዋ ፣ ምክር ፣ ሁለት ፣ ቀን ፣ ካደረች ፣ በኋላ ፤ ካልሄድኩ ፣ ብላ ፣ እንደገና ፣ እስቸገረች ። የመጀመሪያውንና ፣ ያሁኑን ፣ የመሄድ ፣ እሳቧን ፣ ሰማሁ ። ከውጪ ፣ ሀገር ፣ መጥተሽ ፤ አሥራ ፣ አምስት ፣ ቀን ፣ በከተማ ፣ ስትቆዪ፤ እሉ ፣ ወይም ፣ የሉም ፣ ብለሽ ፣ መቼ ፣ ጠየቅሽን ፣ የወላድ ፣ ሆድ ፣ ሆኖ ብን ፣ ባየንሽ ፣ ጊዜ ፣ ቅሬታችንና ፣ ኀዘናችንን ፣ በደስታ ፣ ለወጥነው ፣ እንጂ ፤ ጭካኔሽን ፣ በዚህ ፣ ብቻ ፣ መረዳት ፣ በተገባን ፣ ነበር ። በወላጅና ፣ በልጅ ፣ መካከል ፣ ያለውን ፤ አሁን ፣ ማመዛዘን ፣ ባትቺይም ፣ ስትወልጂ ፣ ታገኝዋለሽ ፤ በዚያን ፣ ጊዜም ፣ እኛን ፣ ታስታውሻለሽ ። አሁን ፣ ግን ፣ ከፈቃዳችን ፣ ውጪ ፣ ስለሆንሽ ፣ የወደድሽውን፣ ማድረግ፣ ትችያለሽ ፣ ብዬ ፣ ቁርጥ ፣ ያለ ፣ ቃል ፣ ነገርኳት ።

ቡርከት ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ጉዳይዋ፡አይደለም ። እንዲያውም፡‹‹ዱ፡አይ፡ ኬር ፡ » ግድ ፡ አለኝ ? ብላ ፡ ለመሄድ ፡ ዕቃዋን ፡ አዘጋጀች ። አይጨ ክኔ ! እምዬ ፡ እናት ፤ እባክሽን ፡ የዛሬን ፡ እደሪና ፡ ነገ ፡ ሂጂ ፡ ብላ ፡ ለመነቻት ። እዬዬ ፤ ይህ ፡ ጥቁር ፡ ሕዝብ ፡ ከቶ ፡ መቼ ፡ ይሆን ፡ ሰው ፡ የሚሆን ፡ ብላ ፡ በብስጭት ፡ ስትቀመጥ ፡ ሰማኋት ።

የኛ ፡ ፈረንጅ ፡ ምን ፡ አልሽ ፡ እባክሽን ፡ አልኩና ፡ ከላይዋ ፡ ላይ ፡ ጉብ ፡ ብዬ ፡ አባታዊ ፡ ቅጣት ፡ ስፈጽምባት ፡ በጮኸች፡ ጊዜ፡ ደንግጣ፡ ከውጪ ፡ እንደገባች ፡ ከላዬ ፡ ላይ ፡ ወድቃ ፡ አስጣለቻት ፡ ፀሐይ ።

ውዴ ፡ ፀሐይ ፡ ከተገናኘን ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፤ ሐሳቤ፡ ከሐሳብሽ ፤ ሐሳብሽ ፡ ከሐሳቤ ፡ ጋር ፡ ሳይጋጭ ፡ ተስማምተን ፡ ኖረናል ። አሁን ፡ የምለምንሽ ፤ የኛ ፡ ፈረንጅ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ መሄድ ፡ የለባትም ። ቀጥ ፡ ብላ ፡ የቤት፡ባልትና ፡ ሥራ ፡ እዚሁ ፡ ትሥራ ። በሠራችው ፡ ተፀፅታና ፡ ጠባይዋን ፡ አርማ ፡ መልካም ፡ ጠባይ ፡ እስክትይዝ ፡ ድረስ ፡ ከኛ ፡ ልትርቅ ፡ አይገባትም ፡ አልኳት ።

አይ ፤ ይህ ፡ ሁሉ ፡ እንዳይደርስ ፡ ብዬ ፡ ለብቻ ፡ መክሬያት ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ልጇን ፡ ምን ፡ እንዳስነከዋት ፡ በውነቱ፡ አላውቅም። የኛ ፡ ልጅ፡ ሆና ፤ እንደዚህ ፡ ትሁን ! የሚያስለቅስና ፡ የሚያሳዝን ፡ ነው ። ይህ፡ ብቻ ፡ አይምሰልህ ፤ ከቦርሳዋ ፡ ወጣ ፡ አድርጋ ፡ የምታጨሰው፡ ጢስ፡ አለ ። ባለምደው ፡ እንደሆን ፡ እንጂ ፡ ሽታው ፡ ጥሩ ፡ አይደለም ። የመጣ ችለት ፡ ስስማት ፡ የአፍዋ ፡ ጠረን ፡ እንደ ፡ ጢስ ፡ ይሸት ፡ ነበር ። እንዳል ነግርህ ፤ ትንሽ ፡ ትልቁን ፡ ለወንድ ፡ መንገር ፡ ጥሩ ፡ ባለመሆኑ ፡ ነው ።

አሁንም ፡ መልካም ፡ አሰበኻል ። ርስዋ፡ አኩራፊ ፤ እኛም ፡ አኩ ራፊ ፡ ሆነን ፡ የወደድሽውን ፡ ወይም ፡ የፈለግሽውን፡ ለማድረግ ፡ መብ ት ፡ አለሽ ፡ ብለን ፡ መረን ፡ ብንለቃት ፤ ነገ ፡ ፀፀቱ ፡ ተመልሶ ፡ ለኛ ፡ ነው ፡ አለች ፡ ፀሐይ ።

ለካስ ፡ ትምባሆ ፡ ታጨሳለች ። ጉሽ ፡ የኛ ፡ ልጅ ፡ ምንኛ ፡ ተም ራለች ፤ ምንኛስ ፡ ሠልጥናለች ። የትምባሆ ፡ ልማድ ፡ ካላትማ ፤ ምን ፡ ተስፋ ፡ አለ ? መቼስ ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ እንችላለን ። ከርስዋ ፡ የጠበቅ ነው ፡ ይህ ፡ አልነበረም ። እግዚአብሔርን ፡ የበደልነው ፡ ይኖራል ፤ እኛን ፡ ለመቅጣት ፡ የመጣ ፡ ነውና ፡ ይቅር ፡ ይበለን ፡ ብዬ ፡ ወደፈጣ ሪዬ ፡ አመለከትኩ ።



ከኛ ፡ ያልጠበቀችው ፡ ጠንካራ፡ ቅጣት ፡ በደረሰባት ፡ ጊዜ ፡ ደነገ ጠች ። እንግድነትዋ ፡ ቀርቶ ፡ ወደ ፡ ጓዳ ፡ ገባ ፡ ብላ ፡ ማናቸውንም ፡ ሥራ ፡ እንድትሠራ ፡ ታዘዘች ። ይሁንና ፡ ከሥራው፡ ጋር ፡ ገና ፡ ያልተ ዋወቀች ፡ በመሆንዋ ፤ ግራ ፡ ገባት ። እናትዋ ፡ ሁኔታውን ፡ ካጠናች ፡ በኋላ ፤ ይህች ፡ ልጅ ፡ ለአቅመ ፡ ሔዋን፡ ደርሳለች ። የቤት፡ እመቤት፡ የሚጠይቀውን ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ የሚያስችል ፡ አንድም ፡ ዕውቀት፡ የላት ። ባል ፡ ብታገባ ፤ ርስዋ ፡ ከወንድ ፡ የማትሻል ፡ ከሆነ፤ ቤቱ፡ በማን፡ ይመራል ? ይህማ ፡ ወላድ ፡ የበደለሽ ፡ እየተባለች ፤ ተሰድባ ፡ ልታሰድ በን ፡ አይደለም ?

ሴት ፡ ልጅ ፡ የቤት ፡ባልትና ፡ሞያ ፡ ከሌላት ፤ መልክዋን ፡ ብቻ ፡ አይቶ ፡ የሚያገባ ፡ ይኖር ፡ ይሆን ? አሽከርና ፡ ገረድ ፡ ቢቀጠርስ ፤ ቤቱ ፡ መመራት ፡ ያለበት ፡ በቤትዋ ፡ እመቤት ፡ ነው ። ካላወቀች ፤ ቤት ዋን ፡ እንደምን ፡ አድርጋ ፡ ልትመራ ፡ ትችላለች ኧረ ፡ ጉድ ፡ ነው ። ይህችን ፡ ልጅ ፡ ማስተማር ፡ አለብኝ ፡ አለችና ፤ ብታምንበትም፡ ባታምንበትም ፡ ጉድለትዋን ፡ እያስረዳች ፡ መሞከርና ፡ ማስተማር ፡ ጀመረች ፡ ፀሐይ ።

ልጄ ፡ ሆይ ፤ በባዕድ ፡ ሀገር ፡ የቆየሽበት ፡ ጊዜ ፡ ትንሽ ፡ ባለመ ሆኑ ፤ እኔ ፡ የማላውቀውን ፡ ተምረሽ ፡ ይሆናል ። ይሁንና ፡ እኔ ፡ ከማው ቀው ፡ ከቤት ፡ ባልትና ፡ ሞያ ፤ አንዱንም ፡ ባለማወቅሽ ፡ በኔ ፡ ዘንድ ፡ የተማርሽ ፡ አይደለሽም ። ምንም ፡ ሌላ ፡ ዕውቀት ፡ ኖሮሽ ፤ ወንዶች ፡ ከዋሉበት ፡ ብትውይ ፤ ሴት ፡ በመሆንሽ ፡ ሌላ ፡ የቤት ፡ ውስጥ ፡ ኃላፊ ነት ፡ አለብሽ ፤ የቤት ፡ ውስጥ ፡ ኃላፊነት ፡ ወስደሽ ፡ ቤትሽን ፡ በቤት ፡ ባልትና ፡ ሞያ ፡ ለመምራት ፡ የሚያስችል ፡ ዕውቀት፡ ያለሽ፡ ይመስልሽ፡ ይሆን ? ሌላ ፡ የውጭ ፡ ሥራ ፡ ከመያዝሽ ፡ በፊት ፤ የቤት ፡ ባልትና ፡ ሞያ ፡ ማወቅ ፡ አለብሽ ።

ኧረ ፡ ቤት ፡ እንደዚሁ ፡ በቀላል ፡ የሚተዳደር ፡ አይምሰልሽ ። ልጅ ፡ መውለድ ፡ አለ ። የወለዱትን ፡ ልጅ ፡ ጤናውን ፡ ጠብቆ ፡ ማሳ ደግ ፡ ቀላል ፡ ሥራ ፡ አይደለም ፡ ገረድና ፡ አሽከር ፡ የማይገኝበት፡ ጊዜ፡ አለ ። ሞያ ፡ ካለ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ፡ ወደ ፡ ወጥ ፡ ቤት፡ ገባ ፡ ብሎ ፡ ሁሉን፡ ለማዘጋጀት ፡ ይቻላል ፤ ከሌለም ፡ የሚወድሽን ፡ ወይም ፡ የምትወጂ ውን ፡ ባልሽን ፡ ዓይን፡ ዓይኑን፡ ብታዪው ፤ ይሰድብሻል ፤ ወይም፡ ንቆ ፡ ይጠላሻል ፡ እንጂ ፤ አንቺ ፡ እያለሽ ፡ ርሱ ፡ ወጥ ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ አይሠ

ራልሽም ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እናቴ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይይልሽ ፤ ነፍስሽን ፡ አይማረው፡ ትያለሽ ። ልጄ ፡ ስለዚህ ፡ በአጭር ፡ ታጥቀሽ ፡ እየሠራሽ ፡ መማር ፡ አለብሽ ፡ አለቻት ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ቡርክትን ፡ አለወጣትም ። እንዲያውም ፤ ይህን ፡ ያህል ፡ ዘመን ፡ በውጭ ፡ ቆይቼ ፤ ብዙ ፡ ነገር ፡ አይቼና ፡ ተምሬ ፡ የመጣ ሁት ፤ ወጥ ፡ ቤት ፡ ገብቼ ፡ ከነርሱ ፡ ጋር ፡ ልልኰስኰስ ፡ ነው ? አላደር ገውም ፡ የፈለጉትን ፡ ያድርጉ ፡ እያለች ፡ ራስዋን ፡ ለራስዋ ፡ ታነጋ ግራለች ። እምዬ ፡ እናት ፡ ግን ፤ በቁጣ ፡ ሳይሆን ፡ በማቆላመጥ ፤ ይህን ፤ እንደዚህ ፡ አድርጊው ፡ እያለች ፡ ስታሠራት ፤ ሰው ፡ ኑሮው ንና ፡ አካባቢውን ፡ ይመስላል ፡ እንደሚባለው ፡ ከቀን ፡ ወደ ፡ ቀን ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ እየተለዋወጠ ፡ እናትዋን ፡ መከተል ፡ ቻለች ። የሥራ ውም ፡ ፍቅር ፡ አደረባት ፡ ያልበሰለውን ፡ አብስሎ ፡ ማቅረብ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፤ የቤት ፡ እመቤት ፡ በቤት ፡ ውስጥ ፡ ያለባትን ፡ ኃላፊነት ፡ ጭምር ፡ ስታስተምራት ፤ የቤትሽ ፡ የውስጡ ፡ ኃላፊ ፡ አንቺ ፡ ብቻ ፡ ነሽ ። ማናቸውም ፡ ነገር ፡ ከቤት ፡ ውስጥ ፡ ፈጽሞ ፡ እስኪያልቅ ፡ መጠ በቅ ፡ የለብሽም ። ዕለት ፡ በዕለት ፡ ገበያ ፡ ከወጣሽ ፡ ቤትሽ ፡ በረከት ፡ ያጣል ። ቢሆንም ፡ ለዓመት ፤ ቢያንስ ፡ ለመንፈቅ ፡ የሚሆን ፤ ከማናቸ ውም ፡ በቤትሽ ፡ ውስጥ ፡ መዘጋጀት ፡ ወይም ፡ መኖር ፡ አለበት ። ይህን፡ ጠብቀሽ ፡ ከማለቁ ፡ በፊት ፡ ከተካሽ ፤ ለመንፈቅ ፡ ያዘጋጀሽው ፡ ጊዜ ፡ እየጨመረ ፡ ይሄዳል ። በዚሁ ፡ መጠን ፡ ቤትሽ ፡ የበረከት ፡ ቤት ፡ይሆ ናል ፡ እያለች ፡ ስትነግራት ፤ የእናትዋ ፡ ሐሳብ ፡ ጠቃሚ ፡ መሆኑን ፡ ከጊዜ ፡ ወደጊዜ ፡ እየተገነዘበች ፤ የተማረ ፡ መቼም ፡ አጥፍቶ ፡ አያጠፋ ምና ፤ የምትላትን ፡ ሁሉ ፡ በጽሕፈት ፡ እየመዘገበች ፡ ያዘች ።

የቤት ፡ ባልትና ፡ ሥራው ፡ ጊዜ ፡ ሳይፈጅባት ፡ ቤቱን ፡ ቀጥ ፡ አድርጋ ፡ ያዘች ። ሁሉንም ፡ አሳክታ ፡ እንዳወቀች ፡ ፀሐይ ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፤ «ምንም ፡ ብቀጥን ፡ ጠጅ ፡ ነኝ» እንደተባለው ፤ ልጃችን ፡ የተማ ረች ፡ ናት ። እኛ ፡ የማናውቀውን ፡ ታውቃለች ። በኛ ፡ በኩል ፡ ልታ ውቅ ፡ ይገባታል ፡ ያልነውን ፡ ወደውጭ ፡ ከሄደች ፡ በኋላ ፡ ረስታው ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ በዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ ትከታተል ፡ ስለነበር ፤ ያ ፡ መሠረት ፡ ሆኗት ፤ ሁሉም ፡ ቶሎ ፡ ገብትዋት ፡ ቤቱን ፡ ቀጥ ፡ አድርጋ ፡ የያዘች ፡



ርስዋ ፡ ነች ። ጥረታችንን ፡ እንድታውቅ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ካወቀች ፡ ራስ ዋን ፡ በራስዋ ፡ የምትረዳው ፤ ንብረት ፡ ከያዘች ፡ በኋላ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ትመለስ ፡ ብላ ፡ አማከረቺኝ ፡ ፀሐይ ።

እውነትሽን ፡ ነው ። ሆኖም ፡ « ታጥቦ ፡ ጭቃ ፡ » እንደተባ ለው ፡ አሁን ፡ ስትመለስ ፤ እዚያው ፡ አስረሽ ፡ ምቺው ፡ ከሚባልበት ፡ ቦታ ፡ ገብታ ፤ ያን ፡ ትምባሆ ፡ ታጨስ ፡ ይሆናል፡ እንግዲህ ፡ አካባቢው፡ ጭምት ፡ ካልሆነ ፤ ርስዋንና ፡ ርስዋን ፡ የመሰሉት ፡ አስተሳሰባቸውን ፡ ሰፋ ፡ አድርገው ፡ በተማሩት ፡ ትምህርት ፡ ኀብረተ ፡ ሰቡን ፡ የሚጠቅ ምና ፡ ኀብረተሰቡ ፡ የሚቀበለውን ፡ ካልሠሩ ፤ አንድና ፡ ሁለት ፡ ቤተ ሰቦች ፡ በልጆቻቸው ፡ ላይ ፡ ብርቱ ፡ ቊጥጥር ፡ ቢያደርጉስ፡ መች ፡ ድኅ ነት ፡ ይገኛል ! ! !

ኀዘናችንና ፡ ቁጣችን ፡ ለራስዋ ፡ መሆኑን ፡ እንንገራትና፡ ለኑሮዋ ፡ የሚያስፈልጋትን ፡ አዘጋጅተን ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ትመለስ ፡ አልኳት ። ሁለታችን ፡ ብቻ ፡ ባለንበት ፡ ቡርክት ፡ ተጠራች ። ደንገጥ ፡ ብላ ፡ ቶሎ ፡ መጣች ። ቁጭ ፡ በይ ፡ አልናት ። የጀመርኩትን ፡ ሥራ ፡ እስካ ጠናቅቅ ፡ ይቅርታ ፡ አድርጉልኝ ፡ አለችና ፡ ፈቀድንላት ። ሥራዋን ፡ እንደጨረሰች ፡ መጣችና ፡ ቆመች ። ባሳየችው ፡ ትሕትና ፤ በጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ትልቅ ፡ ለውጥ ፡ በማምጣቷ ፡ ተደሰትን ።

ልጄ ፡ ቡርክት ፤ ብዬ ፡ ልናገር ፡ ስጀምር ፡ ዕንባዋን ፡ በማፍሰስ ፡ ምርር ፡ ብላ፡አለቀሰች ። ፀሐይ ፡ ብታባብላትም ፡ ዕንባዋ ፡ አልቆም ፡ አለ ። እኔም ፡ ባባብል ፡ ከልብ ፡ በስሜት ፡ ፈንቅሎ ፡ የመጣ ፡ ስለሆነ ፤ ዕንባዋ ፡ አልቆም ፡ አለ ።

ፀሐይም ፡ ልቅሶዋን ፡ ጀመረች ። ሚስቴንና ፡ ልጄን ፡ ተቆጥቼ ፡ ልቅሶዋቸውን ፡ ገቱ ። ዕንባቸውን ፡ ከጠራረጉ ፡ በኋላ ፤ የጀመርኩትን ፡ ልቀጥል ፡ ስደራጅ ፤ ቡርክት ፡ ሲቃ ፡ ይዟት ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ እያለች ፡ ስለተጨነቀች ፤ አሁን ፡ ትረፍ ፡ ብላ ፡ ወደ ፡ መኝታ ፡ ቤት ፡ ወሰደቻት ፡ ፀሐይ ።

በማግሥቱ ፡ ቡርክት ፡ እንደገና፡ ተጠርታ ፡ መጣች ። ቡርክትዬ ፡ ትናንትና፡ ልንነግርሽ ፡ ያሰብነውን ፡ ዛሬ፡ እንቀጥላለን። ልጃችን፡ሆይ፡ ናፍቆታችን ፡ ሳይከፈል ፤ ልብሽን ፡ በነገር ፡ አሻከረነዋል ። በኛ፡ ቁጣ፡ በኛ ፡ ክፉ ፡ ንግግር ፡ ልብሽ ፡ ቢሻክር ፡ ነገ ፡ ታመሰግኝናለሽ ። የትና

ንቱ ፡ ዕንባ ፡ የመፀፀት ፡ ምልክት ፡ እንደሆነ ፡ ስለተረዳነው ፡ በእኛ ፡ በኩል ፡ የቀድሞዋ ፡ ቡርከት ፡ ትሆኛለሽ ፡ ብለን ፡ ተስፋ ፡ አድርገ ናል ። መማር ፡ እስከምን ፡ ድረስ ፡ ነው ? በማመር ፡ ሰው ፡ ይታረማል፡ እንጂ ፤ በመማር ፡ ሰው ፡ የሌለበትን ፤ ኅብረተሰቡ ፡ የማይቀበለውንና፡ የማይወደውን ፤ ለሀገሩና ፡ ለራሱ ፡ የማይጠቅመውን ፡ እንዴት ፡ ይማ ራል ! ! !

ለምሳሌ ፡ ትምባሆ ፡ ታጨሻለሽ ። ባሕር ፡ ማዶ፡ የላከንሽ፡ይሆን፡ እንድትማሪ ፡ አልነበረም ። ለዚህማ ፡ ከሆነ ፡ እዚሁ ፡ ያሉትም ፡ ስለሚ ያጨሱ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ጉዞ ፡ አያሻሽም ፡ ነበር ። ይህ ፡ ልማድ ፡ ራስ ሽን ፡ በምን ፡ በኩል ፡ ይጠቅምሻል ? ልማዱስ ፡ ለኅብረተሰቡ ፡ ምን ፡ ይጠቅማል ? ከውጪ ፡ የተቀዳ ፡ ልማድ ፡ ከውስጥ ፡ ባህል ፡ ጋር ፡ እየ ተጋጨ ፤ ከጥቅሙ ፡ ይልቅ ፡ ጉዳትን ፡ እንዳያስከትል ፡ መጠንቀቅ ፡ የያንዳንዱ ፡ ብሔራዊ ፡ ግዴታ ፡ ነው ።

ከውስጥ ፡ ባህልና ፡ ልማድ ፡ የሚጣልና ፤ የሚተካ ፡ ቢኖርም ፤ ጥሩና ፡ ግርዱን ፡ የሚያበጥረው ፡ በትምህርት ፡ የተፈተገ ፡ አምዕሮ ፡ አልነበረም ? ትምህርት ፡ የፈተገው ፡ አዕምሮ ፡ ግዙፉንና ፡ ረቂቁን ፡ ያነጥራል ።

ልጃችን ፡ ሆይ ! የሚጠላውንና ፡ የሚወደደውን ፤ ለይቶ ፡ የሚያ ውቅ ፡ ጠፋ ። ሁሉም ፡ በየግል ፡ አስተሳሰቡና ፡ እምነቱ፡ እራመዳለሁ፡ እያለ ፤ የገደል ፡ ማሚቶ ፡ ሆነ ። ልጅ ፡ ያዋቂዎችን ፤ አዋቂዎችም፡የል ጆችን ፡ አያስተውሉም ። ልጃችን ፡ ከውጪ ፡ ተመልሰሽ ፡ በመካከላ ችን ፡ በመገኘትሽ ፡ ደስ ፡ ሲለን ፤ ካንቺ ፡ ያልጠበቅነውን ፡ ጠባይ፡በአ ንቺ ፡ ላይ ፡ አየን ።

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ልባችን ፡ በኀዘን ፡ ተነካ ። ከማዘናችን ፡ የተነሣ ፤ እንደፈለገሽ ፡ ሁኝ ፡ አልን ። ይህን ፡ ማለታችን ፤ ስሕተት ፡ ሆነ ። ስሕ ተታችንን ፡ አርመን ፡ ወግ ፡ ነው ፡ ብለሽ ፡ የያዝሽውን፡ እንድታርሚ፡ ለማድረግ ፡ በቍጥጥራችን ፡ ውስጥ ፡ ያዝንሽ ፤ እግዚአብሔር፡ ይባርክ ሽና ፡ በጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ተመለስሽ ። ከእንግዲህ፡ በኋላ ፡ የሚለውጥሽ ፡ የለም ።

ልጃችን ፡ ሆይ ! ስለከተማ ፡ አኗኗርሽም ፡ ቢሆን ፤ ብንመክ ርሽ ፡ እንወዳለን ። ሰው ፡ ደግና ፡ ክፉውን ፡ የሚማረው ፡ ከሰው ፡ ላይ፡ ነው ። ዘወትር ፡ መልካም ፡ ከሚያስቡና ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ ከሚሠሩ ፡ ጋር ፡



የሚውል ፤ የበጎ ፡ ሥራ ፡ ዓላማ ፡ ይከተላልና ፡ ወዳጅና ፡ ጓደኛ ፡ የምታ ደርጊያቸውን ፡ ሰዎች ፤ በመልካም ፡ ምግባራቸው ፡ ብቻ ፡ ምረጪ ።

ሴት ፡ መሆንሽን ፡ አትርሺ ። ሴት ፡ ልጅ ፡ የምትመረጠው ፤ በው በትዋ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፤ በጠባይዋ ፡ ነው ። ሴትን ፡ ልጅ ፡ የሚያስከብ ራት ፡ ትዳርዋ ፡ ነው ። ትዳር ፡ ከሌላት ፡ በማንኛውም ፡ ትደፈራለች ። ሴት ፡ ልጅ ፡ የቤት ፡ እመቤትና ፡ እናት ፡ ነች ። መልካም ፡ ዘር፡ ለሀገር፡ ታበረክታለች ።

የሰው ፡ ልጅ ፡ ከጨለማ ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ የተሸጋገረውና ፡ ደኅን ነት ፡ ያገኘው ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከሴት ፡ በተገኘ ፡ ቅዱስ፡ ዘር፡ ነው። ቅድስና ፡ የሚገኘው ፡ ከንጽሕና ፡ ነው ።

ልጄ ፡ ሆይ ! የሰውን ፡ ፍጻሜ፡ እስቲ ፡ አስተውዪው። ሰው፡የዚህ፡ ዓለም ፡ ቴያትር ፡ ሆኖ ፡ ከመታየቱ ፡ በቀር ፡ ፍጻሜው፡ ምን፡ ያምራል? ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፤ በቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ የታዘዙትን ፡ የእግዚአብሔ ርን ፡ ትእዛዛት ፡ ከመፈጸምና ፡ ለሀገርና ፡ ለወገን ፡ የሚበጅ ፡ ሥራ ፡ ሠርቶ ፡ ከማለፍ ፡ የተሻለ ፡ ምንም ፡ ምርጫ ፡ የለም ።

ልጄ ፡ ሆይ ! በአሁኑ ፡ ዕድሜሽና ፡ ሁኔታሽ ፡ ይህ ፡ ምክሬ ፡ በአ ንቺ ፡ ዘንድ ፡ የተጠላ ፡ ነው ። ጣፋጭ ፡ ነው ፡ ብለሽ ፡ የያዝሽው ፡ የዓ ለም ፡ ኑሮ ፤ ከጣፋጭነት፡ ወደ፡ መራራነት፡ ከዕድሜ ፡ ጋር ፡ የሚለወጥ በት ፡ ጊዜ ፡ በፊትሽ ፡ ተደቅኖ ፡ ስለሚጠብቅሽ ፤ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ታስ ታውሽን ፡ ይሆናል ፡ ብዬ ፡ ከእውነተኛ ፡ ስሜት ፡ በመነጨ ፡ የአባት ነት ፡ ምክሬን ፡ መከርኳት ።

አንገትዋን ፡ ጐንበስ ፡ አድርጋ ፡ መሬት ፡ እየቆረቆረች ፤ የኔን ፡ የአባትዋንና ፡ የእናትዋን ፡ ምክርና ፡ ተግሣጽ ፡ አዳመጠች ። እስተያየ ትዋን ፡ ለመግለጥ ፡ ስትጀምር ፤ በዓይኖችዋ ፡ ዕንባ ፡ ግጥም ፡ አለ ። መናገርም ፡ ባለመቻልዋ ፡ ንግግርዋ ፡ ተቋረጠ ። ከለቅሶዋ ፡ ገብ፡ ብላ፡ ንግግርዋን ፡ ቀጠለች ።

አባባ ፤ እማማ ፤ ምክራችሁንና ፡ ተግሣጻችሁን፡ በጥሞና ፡ ተቀ ብየዋለሁ ። በኔ ፡ የዕውቀትና ፡ የዕድሜ ፡ ደረጃ ፡ የደረሱት ፡ ቀርቶ ፡ ፊደል ፡ የቈጠሩ ፡ የሚናገሩት ፡ ሁሉ ፤ ከዕውቀት ፡ የመነጨ ፡ እየመሰ ላቸው ፡ ፍላጎታቸውን ፡ እንዲፈጽሙ ፡ ወላጆች ፤ ልጆቻቸውን፡ መረን፡ በመልቀቃቸው ፤ ልጆች ፡ ከወላጆቻቸው ፡ ቍጥጥር፡ ውጪ ፡ ሆነዋል።

በትምህርት ፡ ቤት ፡ ያሳለፍኩትን ፡ ዘመን ፤ እናንተ ፡ በወሰናች ሁብኝ ፡ ቅጣት ፡ ውስጥ ፡ ሆኜ ፡ እስቤዋለሁ። ከሀገራችን፡ ወደ፡ሌላው፡ ሀገር ፡ የሄድነው ፡ ጥበብን ፡ ለመቅሰም ፡ መሆኑን ፡ ማስረዳት ፡ አያስ ፈልግም ። በአዕምሮ ፡ ዕውቀትና ፡ በዕድሜ ፡ ሳይበስሉ ፡ መሄድ ፡ ረግ ረግ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ እንደመዋጥ ፡ የሚቈጠር ፡ ነው ።

ብዙ ፡ ወላጆች ፡ ልጆቻቸውን ፡ ውጪ ፡ ሀገር ፡ ልከው ፡ ከፊታቸው ፡ ገለል ፡ ማድረጋቸውንና ፡ በተስፋ ፡ መጠበቃቸውን ፡ እንደ ፡ ታላቅ ፡ አድራጎት ፡ ቈጥረውታል ። ከሥፍራው ፡ ድረስ ፡ ሄዶ ፡ ያየ ፡ አይመኘውም ። ከኔና ፡ እኔን ፡ ከመሳሰሉ ፡ ምን ፡ ይፈለጋል ። የጐደለ ውንና ፡ የሚፈለገውን ፡ ካወቅን ፤ የማይጠቅመውን ፡ ተወት ፡ አድር ገን ፤ የሌለው ፡ እንዲኖር ፤ የጐደለው ፡ እንዲሟላ ፡ ማድረግ ፤ የኛ ፡ የዘ መኑ ፡ ትውልድ ፡ ፈንታ ፡ መሆኑን ፡ ማስተዋል ፡ ነው ፡ በበለጠ ፡ የጐ ደለን ።

ለአጭርም ፡ ሆነ ፡ ረዘም ፡ ላሉ ፡ ዓመታት ፡ ሰው ፡ ከኖረ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ያያል ። ይሁንና ፡ ሁለት ፡ አካሎች ፡ በአስተሳሰብ ፡ አልተገና ኙም ። ዓለም ፡ የደረሰበትን ፡ ዓይተናል ፡ የሚሉ ፤ እንዳየነው ፡ ይሁን ፡ ቢሉም ፤ ላላዩት ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ስሜት፡ አይሰጥም። የሰዎችን ፡ሥራ፡ ማየት ፡ የራስን ፡ በራስ ፡ ለመናቅ ፡ አይደለም ። ተቆጭቶ ፡ ራስን ፡ በራስ ፡ ወደ፡ማስቻል፡ ደረጃ ፡ ለማድረስ ፤ ሐሳብን፡ ለሥራ፡ መቀስቀስ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ሳይሠሩ ፡ ለምን ፡ እኛስ ፡ እንደነሱ ፡ አንሆንም ፡ እያሉ ፡ በመቅበጥበጥ ፤ ለሌሎች ፡ ራስ ፡ ምታት ፡ መሆን ፡ ምን ፡ ዋጋ ፡ አለው።

ለመሻሻልና ፡ አሰቡት ፡ ግብ ፡ ለመድረስ ፡ መሠረቱ ፡ ሰላም ፡ ነው ። ከሰላማዊ ፡ ኑሮ ፡ ይልቅ ፤ ጥፋትን ፡ ወልዶ ፤ ከጥፋት ፡ በኋላ ፡ የሚጣለው ፡ መሠረት ፡ ለሀገር ፡ ታላቅ ፡ እድገት ፡ ይሰጣል ፡ ብለው ፡ የሚያምኑ ፡ ይኖራሉ ። የሚያስከትለው ፡ ጉዳት ፡ ግን ፡ ዘወትር፡ አዲስ፡ ቤት ፡ ሠሪ ፡ እያደረገ ፤ ከመኖር ፡ በቀር ፡ ዘለቄታ ፡ ውጤት ፡ እንደሌለው ፡ አለማስተዋል ፡ ነው ። ጥፋት ፤ ጥፋትን ፡ ሲወልድ ፡ ዓለም፡በበኩልዋ ፡ ቁና ፡ ሰፋሪ ፡ ስለሆነች ፤ ዛሬ ፡ ከተሟላላት ፡ ጋር፡ ትዘፍናለች፡ ያንን ፡ ትታ ፡ በማግሥቱ ፡ ሌላውን ፡ ትከተላለች ። የሰው ፡ ልጆች ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ቴያትር ፡ ሆነው ፡ ይታያሉ።



መሻሻል ፡የነበር ፡ ነው ። አሁንም ፡ ያለ ፡ ነው ፤ ወደፊትም፡ የሚኖር ፡ ነው ። መሠረቱን ፡ እንደያዙ ፡ ወይም ፡ እንደጨበጡ ፡ የሚደረግ ለውጥ ፡ መሠረታዊ ፡ አቅዋም ፡ ይኖረዋል ። ቁም ፡ ነገሩ ፡ ይህ፡ሲሆን፡ ዘመን ፡ የሚያነሣቸው ፤ በራሳቸው ፡ ስሜት ፡ ብቻ ፡ እየተጓዙ ፤ አምባገነን ፡ በሆነ ፡ አነሣሥና፡ ሥልጣን ፤ ያንንም፡ ልያዘው ፡ እያሉ ፡ በጀአግራሬ ፡ ከተወሰነላቸው ፡ ሀገር ፡ አልፈው፡ ግዛት፡ እናስፋፋለን፡ብለው፡ ሲሮጡ ፤ የራሳቸውን ፡ ጭምር ፡ አጥተው ፡ ለሕዝብ ፡ መቅሠፍት ፡ ይሆናሉ ፡ ስትል ፡ አስረዳችን ።

ልጄ ፤ ካንቺ ፡ ቀደም ፡ ብለን ፡ በዚህች ፡ ዓለም ፡ የተገኘነው ፡ እስከዚህ ፡ ጠልቀን ፡ ያላስተዋልነውን፤ ከኛ ፡ አብራክ ፡ ትናንት ፡ የተገኘሽው ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ጠለቅ ፡ አድርገሽ ፡ የተመራመርሽው ፤ በመማርሽ ፡ ስለሆነ ፤ በአነጋገርሽ ፡ ልባችን ፡ ተነካ ።

ኧረ ፡ ለመሆኑ ፤ አንቺ ፡ እንደዚህ ፡ ጠለቅ ፡ ያለ ፡ አስተያየት ፡ እንዳለሽ ፡ ሁሉ ፤ እንዳንቺ ፡ ያሉ ፡ ሌሎችም ፡ ይኖሩ ፡ ይሆን ?

አዬ ፡ አባባ ፤ ከራስ ፡ ጸጉር ፡ የበዙ ፡ አሉ ። ምን ፡ ይሆናል ፤ ጠለቅ ፡ አድርገው ፡ ባለመመርመራቸው ፡ ቁምነገሩን ፡ ትተው ፡ ከንቱውን ፡ ይከተላሉ። ታሪክ ፡ ዘመናትን፡ እየተከተለ ፡ በዘመናት ፡ የሚሠሩትን ፡ ይመዘግባል ። ያለፈው ፡ በዘመኑ ፡ ካለው ፡ ጋር ፡ ሲመዛዘን ፤ ልዩነት ፡ ይገኝበታል ፡ አለችን ።

ልጃችን ፡ በመልካም ፡ በመመራቷ ፡ ተደስተን ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ እንድትመለስና ፡ በዕውቀቷ ፡ አገሯን ፡ እንድታገለግል ፡ ላክናት ። ከሥልጣኔ ፡ የተቀዳ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ በአጓጉል ፡ አኗኗር ፡ ላይ ፡ የሚገኙትን ፡ ጓደኞችዋን ፡ ለመመለስ ፡ ጣረች ።

ጥራም ፡ አልቀረች ፤ ለጓደኞችዋ ፡ ከሥልጣኔ ፡ የተገኘ ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ የያዝኩትን ፡ ተወዳጅ ፡ አባትና ፡ እናቴ ፡ እንድተው ፡ በነገሩኝ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ከፋኝ ። ሆኖም ፡ ተግሣጻቸው ፡ በላዬ ፡ ላይ ፡ ወረደ ። ከመስማት ፡ በቀር ፡ መናገር ፡ አልቻልኩም ። በቍጥጥራቸው ፡ ሥር ፡ ወደቅሁ ። ራሴን ፡ በራሴ ፡ ማዘዝ ፡ ቀርቶ ፤ በነርሱ ፡ ትእዛዝ ፡ ብቻ ፡ እንድመራ ፡ ተገደድኩ ። መሥራትም ፡ ግድ፡ ሆነብኝ ። ለጊዜው፡ ይከፋኝ፡ እንጂ ፤ እያደረ ፡ ሥራው ፡ ጣመኝ ። የወላጆች ፡ ተግሣጽ፡ ለራሴ ፡ መሆኑን ፡ አስተዋልኩ ። ትሕትና ፡ በተመላ ፡ አኳኋን ፡ ራሴን ፡ ዝቅ ፡ በማድረግ ፤ ወላጆቼን ፡ ለማስደሰት ፡ በጣም ፡ ተጣጣርኩ ።

በይዞታዬ ፡ እየተገረሙ ፤ የተሰማቸውን ፡ ውስጣዊ፡ ደስታ፡ከቀን፡ ወደ ፡ ቀን ፡ በፊታቸው ፡ ሳነብ ፤ እኔም ፡ ደስ ፡ አለኝ ፤ በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ሳለን ፤ በኔ ፡ መሻሻል ፡ ምኞታቸው ፡ ሁሉ ፡ መፈጸሙን ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ዘርዝረውልኝ ፡ የሚያስፈልገኝን ፡ አዘጋጅተው ፡ ላኩኝ ፡ ብላ ፡ ለጓደኞቿ ፡ የገለጠችላቸውን ፡ ምክር ፡ ጽፋ ፡ ላከችልን ።

የቀለም ፡ ጓደኛ ፡ ሆነው ፤ ለረዥም ፡ ጊዜ ፡ አብረው ፡ ያደጉ ፡ ከመ ሆናቸው ፡ ይልቅ ፤ መተሳሰብ ፡ በመካከላቸው ፡ የኖረ ፡ በመሆኑ ፡ ሐሳ ብዋን ፡ ከምስጋና ፡ ጋር ፡ እንደተቀበሉዋትም ፡ ጨምራ ፡ ገለጠችልን ።

ኅብረተሰቡ ፡ የጠላውንና ፡ የሚጠላውን ፡ ራሳቸው ፡ ከመተዋቸ ውም ፡ በላይ ፤ መሰሎቻቸውን ፡ እያስረዱ ፡ ለመመለስ ፡ የሚያደርጉ ትን ፡ ጥረት ፡ ቡርከት ፡ በደብዳቤ ፡ በገለጸችልን ፡ ጊዜ ፡ ምክራችን ፡ ፍሬ ፡ በማፍራቱ ፡ በበለጠ ፡ ደስ ፡ አለን ።

## መርዶ ፡

በወላጅ ፡ እናቴ ፡ ናፍቆት ፡ ተንገብግቤ ፤
እየባባ ፡ ሆዴ ፡ ይሸበራል ፡ ልቤ ።

የጆሮዬን ፡ ታምቡር ፡ ድንገት ፡ እየመታ ፤
ሞታለች ፡ እናትሽ ፡ ጠያቂ ፡ ልጅ ፡ አጥታ ፤
አድሮብኛል ፡ የሚል ፡ የመንፈስ ፡ በሽታ ።

በተድላ ፡ ደስታ ፡ ተንቀባራ ፡ ኖራ ፤
ሲጠፋ ፡ አይታወቅ ፡ የዓለም ፡ አዝመራ ።

አብዛኛውን ፡ ዘመን ፡ የኖረችው ፡ ካንድ ፤
ቀረና ፡ ያ ፡ ሁሉ ፡ እገዳም ፡ መሔድ ።

የነበረች ፡ ስታዝዝ ፡ ሙሉ ፡ ቤተሰብ ፤
ቀረበች ፡ ራሷ ፡ ለማገልገል ፡ ሕዝብ ።

ነበር ፡ የኖረችው ፡ በመለሳለስ ፤
ወፍጮ ፡ ፈጭ ፡ ሆነች ፡ ጥራጥሬ ፡ ገብስ ።

የሠራችው ፡ ሥራ ፡ የፈጸመችው ፤
ከቅዱሳት ፡ እንስት ፡ የሚደመር ፡ ነው ።



እያለ ፡ መንፈሴ ፡ ይጽናናል ፡ በራሱ ፤
አለውና ፡ ፍሬ ፡ ያደገ ፡ አሳብ ፡ ፅንሱ ።

ሞተች ፡ ያልኩ ፡ እናቴን ፡ በግምት ፡ ነበረ ፤
መች ፡ ይቀራል ፡ መርዶው ፡ ሰው ፡ ከተቀበረ ፤
ይኸውና ፡ መጣ ፡ በሐሳብ ፡ አልቀረ ።

ይግባ ፡ መልእክተኛው ፡ እንጠይቀው ፡ ወሬ ፤
አወጣለሁ ፡ ርሜን ፡ ብዬ ፡ ተናግሬ ።

ዋለለ ፡ ልባችን ፡ ተንዶ ፡ ተንዶ ፤
ግድ ፡ የለም ፡ ይረጋል ፡ በምንሰማው ፡ መርዶ ።

ተላላው ፡ ሰው ፡ ሞኙ ፡ ለሞት ፡ ያለቅሳል ፤
የሚያየው ፡ ሰው ፡ ቆሞ ፡ ቅርጹ ፡ ምን ፡ ይመስላል ።

የሞተውስ ፡ ሞተ ፡ ነፍሱን ፡ ይማረው ፤
ይታያል ፡ በምን ፡ ላይ ፡ በሕይወት ፡ ያለው ።

ሕይወት ፤ ሕይወት ፡ ሲባል ፡ ቀላል ፡ ይመስላል ፤
እንዳይጠፋ ፡ ሕይወት ፡ ይኑር ፡ መሰላል ።

የሕይወት ፡ መሰላል ፡ እውታሩ ፡ ምንድንነው ?
ማለት ፡ ለኔ ፡ ትቶ ፡ ለኛ ፡ ማለቱ ፡ ነው ፤
ያለውም ፡ ለሌለው ፡ እጁን ፡ መዘርጋት ፡ ነው ።

በብቸኛ ፡ ኑሮ ፡ ራስን ፡ መውደድ ፤
ይቅር ፡ አያዋጣም ፡ ያስከትላል ፡ ጉድ ።

ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፤ ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ ጣጣ ፤
እንኑር ፡ ተሳስበን ፡ ሰላምን ፡ እናምጣ ።

---

## ክፍል ፣ ፲፡

# የቡርክትና ፡ የዕምላዕሉ ፡ ጋብቻ ፡

በአክብሮትና ፣ በፍቅር ፣ የሚመለከቱንን ፣ እናቶቻችንን ፣ ከአ ጣን ፣ በኋላ ፤ አስተሳሰባችን ፣ ለራሳችንና ፣ ለልጆች ፣ ብቻ ፣ ሆነ ።

በመካከላችን ፣ የሚታየው ፣ የተቀደሰ ፡ ፍቅር ፤ ጊዜ ፣ የማይለው ጠው ፤ ዘወትር ፡ የጋለ ፣ ሆኖ ፣ በመታየቱ ፤ በፍቅር ፣ የሚመለከቱን ፣ ደስ ፣ ሲላቸው ፤ በጥላቻ ፣ ለሚያዩን ፣ የቅናት ፣ ቅንቅን ፣ ያዛቸው ።

የፍቅር ፡ ባለቤት ፣ በመካከላችን ፣ ስላለ ፤ ጊዜ ፣ ሳይለውጠው ፤ ትዳራችንን፣ እያስፋፋን ፣ ስንኖር ፤ ከአብራካችን፣ የተከፈሉት፣ ልጆች፣ አደጉ። በትምህርትም ፣ ከተፈጥሮ ፣ ጓደኞቻቸው ፣ አላነሱ ። ቡርክት ፣ ትዳር ፣ ባለመያዟ ፣ ሐሳብ ፡ አደረብን ፤ ከዕለታት ፣ አንድ፣ ቀን፣ ይህንኑ፣ አንስተን ፣ ስንጨዋወት ፤ የበኵር ፣ ልጃችን፣ ትዳር ፣ ባለመያዟ ፣ ባላዝ ንም ፣ ቅር ፣ ሳይለኝ ፣ አልቀረም ፤ ሴት ፣ ልጅ ፣ ለአቅመ ፡ ሔዋን ፣ ከደ ረሰች ፡ ትዳር ፡ መያዝ ፣ ይገባታል ። ሰው ፣ በሰው ፣ ይስታል ፤ ሰው ፣ ናትና ፣ ከዕለታት ፣ አንድ ፣ ቀን ፣ ከስሕተት ፣ ላይ ፡ ትወድቃለች ፣ ብዬ፡ ማሰቤ ፣ አልቀረም ፣ ከቶ ፣ ምን፣ ይሻል ፣ ይሆን ? ዘጠኝ ፣ ወር፣ አርግዤ፣ በምጥ ፣ ከወለድኳት ፣ የበለጠ ፣ ምጥ ፣ ይዞኛል ፣ ብላ ፣ አዋየችኝ ፣ ፀሐይ ።

በሐሳቤ ፡ የተቋጠረውን ፣ ፈታሽው ፤ በአሁኑ ፣ ዕድሜዋ ፣ ልጃችን፣ ባል ፣ አግብታ ፣ ባለትዳር ፣ ባለመሆኗ፣ እኔንም ፣ አሳስቦኛል ። በወግ ፣ በማዕርግ ፤ ሥርዓተ ፡ ጋብቻ ፣ ሳትፈጽም ፣ ብትደፈር ፣ ዕድሏ ፣ ተሰበረ፣ ማለት ፣ ነው ።

ወላጅ ፣ በልጆቹ ፣ ላይ ፣ ያለበት ፣ ኃላፊነት ፣ የተወሰነ ፣ ደረጃ ፣ የለውም ። ከተወለዱበት ፣ ቀን ፣ ጀምሮ ፤ በሰውነት ፣ ብቻ ፣ ማሳደግ ፣ ሳይሆን ፤ በዕውቀት ፣ አጐልምሶ ፣ ለማሳደግ ፣ ያለው ፣ ጥረት ፤ ከትምህ ርት ፣ በኋላ ፣ ሥራና ፣ ትዳር ፣ ለማስያዝ ፣ ያለው ፣ አስተሳሰብ ፣ ቀላል ፣ አይደለም ። አሁን ፣ በልጃችን ፣ ላይ ፣ የቀረን ፤ መልካም ፣ አቅዋም ፣

ያለው ፡ ትዳር ፡ ይዛ ፡ ማየት ፡ ነው ፡ አልኳት ።

እስተያየቴን ፡ ከአዳመጠች ፡ በኋላ ፡ አብርሃም ፡ ለይስሐቅ ፡ ሚስት ፡ የምትሆነውን ፡ እንዲሰጠው ፡ ፈጣሪውን ፡ በጸሎት ፡ ቢያስ በው ፤ ርብቃን ፡ የመሰለች ፡ የደግ ፡ ዘር ፡ ሰጠው ። በአጠቃላይ ፡ ስንና ገር ፤ የቤተሰብን ፡ ኑሮ ፡ የቀደሰ ፡ ማነው ? ሁሉንም፡ በእምነት፡ ለርሱ፡ እንተወው ፡ ስትል ፡ እምነቷን ፡ በፈጣሪዋ ፡ ላይ ፡ ጣለች ፡ ፀሐይ ።

ከአብራካችን ፡ የተከፈሉት ፡ ልጆቻችን፡ በአቀዋም፡ ሰው ፡ ቢሆኑ፡ ሰው ፡ የሚያስኛቸውን ፡ ጠባይ ፡ ይዘው ፡ እንዲገኙ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምኞ ትና ፡ ሐሳብ ፡ ስላለን ፡ ዘወትር ፡ እያነሣን ፡ እንወያያለን። በአደባባይ፡ እንደመዋሌ ፡ ብዙ ፡ ዐያለሁ ፡ እሰማለሁ ። ፀሐይና ፡ ጨረቃ ፤ ብርሃ ንና ፡ ጨለማ ፤ ክረምትና ፡ በጋ ፡ የተፈጥሮ ፡ ግዴታቸውን ፡ ባለማቋ ረጥ ፡ ይሠራሉ ። ለሰውም ፡ ከተሰጠው ፡ አካሉ ፡ ዓይን፡ ያያል ፤ ጆሮ፡ ይሰማል ፤ አዕምሮ ፡ ያስባል ። ሰውነቴን ፡ ንቃ ፡ አድርጌ ፡ ሳዳምጥ ፡ መልካም ፡ ቤተሰቦች ፡ ልጆቻቸውን፡ በሥርዓት ፡ ለማሳደግ፡ ቢጥሩም፡ ምን ፡ ዋጋ ፡ አለው ! ምን ፡ ዋጋ ፡ አለው ! ምን፡ ዋጋ ፡ አለው ! ብለው፡ በኀብረት ፡ ተናገሩ ።

እንዴት ፡ ነው ፡ በልጆች ፡ አስተዳደግ ፡ ላይ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ የተ ባበረ ፡ ሐሳብ ፡ የተናገሩት ፡ ብዬ ፡ በንቃት ፡ ማዳመጤን ፡ ቀጠልኩ ። ልጆች ፡ የሚውሉት ፡ በሺ ፡ ከሚቈጠሩ ፡ ጋር፡ ነው። እንደብዛታቸው ፡ ጠባያቸው ፡ የተለያየ ፡ ከመሆኑም ፡ ይልቅ ፤ ልዩ፡ ልዩ ፡ ጠባይ፡ ከውጭ፡ ይቀስማሉ ። የሚወደደውንና ፡ የሚጠላውን ፡ ሳይለዩ ፤ ሁሉንም ፡ አግ በስብስው ፡ በጀርባቸው ፡ አዝለው ፡ እሹሩሩ ፡ ይሉታል ።

እናት ፡ ልጅን ፡ እሹሩሩ ፡ የምትለው ፡ ለተወሰነ፡ ዓመታት፡ ነበር፤ የነዚህ ፡ ዘመን ፡ የማይወስነው ፤ ከአንዱ፡ ጀርባ ፡ ሲወርድ፡ ወደ ፡ አንዱ፡ ጀርባ ፡ የሚተላለፍ ፡ የዘመኑ ፡ በሽታ ፡ ሁኗል ።

ሰው ፡ እንዴት ፡ የራሱን ፡ ጠልቶ ፡ የሰውን ፡ ብቻ ፡ ይወዳል ? ዓለም ፡ ቅጂ ፡ ነው ። የሌለውን ፡ ይቀዳል ፡ እንጂ ፡ እንዴት፡ ያለውን፡ ይተዋል ። የራስን ፡ ተውሕቦ ፡ ለመስጠት፡ መጣርስ ፡ እንዴት ፡ ይቅር፡ እያሉ ፡ በሰፊው ፡ ተነጋገሩ ።

በመሸጋገሪያ ፡ ዘመን ፡ ላይ ፡ የሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ጥሩና ፡ ግርዱን ፡ አይለይም ። ሥራው ፡ ሁሉ ፡ የተበጣበጠና ፡ የተመሰቃቀለ ፡



ሆኖ ፤ የሰውን ፡ አዕምሮ ፡ ይበጠብጣል ። አባቶች ፡ ሲተርቱ፡ «ራሱን፡ የማይችል ፡ እንገት ፡ የለም ፡» ከባዱንም ፡ ሆነ ፡ ቀላሉን ፡ አብሮ ፡ የተ ፈጠረው ፡ እንገት ፡ ይሸከማል ። አዕምሮ ፡ ለማመዛዘን ፤ እንገት፡ የተፈ ጠረው ፡ ራሱን ፡ ከመሸከሙም ፡ በላይ ፡ አዙሮ ፡ ለማየት ፡ ነው ።

በዘመናት ፡ ብዛት ፡ ነፃነት ፡ አጥተው ፡ የኖሩ፡ ሕዝቦች ፤ በጠላት፡ አገዛዝ ፡ ብዙ ፡ ትውልድ ፡ አሳልፈው ፤ በሺህ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ዘመናት ፡ ያላነፃነት ፡ ኑረው ፤ ተስፋ ፡ ባለመቍረጥ ፤ ባደረጉት፡ ትግል፡ በነፃነት፡ የሀገራቸው ፤ የምድሩዋና ፡ የአፈርዋ ፡ ባለቤት ፡ ሲሆኑ ፡ የዘመናት ፡ ብዛት ፡ከሥር ፡ ከመሠረቱ ፡ ያጠፋውን ፡ ባህልና ፡ ልማድ ፤ እንደገና ፡ መሥርተው ፡ ለመኖር ፡ ይታገላሉ ፡ አለ ፡ አንዱ ፡ ከመካከላቸው ።

ሌላው ፡ ደግሞ ፤ እኛ ፡ የምንወያይበትን ፡ ሁሉም ፡ በግለት ፡ ይና ገረዋል ። ታዲያ ፡ ሁሉ ፡ ተናጋሪ ፡ ሆነ ፡ እንጂ፡ ለበሽታው፡ መፍትሔ፡ ያገኘ ፡ የለም ።

ኅብረተሰቡ ፡ የሚጠቅመውንና ፡ የሚጐዳውን ፡ ለይቶ ፤ በእግሩ፡ ለሚተካው ፡ ትውልድ ፡ ካላስተላለፈ ፤ ከራሱ ፡ የበለጠ ፡ ሌላው ፡ ያስ ብልኛል ፡ ብሎ ፡ በዝምታና ፡ በትዝብት ፡ እየተመለከተ ፡ አንዱ ፡ በአ ንዱ ፡ ላይ ፡ ቢያሳብብ ፡ በታሪክ ፡ ፊት ፤ ነፃነት ፡ አያገኝም ።

ካልሠራ ፡ የዕለት ፡ ምግብና ፡ ልብስ ፡ ከማንም ፡ እንደማያገኝ ፡ የሚያውቅ ፤ የሚጠቅመውንና፡ የማይጠቅመውን ፡ ለይቶ፡ አያውቅም፡ ለማለት ፡ አይቻልም ። እያንዳንዱ ፡ ራሱን፡ ወድዋልና ፡ ለታሪክ፡ ምን ያቆይ ፡ ይሆን ? አላቸው ። እኔም ፡ የዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ለካ ፡ ሁሉንም ፡ አሳ ስቧል ፡ የሚል ፡ መንፈስ ፡ አሳደረብኝ ። ሰዎች ፡ የተለዋወጡትን ፡ ሐሳብ ፡ በዝምታ ፡ ያዳመጥክ ፡ ከሆነ ፡ መልካም ፡ ነው ። ለመስማት ፡ መቸኰል ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ለመናገር ፡ መቸኰል ፡ አይጠቅምም ። ለሰ ሙትም ፡ ሁሉ ፡ መልስ ፡ አይሰጥም ።

እስከዚህ ፡ መነጋገር ፡ የደረስነው ፡ በልጆችን ፡ ትዳር፡ አለመያዝ፡ ነው ። ዕድሏ ፡ የሚጠብቃትን ፡ በተስፋ ፡ እንጠብቅ ፡ እንጂ ፤ በኛ ፡ አስ ተሳሰብ ፡ ለማይቃናው ፡ እንድከም ፡ እንዳለች ፡ ፀሐይ ፤ እንግዶች ፡ መጥተዋል ፡ አለ ፡ አሽከር ፤ ይግቡ ፡ አልንና ፡ ገቡ ። ከአንዱ ፡ ጋር ፡ የቅርብ ፡ ዕውቀት ፡ ስላለን ፤ ሰላምታ ፡ ተለዋወጥን ። ፀሐይም ፡ ከእንግ ዶቹ ፡ ጋር ፡ ተዋውቃ ፤ እንደወይን ፡ የጠራ ፡ ጠላና ፤ እንኮይ ፡ የመሰለ ጠጅ ፡ አቀረበች ።

እንግዶቹ ፡ ከመጋበዛቸው ፡ በፊት ፡ የመጡበትን ፡ ለመግለጥ ፡ ብድግ ፡ አሉ ። በመገባበዝ ፡ ደቂቃዎች ፡ አለፉ ። በመጨረሻም ፡ ልጃችንን ፡ በሚስትነት ፡ የፈለጋት ፡ ሰው ፡ ለአማላጅነት ፡ እንደላካቸው ፤ የማን ፡ ልጅ ፡ እንደሆነ ፡ ዘሩን ፡ ሳይቀር ፡ ዘርዝረው ፡ ነገሩን ።

ዓይን ፡ ለዓይን ፡ ከፀሐይ ፡ ጋር ፡ ተያየን ። ልጃችን ፡ በዕድሜ ፡ የገፋች ፤ በዕውቀት ፡ የበሰለች ፡ ስለሆነ ፤ በበኩላችን ፡ እናጥናው ፤ ርስዋንም ፡ እንጠይቅ ፡ አልናቸው ።

በበኩላችሁ፡ ማጥናታችሁን ፡ እንወዳለን ። የርስዋንም ፡ ሐሳብ ፡ ማወቅ ፡ የበለጠ ፡ የሚወደድ ፡ ነው ። መልሱን ፡ ለመቀበል ፡ ቀጠሮ ፡ ስጡን ፡ አሉና ፡ በቀጠሮ ፡ ተለያየን ።

የቡርክት ፡ ትዳር ፡ አለመያዝ ፡ አሳስቦን ፡ በምንወያይበት ፡ ሰዓት ፤ አማላጆች ፡ በመምጣታቸው ፡ ተገርመን ፡ ስንወያይ ፤ የርስዋን፡ ስምምነት ፡ ሳያገኙ ፡ አልጠየቁንም ። ስምምነቱ ፡ ከርስዋ ፡ ያለ ፡ ይመስለኛል ። ለምን ፡ ያልክ ፡ እንደሆነ ፤ ርስዋ ፡ ፈረንጅ ፡ ሀገር ፡ ድረስ ፡ ሄዳ ፡ ተምራለች ። በሚስትነት ፡ የፈለጋት ፤ ሰውም ፡ ጠባዩንና ፡ የተፈጥሮ ፡ ዕውቀቱን ፡ አላውቅም ፡ እንጂ ፤ በትምህርቱ ፡ ይሀን ፡ ያሀል ፡ የገፋ ፡ አይመስለኝም ፡ አለች ፡ ፀሐይ ።

ያም ፡ አለ ፡ ያ ፡ ያልሽው ፡ ትክክል ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። ልጃችን ፡ ተስማምታ ፡ እንድንጠየቅ ፡ አድርጋ ፡ እንደሆነ ፡ በአድናቆት ፡ አመሰግናታለሁ ። የውጪውን ፡ ዓለም ፡ ያየ ፡ እያዳቀለ ፡ የውጪ ፡ ቋንቋ ፡ መናገር ፡ የሚችል ፡ በማግባት ፡ ፋንታ ፤ ይህን ፡ የመረጠችበት፡ ምክንያት ፡ ይኖራት ፡ ይሆናልና ፡ እንሰማዋለን ፤ መልእክተኛ ፡ እንላክና ፡ ቡርክት ፡ ትምጣ ፡ ተባባልን ።

መልእክተኛው ፡ ሄደ ። ቡርክት ፡ መልእክተኛውን ፡ በሥርዓት ፡ ተቀብላ ፤ በማስተናገድ ፡ ከእነጋገረችው ፡ በኋላ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ባልበለጠ ፡ ጊዜ ፡ እንደምትመጣ ፡ መልሱን ፡ ይዞልን ፡ መጣ ።

ቡርክት ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ከተፍ ፡ አለች ። በናፍቆት ፡ ተቀበልናት። ስለፈለግናት ፡ ጉዳይ ፡ ከመንገራችን ፡ በፊት፡ ስለከተማ ፡ኑሮ፡ ጠየቅናትና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ባህላዊ ፡ ጠባይ፡ እንደተመረዘ፡ ገለጸችልን። ለጥንቱ ፡ ባህልና ፡ ልማድ ፡ ግዴለሽ ፡ ሆኖ ፡ ከሌሎች ፡ በተወረሰ ፡ ባህ



ልና ፡ ልማድ ፡ ለመጠቀም ፡ ይጥራል ። ቀስ ፡ በቀስ ፡ ኃይሉ ፡ እየጠነከረ ፡ ብሔራዊውን ፡ ባህልና ፡ ልማድ ፡ ሊለውጠው ፡ ምንም ፡ አልቀረው ።

ብሔራዊ ፡ ቋንቋችን ፡ ሰፊ ፡ ነው ። በስፋት ፡ የተመሠረተው ፡ የሀገሪቱ ፡ ዋና ፡ ቋንቋ ፡ እየተጣበበ ፡ በሥፍራው ፡ ሌላ ፡ ይተካል ። የሚያኰራን ፡ ቋንቋችን ፡ መሠረቱ፡ እየጠበቀ፤ ከጥንታዊነት፡ ወደ ፡ ዘመናዊነት ፡ የሚራቀቅበትን ፡ መንገድ ፡ ማን ፡ ይሆን ፡ የሚከፍተው ? በአንድ ፡ የትውልድ ፡ ዘመን ፡ ያልነበረው ፡ እንደነበረ ፤ የነበረው ፡ እንዳልነበር ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ።

ሐኪሞች ፡ በሕመምተኛ ፡ ላይ ፡ የሚጠበቡት ፡ በሽታውን ፡ እስኪያውቁት ፡ ድረስ ፡ ነው ። በሽታውን ፡ ካወቁ ፤ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መድኃኒት ፡ ሕመምተኛውን ፡ ከቀሳፊ ፡ በሽታ ፡ ለማዳን ፡ ይጥራሉ ።

ለጠቅላላው ፡ አቋም ፡ የማይጠቅም ፤ እስኪታወቅ ፡ ይጐዳ፡ እንጂ፡ ከታወቀ ፡ አንዱ ፡ በአንዱ ፡ እያመካኘ ፡ ለጉዳዩ ፡ የሚበጀውን ፡ ካለማድረግ ፡ መቆጠብ ፡ ለምን ፡ እንደሆነ ፡ ፍችውን ፡ ያወቀ ፡ ያለ ፡ አይመስለኝም ፡ አለችን ፡ ቡርክት ።

ልጄ ፡ በግለ ፡ ሰብም ፤ ሆነ ፡ በጥንድ ፤ በየሥፍራው ፡ ንግግር ፡ ብቻ ፡ ሆነ። ጠቅላላው ፡ ኅብረተሰቡ ፡ ጉዳቱም ፤ ጥቅሙም ፡ የጋራው ፡ እንጂ ፤ ነገ ፡ የሚመጣው ፡ አንተን ፡ ወይም ፡ እኔናተን ፡ ብሎ ፡ የሚያልፍ ፡ እንደሌለ ፡ ይወቅ ። ለበሽታው ፡ መድኃኒት ፡ በመፈለግ ፡ ፋንታ፡ በዳር ፡ ቆሞ ፡ እየታዘበ ፤ በራሱ ፡ ላይ ፡ ይፈርዳል ። ልጄ ፡ ይህን ፡ ጠለቅ ፡ ብለን ፡ ስንመለከተው ፤ ነቢዩ ፡ ቅዱስ ፡ ዳዊት ፡ በትንቢት ፡ የተናገረው ፡ በዘመናችን ፡ መፈጸሙ ፡ ይሆን ? «ዓይን ፡ አላቸው ፡ አያዩም ፤ ጆሮ ፡ አላቸው ፡ አይሰሙም ፤ አፍንጫ ፡ አላቸው ፡ አያሸቱም ፤ እጅ ፡ አላቸው ፡ አይዳስሱም ፤ በጉሮሮዋቸው ፡ አይናገሩም » ያለውን፡ ሳነብ ፤ ይገርመኛል ፡ አለች ፡ ፀሐይ ።

ቡርክት ፡ እማማ ፡ አለችና ፤ ሐሳባችንን ፡ ወደሌላ ፡ አቅጣጫ ፡ እንምራው ፤ እስካሁን ፡ ያደረግነው ፡ ንግግር፡ ስፋቱ ፡ እንደውቅያኖስ፡ ባሕር ፡ ነው ። እንተወው ፡ ብትላት ፤ ልጄ ፡ ሁሉም ፡ እንደዚሁ ፡ እንተወው ፡ እያለ ፡ ነው ፡ ከዚህ ፡ የደረሰው ። ምርጫ ፡ ሲታጣ ፡ በውድ ፡ ሳይሆን ፡ በግድ ፡ ይተዋል ፡ አለቻት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ለቡርክት ፤ ልጇ ፤ የፍኖረትን ፡ አመጣጥ ፡ በሥነ፡ ፍጥረት ፡ ተምረሽዋል ።

አዳምና ፡ ሔዋን ፡ ተፈጠሩ ። የነርሱ ፡ ዘር ፡ ዛሬ ፡ ዓለምን ፡ አልብ ሷል ። ለወላጆቻችን ፡ አንድ ፡ የሆን ፤ በመካከላችን ፡ ብዙዎች ፡ ፍሬዎች ፡ ተገኘችሁ ። በዚህ ፡ ብቻ ፡ አይቆምም ፤ አንቺም ፡ ትበዢ ለሽ ። ሌሎችም ፡ ይቀጥላሉ ። በዚህ ፡ ነው ፡ የእያንዳንዱ ፡ ቤተሰባዊ ፡ ኑሮ ፡ በስፋት ፡ የሚመሠረተው ።

አንቺ ፡ የቤተሰብ ፡ ኑሮ ፡ መሥራች ፡ እናት ፡ እንድትሆኝ ፡ በኑሮ፡ ጓደኛነት ፡ የፈለገሽ ፡ እንድንፈቅድለት ፡ ሽማግሌ ፡ ልኮብናል ፤ የት ዳር ፡ ጓደኛ ፡ እንዲሆንሽ ፡ አማላጅ ፡ የላከብንን ፡ ከነቤተሰቡ ፡ እናው ቀዋለን ። በበኩላችን ፡ ጋብቻውን ፡ ደግፈናል ። ቢሆንም፡የጉዳዩ ፡ ባለ ቤት ፡ ስለሆንሽ ፡ መሠረታዊ ፡ ሐሳቡ ፡ የሚጸድቀው ፡ ያንቺ ፡ ፈቃ ድሽ ፡ ሲሆን ፡ ነው ፡ አልኳት ።

የልጃገረድ ፡ ወግ ፡ ለማድረስ ፡ አፍራ ፤ አባትና ፡ እናቷን ፡ ቀና ፡ ብላ ፡ ሳታይ ፡ ለደቂቃዎች ፡ መሬት ፤ መሬት ፡ እያየች፡ ተከዘች። አባባ፤ እማማ ፤ የኔ ፡ ትዳር ፡ አለመያዝ ፡ እናንተን ፡ በጣም ፡ እንዳሳሰባችሁ ፡ ይሰማኛል ። ሴት ፡ ልጅ ፡ ለአካለ ፡ መጠን ፡ ከደረሰች ፡ በኋላ ፡ ትዳር ፡ ካልያዘች ፡ ወላጆች ፡ ሐሳብ ፡ እንደሚገባቸው ፡ አምናለሁ ።

አስተሳሰቡም ፡ ትክክለኛ ፡ ነው ። በኔ ፡ ዕድሜ ፤ በአደባባይ ፡ የም ትውል ፡ ልጃገረድ ፡ ቶሎ ፡ ትዳር ፡ አለመያዝዋ ፤ እጅግ ፡ አሳሳቢ ፡ የሚ ሆነው ፡ ለወላጆችዋ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፤ ለራስዋም ፡ ጭምር ፡ ነው ።

ሀገር ፡ በትውልድ ፡ እየሰፋች ፡ ምድርዋ ፡ በተወላጆችዋ ፡ የምት መላውና ፤ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሞያ ፡ የሠለጠኑ ፡ ጠቢባን ፡ ሲገኙ ፡ የሚች ሉት ፤ ጤናማ ፡ ከሆኑ ፡ እናቶች ፡ ጤናማ ፡ ልጆች ፡ ሲገኙ ፡ ነው ። ጤናማ ፡ እናቶች ፡ የሚገኙት ፡ ንጽሕናቸውን ፡ የጠበቁ ፡ ልጃገረዶች ፤ ትዳር ፡ ይዘው ፡ እናቶች ፡ ሲሆኑ ፡ ነው ።

አለባበሴን ፡ የሚያይ ፤ ንጽሕናዬን ፡ የጠበቅሁ ፡ ልጃገረድ ፡ አል መስለውም፤ በትምህርት፡ ቤት፡ በነበርኩበት ፡ወቅትና፡ከውጪ ፡ አገር፡ በተመለስኩ ፡ ጊዜ ፡ መሽቀርቀር ፡ ባበዛም ፡ የናንተ ፡ የወላጆቼ ፡ መል ካም ፡ እርአያ ፡ በአእምሮዬ ፡ የተቀረጸ ፡ በመሆኑ ፤ ትዳር ፡ ይዤ ፡ የቤተ ሰብ ፡ ኑሮ ፡ መሥርቼ ፡ ለመኖር ፡ የረኸም፡ ዘመን ፡ ምኞት፡ ስለነበረኝ፡ ጊዜያዊ ፡ ደስታ ፡ ሳያሸንፈኝ ፤ ክብረ ፡ ድንግልናዬን ፡ ጠብቄያለሁ ።



ብዙ ፡ ፈተና ፡ ደርሶብኝ ፡ አሸንፌአለሁ ። ለማያዛልቅ ፡ ዕለታዊ ፡ ደስታ ፤ ራሴን ፡ አላዋረድኩም ። ራሴን ፡ በራሴ ፡ አስከብሬያለሁ ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ከውጪ ፡ አገር ፡ በተመለስኩ ፡ ጊዜ ፡ ፈጥኜ ፡ እናንተ፡ ዘንድ ፡ ባለመምጣቴና ፡ ከተገናኘንም ፡ በኋላ ፡ ሳንጣጣም ፡ ቀርተን ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ ያላችሁ ፡ አስተያየት ፡ የተለዋወጠም ፡ ቢሆን ፤ ለጋብቻ ፡ ያለኝ ፡ ስሜት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ በመሆኑ ፤ ክብረ ፡ ንጽሕናዬን ፡ ጠብቄ ፡ ኖሬያለሁ ።

የትዳር ፡ ጓደኛ ፡ እንዲሆነኝ ፡ የጠየቃችሁ ፡ በቅድሚያ ፡ ጠይቆ ኛል ። አጥንቼዋለሁም ። የቤተሰብ ፡ ኑሮ ፡ ለመመሥረት ፡ የሚበቃ ፡ ሰው ፡ ይሆናል ፡ ብዬ ፡ ተስፋ ፡ አድርጌያለሁ ።

ብዙ ፡ ዓመታት ፡ በውጭ ፡ ዓለም፡ በትምህርት ፡ የቆዩና ፡ እኔም፡ በነበርኩበት ፡ ጊዜ ፡ የነበሩ ፤ ያወቁኝና ፡ ያወቅኋቸው ፤ የትዳር፡ ጓደኛ ፡ እንድሆናቸው ፡ አስቸግረውኝ ፡ ነበር ።

ይሁንና ፡ ጥያቄያቸውን ፡ ልቀበል ፡ አልወደድሁም ። ትዳር ፡ ምን ያህል ፡ ከፍተኛ ፡ ኃላፊነት ፡ እንዳለበት ፤ ይልቁንም ፡ ልጅ ፡ መውለድ ፡ ይመጣል ። ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ የመጣውን ፡ ልጅ ፡ በሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ማሳ ደግ ፡ ኃላፊነቱ ፡ የወላጆች ፡ ነው ። ይህን ፡ በትክክል ፡ የሚያውቁ ፡ ስንት ፡ ናቸው ? እንዲያውም ፡ መውለድና ፡ መዋለድ ፡ የፍጥረታት ፡ ግዴታ ፡ ነው ። የተወለደው ፡ በዕድሉ ፡ ይደግ ፡ ብለው ፡ ስለልጆች ፡ አስተዳደግ ፡ ደንታ ፡ የሌላቸው ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ። የዛሬ ፡ ልጅ ፡ « በዕድሉ ፡ » በሚባል ፡ ስም ፡ ብቻ፡ ሊያድግ ፡ አይችልም ። ጤናውን፡ ተንከባክቦ ፡ ማስተማር ፡ ግዴታ ፡ ሆኗል ።

የኑሮ ፡ ጓደኛ ፡ እንድሆነው ፡ የጠየቀኝን ፤ ጥያቄውን ፡ ተቀብዬዋ ለሁ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ እናንተም ፡ ስትቀበሉት ፡ የትዳር ፡ ጓደኛ ፡ ይሆነ ኛል ።

አንቺ ፡ የተማርሽ ፡ ነሽ ፡ በትምህርት ፡ ካንቺ ፡ ላቅ ፡ ያለ ፤ ወይም ፡ ተወዳዳሪ ፡ የሆነ ፡ እንጂ ፤ እንዴት ፡ ይህን ፡ ታገቢያለሽ ፡ ብለውኛል ፡ ጓደኞቼ ። ይሁንና ፡ ጠባዩ ፡ ከጠባዩ ፡ ተስማሚ ፡ ሆኖ ፡ በትዳር ፡ ከተ ሳሰብን ፤ ርሱ ፡ የማያውቀውን ፡ ከኔ ፡ ይማራል ፤ እኔ ፡ የማላውቀውን፡ ከርሱ ፡ እማራለሁ ።

የዘመኑ ፡ ሰዎች ፡ አምነው ፡ የተቀበሉት ፤ የዕውቀት ፡ መለኪያ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ አይኑረው ፡ እንጂ ፤ ለማወቅ ፡ ባደረገው ፡ ትጋት፡

አስተዋይ ፡ ሆንዋል ። ሳነጋግረው ፡ አስተሳሰቡና ፡ አስተያየቱ ፤ ተም ረናል ፡ ብለው ፡ ከሚመኩት ፡ የበለጠ ፡ ግምት ፡ የሚሰጠው ፡ ሆኖ ፡ አግኝቼዋለሁ ። እንኳን ፡ እኔ ፡ ልበልጠው ፤ እኔ ፡ ከርሱ ፡ የምማረው ፡ ይኖራል ። በመሠረቱ ፡ እናንተ ፡ ከተቀበላችሁት ፡ በበኩሌ ፡ ተቀብዬ ዋለሁ ፡ አለችኝ ።

ውዲቱ ፡ ልጃችን ፡ በውነትም ፡ ተምረሻል ። ሌሎች ፡ የተከተሉ ትን ፡ ሳትከተይ ፡ የሚስማማሽን ፡ በመምረጥሽ ፡ ከልብ ፡ ነው ፡ የመረ ቅንሽ ፡ ሐሳብሽና ፡ ሐሳባችን ፡ ከተጋጠመ፤ ሠርጋችሁ ፡ መቼ ፡ ቢሆን ፡ ትወጃለሽ ? ይሆን ፡ የጠየቅንሽ ፡ መልእክተኞች ፡ ሲመጡ ፡ ሁሉንም ፡ ተነጋግረን ፡ እንድንጨርስ ፡ አልናት ።

የሚፈጸመው ፡ እናንተ ፡ በተስማማችሁበትና ፡ በፈቀዳችሁት ፡ ጊዜ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ ያልኩት፡ አይደለም ። ቢሆንም ፡ ሐሳብ፡ ለመስጠት ፡ ያህል ፡ ሳሳስባችሁ ፡ የምወደው ፤ መማር ፡ ለመመራመር ፤ ከመሥራት፡ በፊት ፡ ከምን ፡ ተነሥቶ ፡ ወዴት ፡ እንደሚደርስ ፤ ምንስ ፡ ጥቅም ፡ እን ደሚሰጥ ፡ ለማሰብ ፡ ነው ።

እናንተ ፡ ውድ ፡ ወላጆቼ ፡ የብዙ ፡ ቤተሰብ ፡ ኃላፊነት ፡ አለባ ችሁ ፤ በአካባቢያችሁ ፡ የዕለት ፡ ራት ፡ የሌላቸው ፡ የናንተን ፡ እጅ ፡ አይተው ፡ የሚኖሩ ፡ ብዙዎች ፡ አሉ ። ይህ ፡ ከባድ ፡ ኃላፊነት ፡ እያለ ፡ ለኛ ፡ ድግስ ፡ ደግሶ ፡ በሽህ ፡ የሚቈጠር ፡ ሕዝብ ፡ መጥራት ፡ ጥቅሙ ፡ ለኛ ፡ ለእግቢዎች ፤ ወይስ ፡ ለምትድሩን ፡ ለናንተ ፡ ነው?

ለናንተ ፡ ነው ፤ በናንተም ፡ ምክንያት ፡ ለኛም ፡ ነው ፤ የሚባል ፡ ከሆነ ፡ በበኩሌ ፡ አልቀበለውም ። ለእኛ ፡ የሚታሰብ ፡ ከሆነ ፤ በፊታ ችን ፡ ብዙ ፡ የሚጠብቀን ፡ የብዙ ፡ ቤተሰብ ፡ ኃላፊነት፡ ስላለብን፤ ደስ፡ የሚለን ፡ ቤተሰባዊ ፡ ኑሮዋችንን ፡ የምናጸቁምበት ፡ ድጋፍ ፡ ብናገኝ ፡ ነው ።

በሠርጋችን ፡ ግን ፡ የማይቀሩ ፡ ቤተ ፡ ዘመዶችና ፤ የቅርብ ፡ ጐረ ቤቶች ፡ ብቻ ፡ ባሉበት ፡ መፈጸሙ ፡ በቂ፡ ነው ። ይህን ፡ ሐሳቤን ፡ ለኑሮ፡ ጓደኛነት ፡ የፈለገኝ ፡ እንደሚስማማበት ፡ አምናለሁ ። ፈቃዳችሁ ፡ ሆኖ ፡ ይህን ፡ ሐሳብ ፡ ብትቀበሉኝ ፡ እወዳለሁ ፡ አለች ፡ ቡርክት ።

የኛን ፡ ጋብቻ ፡ አስታውሰን ፤ ከተያየን ፡ በኋላ ፤ ልጂ ፡ በመሠ ረቱ ፡ ጋብቻውን ከተቀበልሽው ፡ ለሠርጉ ፡ ልናደርገው ፡ የሚገባ ንን ፡ እንቺ ፡ ከኑሮ ፡ ጓደኛሽ ፡ ጋር ፡ ተመካከረሽ ፡ የምንመራበትን ፡



ስጡን ፤ ያንቺን ፡ ፈቃድ ፡ እንከተላለን ። የኑሮ ፡ ጓደኛ ፡ ቤተሰቦችም ፡ ተመሳሳይ ፡ በሆነ ፡ ዝግጅት ፡ እንዲስማሙ ፡ አድርጊ ፡ አለቻት፡ ፀሐይ ።

ቡርክት ፡ አመስግናን ፡ ስለሠርጋቸው ፡ እኛ ፡ ባልነው ፡ ቀን ፡ ሊፈጸም ፡ እንደሚችል ፡ አረጋግጣልን ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ተመለሰች።

ስለሠርጉ ፡ ዝግጅት ፡ ስንነጋገር ፤ ቃል ፡ ኪዳን ፡ (ቀለበት) ከሠር ጋቸው ፡ በፊት ፡ ያድርጉ ፤ ወይስ ፡ በሠርጉ ፡ ጊዜ ፡ አብሮ ፡ ጣጣው ፡ ይለቅ ፤ ማንኛው ፡ ይሻል ፡ ይመስልኻል ፡ ብላ ፡ ጠየቀችኝ ፡ ፀሐይ ።

መልእክተኞቹ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ በመሠረቱ ፡ ጋብቻውን ፡ መቀ በላችንን ፡ ስናረጋግጥ ፤ ስለዚሁና ፡ ስለሠርጋቸውም ፡ ቢሆን ፡ ሙሽ ሮቹ ፡ በሚወስኑት ፡ እንዲፈጸም ፡ ለመልእክተኞቹ ፡ እናስገንዝባቸው። ወላጆች ፡ በዚህ ፡ ከተስማማን ፤ ጉዳዩን ፡ ለሙሽሮቹ ፡ እናስተላልፈዋ ለን ፡ ብዬ ፡ መልስ ፡ ሰጠኋት ።

በዚህ ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ እንዳለን ፡ መልእክተኞች ፡ በቀጠሮዋቸው፡ ከተፍ ፡ አሉ ። ከተሟላ ፡ ባልትና ፡ ጋር ፤ ደስ ፡ በሚያሰኝ ፡ አኳኋን ፡ መልእክተኞቹን ፡ ተቀበልናቸው ።

መልእክተኞቹ ፡ ለተላኩበት ፡ ምን ፡ መልስ ፡ እንደሚያገኙ ፡ ገና፡ ከማወቃቸው ፡ በፊት ፡ በአቀባበላቸው ፡ ብቻ ፡ ረኩ ። ወደዚያው ፡ የፀ ሐይ ፡ የቤት ፡ ባልትና ፡ ያቀናበረው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መጠጥ ፡ ተደርድሮ፡ ቀረበ ።

በግብዣው ፡ ላይ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ጣልቃ ፡ ሳናስገባ ፤ ስለጋብቻ ቸው፡ ሐሳባችንን ፡ ገለጥንላቸው ፤ አመስግነው ፡ ሄዱ ፡ ሽማግሌዎቹ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቡርክትና ፡ እጮኛዋ ፡ ዕምላዕሉ ፡ የጋብቻችን ፡ ቀን ፡ በናንተ ፡ ይወሰን ። ፍጥምጥሙም ፡ በዚያው ፡ ቀን ፡ አብሮ ፡ ቢከናወን ፡ እንወዳለን ፡ የሚል ፡ ሁለቱም ፡ የፈረሙበት ፡ ደብዳቤ ፡ ላኩልን ።

የነሱ ፡ ደብዳቤ፡ መነሻ፡ ሆኖ፤ወላጆቹ፡ ተገናኝተን፡ የጋብቻቸውን፡ ቀን ፡ ወሰንን ። ቡርክትና ፡ ዕምላዕሉ ፤ የጋብቻቸውን ፡ ቀን ፡ ሲያ ውቁ ፤ በድግስ ፡ ብዛት ፡ የሚደረገውን ፡ ለማስቀረት ፡ ቡርክት ፡ ለእ ጮኛዋ ፡ ለዕምላዕሉ ፤

ፍቅሬ ፤ ወደፊት ፡ የሚጠብቀንን ፡ ኑሮ ፡ በመተፋፈር ፡ የምንቋቋ መው ፡ ስላልሆነ ፤ በግልጥ ፡ እንጋገር ፡ ከተዋወቅን ፡ በጋብቻችንም ፡ ከተሳሰብን ፤ አሁን ፡ ድረስ ፡ በመተፋፈር ፡ ይሁን ፡ አላውቅም ፡ ፍሬ፡ ያለው ፡ እምብዛም ፡ አልተነጋገርን ።

የጋብቻችን ፡ ቀን ፡ ተወስንዋል ። ወላጆቻችን ፡ እኔ ፡ እበልጥ ፤ እኔ ፡ እበልጥ ፡ እያሉ ፡ የድግስ ፡ ውድድር ፡ እንዳያደርጉ ፡ መምሪያ ፡ ሐሳብ ፡ ብንሰጣቸው ፡ ምን ፡ ይመስልሻል፡ ብላ ፡ የጠየቀችበትን ፡ ደብ ዳቤ ፡ ግልባጭ ፡ ላከችልን ፤ ቡርክት ፤ ይህን ፡ ያህል ፡ ግልጥ ፡ በመ ሆኗ ፡ ተገረምን ።

ዕምላዕሉ ፡ ብልህ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፤ ቡርክት ፡ ፈረንጅ ፡ ሀገር ፡ ሄዳ ፡ የተማረችና ፡ ባለዲግሪ ፡ በመሆንዋ ፤ ራሱን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፤ ርስ ዋን ፡ በከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ያያት ፡ ኖሮ ፡ ውዶ ፡ ሆይ ፤ ከአንቺ ፡ የተሻለ ፡ አስተያየት ፡ ወይም ፡ ዕውቀት ፡ የለኝምና ፡ አንቺ ፡ ባልሽው፡ እስማማለሁ ፡ ብሎ ፡ ሲመልስላት ፡ እርሷ ፡ እንዳደረገችው ፡ ሁሉ፡ ግል ባጩን ፡ ላከልን ።

ርስዋን ፡ ከርሱ ፡ በላይ ፡ ዐዋቂ ፡ አድርጎ ፡ ራሱን ፡ ዝቅ ፡ አድ ርጎ ፡ እምላዕሉ ፡ በመናገሩ ፡ ወንድሜ ፡ ከእንግዲህ ፡ በኋላ ፤ ለኔ ፡ ካንተ ፤ ለአንተ ፡ ከኔ ፡ የሚቀርብ ፡ የለም ። ምንም ፡ ከእንደበታችን ፡ ሲነገር ፡ ይለያይ ፡ እንጂ ፤ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሲውል ፡ ሐሳባችን ፡ አንድ ፡ መሆን ፡ አለበት ። በምናደርገው ፡ ገለጣ ፡ ስሕተት ፡ ቢኖር ፤ አንተን ፡ ዐላዋቂ ፡ ወይም ፡ እኔን ፡ ዐዋቂ ፡ በማድረግ ፡ መወያየት ፡ የለብንም ። በዚህና ፡ በዚያ ፡ እገሌ ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ፡ ቢባል ፤ ሌላው ፡ ደግሞ ፡ በዚያና ፡ በዚህ ፡ ዐዋቂ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ በተፈጥሮም ፡ ሆነ ፤ በመማር ፡ የሚያውቀው ፡ የተለያየ ፡ ስለሆነ ፤ ያወቀውን ፡ ለማ ያውቀው ፡ ማካፈል ፡ ይገባል ፡ ያለችበትን ፡ ሁሉ ፡ ላከችልን ።

የልጆችንን ፡ ሠርግ ፡ መሰናዶ ፡ እየተመካከርን ፡ ስናሰናዳ ፤ በልጆ ችን ፡ አስተሳሰብ ፡ ልባችን ፡ በደስታ ፡ ተመስጦ ፡ ስሜታችንን ፡ ተገላ ለጥን ። የምወድህ ፡ መክብብ ፡ አለች ፡ ፀሐይ ፤ የልጆችን ፡ የቡርክት ፡ ጠቅላላው ፡ ሁኔታዋ ፡ በመላ፡ በሰውነቴ፡ የደስታ፡ ስሜት ፡ ፈጠረብኝ ። ከፈረንጅ ፡ ሀገር ፡ እንደመጣች ፤ ከናፍቆታችን ፡ የተነሣ ፡ ዓይንዋን ፡ በዓይናችን ፡ ለማየት ፡ ጓጉተን ፤ በከተማ ፡ ጓደኞቿ ፡ ለውጣን ፡ ዘግ



ይታ ፡ በመምጣቷ ፡ የተሰማን ፡ ኀዘን ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነበር ። ከመጣ ችም ፡ በኋላ ፤ ዓይንዋን ፡ በዓይናችን ፡ እይተን ፡ ገና ፡ ሳንጠግባት ፡ ወደ ከተማ ፡ ለመሄድ ፡ ከመነሣትዋም ፡ ይልቅ ፤ በንግግር ፡ እንዳሳዘነችንና ፡ ለሕይወታዊ ፡ ኑሮ ፤ የማይጠቅም ፡ ልማድ ፡ አይተንባት ፡ ነበር ።

ወንድሜ ፡ መውለድማ ፤ ሕይወት ፡ ያላቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ፍጥረ ታት ፡ ሁሉ ፡ ይዋለዱ ፡ የለም ፤ ዘር ፡ እንደማይዘራ ፡ የለም ። መሬትም የጣሉባትን ፡ ዘር ፡ ታበቅላለች ። የተጣራ፡ ፍሬ ፡ የምትሰጠው፡ መሬት፡ እንዴት ፡ ያለች ፡ ናት ። እንደምን ፡ ባለ ፡ እኳኋን ፡ የተያዘች ፡ ናት ። አረምና ፡ አራሙቻ ፡ የሌላት ፡ ንጹሕ ፡ ዘር ፡ ስትቀበል ፤ አብዝታ ፡ ጥሩ ውን ፡ ፍሬ ፡ የምትሰጣት ፡ ናት ። የሰውም ፡ ዘር ፡ ከንጹሕ ፡ ዘር ፡ ሰው ነት ፡ ላይ ፡ ያረፈ ፡ እንደሆነ ፡ የሚገኘው ፡ የሰው ፡ ፍሬ ፡ የተባረከ ፡ ይሆ ንና ፡ ለሀገርና ፡ ለወገን ፡ ተስፋ ፡ ይሆናል ።

ልጆች ፡ ለአባቶችና ፡ ለአረጋውያን ፡ የሚገባቸውን ፡ ክብር ፡ በመ ንፈግ ፡ ሞታቸውን ፡ እንጂ ፡ መኖራቸውን ፡ ባለመሻታቸው ፡ በምረቃ ፡ ፈንታ ፡ እርግማንን ፡ አትርፈዋል ።

መክብብ ፡ ከአሰብነው ፡ ኧረ ፡ ስንቱ ፡ ይወራል ። እንዲያውም ፡ ዝም ፡ ሳይሻል ፡ አይቀርም ። የአንድ አገር ፡ ክብሩ ፡ ታሪኩ ፡ ነው ። ታሪክ ፡ የሚባለው ፡ ባህሉና ፡ ልማዱ ፡ ቋንቋው ፤ ይህንና ፡ ይህን ፡ የመ ሰለው ፡ ሁሉ ፡ በአንድ ፡ ላይ ፡ ተደምሮ ፡ ነው ፡ ባለች ፡ ጊዜ ፤ ፍጆታ ፡ ሳልጠይቅ ፡ ፀሐይ ፡ ይህን ፡ ዓይነት ፡ አነጋገርና ፡ አስተሳሰብ ፡ ማንም ፡ አይቀበልም ።

እንዲያውም ፡ ለሥልጣኔ ፡ እርምጃ ፡ እንቅፋት፡ ስለሆነ፡ መጠረግ፡ አለበት ፡ እየተባለ ፡ በሙርኝ ፡ ለመጥረግ ፡ ይቃጣል ። አላርፍ ፡ ብለሽ ፡ መዘዝ ፡ ልታመጪ ፡ ነውና ፡ ዝም ፡ አይነቅዝም ፡ እንደተባለው ፡ ዝም ታው ፡ ሳይሻል ፡ የሚቀር ፡ አይመስለኝም ፡ አልኳት ።

ሳይተነፍስና ፡ ሳይናገር፡ዝም፡እንዳለ ፡ የሚቀር ፡ ሬሣ ፡ ነው፡እንጂ፡ ሕይወት ፡ ያለው ፡ መናገር ፡ አለበት፡፡ምን ፡ ማለትህ ፡ ነው ፡ መክብብ፡ አሁንስ ፡ አበዛኸው፡አለችና፡ ፀሐይ ፤ እስቲ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ የነበረውን ፡ አስታውስ ፤ አባትና ፡ እናት ፡ እንደምን ፡ ነበር ፡ የሚከበሩት ። በዕድሜ ፡ ትልቅ ፡ የሆነ ፡ ወንድም ፡ ወይም ፡ እኅት ፡ እንዴት ፡ ነበር ፡ የሚታፈሩ ።

አረጋዊ ፡ አባቶች ፡ ብቅ ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ ይደረግላቸው ፡ የነበረው ፡ አክብሮትና ፡ ከነርሱም ፡ ይገኝ ፡ የነበረው ፡ ምርቃን ፡ ይታወስሻል ? ዛሬ ፡ እነዚህን ፡ የመሰሉት ፡ ተጠልተው ፡ ለምን ፡ ቦታ ፡ ያጣብባሉ ፡ በቶሎ ፡ ሥፍራ ፡ አይለቁም ፡ እየተባሉ፤ ሕይወታዊ ፡ አቋማቸው ፡ ሳይ ፈለግ ፤ በድካማቸው ፡ ያቆዩት ፡ ሀብት ፡ ብቻ ፡ እየተፈለገ ፡ ሞት ፡ ሲፈረ ድባቸው ፡ ይዋላል ።

ፀሐይ ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ ልናገር ፡ እባክሽን፡ ብዬ፡ በመለመን ፤ አንዱ፡ በአንዱ ፡ ላይ ፡ የሚናገረው ፤ የሚያየው ፤ የሚሰማው ፤ የሚነቅፈው ፡ ውሎ ፡ አድሮ ፡ በያንዳንዱ ፡ ላይ ፡ የሚደርስ፡ ዕጣ፡ ነው ። ዛሬ ፡ የተጠሉ፡ ትናንት ፡ ወጣት ፡ ነበሩ ። ዛሬ ፡ ወጣት ፡ ነን ፡ ያሉ ፤ ነገ ፡ ጃጅተው ፡ በዛሬዎቹ ፡ የተናገሩት ፡ የነገዎቹ ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ሚናገሩ ፡ ለምን ፡ አያስቡም ?

መክብብ ፡ መልካም ፡ ተናገርክ ፤ የዛሬ ፡ ሰው ዛሬ ፡ የሚሠራው ፤ ዛሬ ፡ የተናገረው ፡ ነገ ፡ በእኔ ፡ ይደርሳል ፡ ካለማ ፤ ማንም ፡ በማንም ፡ ላይ ፡ ግፍና ፡ በደል ፡ ባልሠራም ፡ ባልተናገረም ፡ ነበር ። ይህ ፡ አይሆንም ። ሰው ፡ የፊቱንና ፡ በፊቱ ፡ ያለውን ፡ እንጂ ፡ የወደ ኋላውንና ፡ ወደፊት ፡ የሚመጣውን ፡ መቼ ፡ ያመዛዝናል ። በዚህ ፡ ላይ ፡ እንነጋገር፡ያልን ፡ እንደሆነ፡ የሰው ፡ ባርሕይ፡ከእንሳስ ፡ የማያንስ ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ።

እንስሳ ፡ ለሣር ፡ ግጦሽ ፡ የተለቀቀ ፡ እንደሆነ ፤ በፊቱ ፡ ያለውን ፡ አጣርቶ ፡ ሳይግጥ ፡ የሚታየውን ፡ ሁሉ ፡ ለማዳረስ ፡ ነጩት ፤ ነጩት ፡ እያደረገ ፡ ወደፊቱ ፡ ይገሠግሣል ። ከአዳረሰ ፡ በኋላ ፡ ረግጦ ፡ አልፎት፡ ወደነበረው ፡ እንደገና ፡ ይመለሳል ። ሰውም ፡ ለጊዜው ፡ ያንንም ፡ ያዝ ኩት ፤ ያንንም ፡ ያዝኩት ፡ ብሎ ፡ እዚያም ፡ እዚያም ፡ ረግጦ ፡ ያንንም ፡ ከዚያ ፡ ጋር ፡ አጋጭቶ ፡ ከተወሰነለት ፡ ላይ ፡ ሲደርስ ፡ እንደገና ፡ ይመ ለሳል ።

ይህ ፡ ዓለም ፡ የሚወጡበትና ፡ የሚወርዱበት ፡ የአቀበትና ፡ የቁ ልቁለት ፡ ዓለም ፡ መሆኑን ፡ የዓለም ፡ ሰው ፡ እያወቀ ፤ አንተም ፡ ተው ፤ አንተም ፡ ተው ፡ ቢሉት ፡ ለምን ፡ ብዬ ፡ እንነገሌ ፡ ከደረሱበት ፡ ደርሼ ፡ እመለሳለሁ ፡ እያለ ፡ ለውድድር ፡ ይሽቀዳደማል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ እቸንፎ ፡ ያለፈ ፡ የለም ። ሁሉም ፡ ሩጦ ፡ ሲደክመውና ፡ ሲታክተው ፡ ይመ ለሳል ።



በዘመናት፡ ኑሮው፡ ያለፉ፡ ስለነበሩበት፡ ዘመን፡ቢጠየቁ፤ ደስታው፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደነበረ ፡ ሲናገሩ ፡ ያስጐመጃሉ ። በዘመኑ ፡ ያለው ፡ ያለፉት ፡ ይህን ፡ ሳያዩትና ፡ ሳይጠቀሙበት ፡ አለፉ ፡ ብሎ ፤ ያለበትን ፡ ዘመን ፡ ካላየው ፡ ዘመን ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ አብልጦ ፡ ይገምታል ። ሆኖም ፡ ያለፈውም ፡ ሆነ ፡ ያለንበት ፡ ዘመን ፤ የሚጠላበትና ፡ የሚወ ደድበት ፡ ትዝታን ፡ ያኖራል ፡ እንጂ ፡ ፍጹምነት ፡ የለውም ።

እንዲያውም ፡ በታሪክ ፡ መስታወት ፡ ያለፈውን፡ ካለንበት፡ ዘመን፡ ጋር ፡ አተኩሮ ፡ ሲመለከቱት ፤ ያለፈውን ፡ በትዝታው ፡ እንወደዋለን ።

ያለፈውንም ፡ ሆነ ፤ የያዝነውን ፤ የሚመጣውን ፡ በአስተሳሰብ ፡ መነጽር ፡ ሲያዩት ፡ ወይም ፡ ሲመረምሩት ፤ ዘመናት ፡ አይለወጡም ፡ አይበዙም ፡ አያንሱም ፤ እነዚያው ፡ ናቸው ።

ይህ ፡ ከሆነ ፡ ያለፈው ፡ ዘመን ፡ የሚወደደው ፤ ያለንበት ፡ የሚጠ ላው ፡ በዘመናት ፡ መለዋወጥ ፡ ሳይሆን ፤ በሰዎች ፡ ተለዋዋጭነት ፤ የነ በረው ፡ ሲያልፍ ፤ ያልነበረው ፡ ሲተካ ፤ የዘመናት ፡ ክፋትና ፡ በጎነት ፡ የሚለካው ፤ በሰዎች ፡ መሆኑ ፡ ነዋ ፡ አልኳት ።

ሰው ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ መቼ ፡ መስክሮ ፡ ያውቃል ። ወደ ፡ ሌላ፡ ጠጋ አድርጎ ፡ ይናገራል ፡ እንጂ ። ዘመናት ፤ ዘመነ ፡ ብሉይ ፤ ዘመነ ፡ ሐዲስ፡ ተብለው ፡ ይጠራሉ ። ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ዘመነ ፡ ብሉይ ፤ ከልደቱ ፡ በኋላ ፡ ዘመነ ፡ ሐዲስ ። ዘመነ ፡ ብሉይን ፡ የፍዳ ፤ ዘመነ ፡ ሐዲ ስን ፡ የምሕረት ፡ ዘመን ፡ ይሉታል ። አራቱ ፡ ወንጌላውያን ፡ በየአ ራት ፡ ዘመናት ፡ ይሻሻራሉ ፤ ይፏፏማሉ ።

የሰው ፡ ልጅ ፡ በነዚህ ፡ ዘመናት ፡ መካከል ፡ በብዛት ፡ ይመጣል ፤ ይሄዳልም ። በብዛት ፡ የታየው ፡ በዘመናት ፡ መካከል ፡ ሲጠፋ ፡ ሌላ ውን ፡ በብዛት ፡ ይተካል ። ወንጌላውያን ፡ በየዓመቱ ፡ ሲለዋወጡ ፡ የተሿሚው ፡ ወንጌላዊ ፡ ዘመን ፤ የሰላምና ፡ የደስታ ፡ ዘመን፡ እንዲሆን፡ ሰዎች ፡ መልካም ፡ ምኞታቸውን ፡ ይለዋወጣሉ ። እንደ ፡ እውነቱ ፡ ከሆነ ፡ በዘመናት ፡ መካከል ፡ ሰላም ፡ እየኖረ ፡ የሰው ፡ ልጅ፡ የመኖር፡ ዘመኑን ፡ በተድላና ፡ በደስታ ፡ ሊያሳልፍ ፡ የሚችለው ፡ ሰላምን ፡ የሚ ሿት ፡ የሰላም ፡ ሰዎች ፡ ሲኖሩ ፡ ነው ።

ናዚስትና ፡ ፋሺስት፡ ዓለምን ፡ ለመግዛት ፡ ተነሣሥተው ፡ በተባ በሩበት ፡ በሁለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ የስንት ፡ ሰዎች ፡ ደም ፡ በከ

ንቱ ፡ ፈሰሰ ። ያ ፡ የጥፋት ፡ ዘመን ፡ አሁንም ፡ ከሰዎች ፡ ፊት ፡ ገና ፡ አል ጠፋም ። እሳቱ ፡ የገረፋቸው ፡ ሲያስታውሱት ፡ ከዓይናቸው ፡ ዕንባ ፡ ይረግፋል ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ያልነበሩ ፡ ጥፋቱን ፡ በታሪክ ፡ ቢረዱትም ፡ መከ ራው ፡ የነካቸውን ፡ ያህል፡ ቍስሉ ፡ ስላልተሰማቸው ፤ ሦስተኛው ፡ የዓ ለም ፡ ጦርነት ፡ ተነሣሥቶ ፡ የሰው ፡ ዘር ፡ ከምድረ ፡ ገጽ ፡ እንዲጠፋ ፡ የጦርነት ፡ እሳት ፡ እንዲቀጣጠል ፡ ማገዶውን ፡ አንዱ ፡ ሲያቀብል ፡ ሌላው ፡ እሳቱን ፡ ለመለኮስ ፡ ይጣደፋል ።

የጥፋቱ ፡ ዋዜማ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ድምፁን ፡ እያ ስተጋባ ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ ጥፋት ፡ ያበስራል ። ለጥፋት ፡ ምክንያት ፡ የሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡ እንደመኖራቸው ፡ ለሰላምም ፡ የሚጥሩ ፡ የሰላም ፡ ሰዎች ፡ በመኖራቸው ፡ እየሸመገሉ ፡ ዓለምን ፡ በማስታመም ፡ ይዘው ታል ፡ እንጂ ፤ ከሕመሙ ፡ ፍጹም ፡ ፈውስ ፡ እንዲያገኝ ፡ ለማድረግ ፡ አልቻሉም ።

በጦርነት ፡ እሳት ፡ የተቀጣው ፡ የሰው፡ ልጅ ፡ ድምፁን ፡ በሰማ፡ ጊዜ ፡ እየበረገገ ፡ ፍጹም ፡ ፀጥታ ፡ ሳይኖረው ፤ ዕርቅ ፡ ሲሰማ ፡ ደስ ፡ እያለው ፤ ዕርቁ ፡ ሲፈርስ ፡ እየተደናገጠና ፡ እያዘነ ፤ ጆሮውን፡ ለወሬ፡ ከፍቶ ፡ የሚመጣውን ፡ ያዳምጣል ፡ አለች ፡ ፀሐይ ።

ፍቅሬ ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ በዚህ ፡ ዓለም፡ ላይ ፡ የሚያመጣውን ፡ ጣጣ፡ የተመራመርን ፡ እንደሆነ ፡ የውቅያኖስን ፡ ባሕር ፡ ያህል፡ ሰፍቶ ፡ ይታ ያል ። ለሰላምም ፡ ሆነ ፡ ለጥፋት ፡ ምክንያት ፡ የሚሆኑ ፡ ሰዎች፡ እንጂ፡ ዘመናት ፡ አይደሉም ፡ ያልሽው ፡ ትክክል ፡ ነው ።

ዓለም፡ ከተፈጠረ፡ዘመን፡ ከተቈጠረ ፡ ጀምሮ፡ በዓለም ፡ ላይ፡ የተፈ ራረቁት ፡ የሰላምና ፡ የጥፋት ፡ ዘመናት ፤ የተመሠረቱት፡በሰዎች፡አነሣሽ ነት፡መሆኑን ፡ በታሪክ ፡ የተመሰከረ ፡ ነውና ፡ ይህ ፡ በኛ ፡ አስተሳሰብ ፡ ደኅንነት ፡ የሚያገኝ ፡ ባለመሆኑ ፡ እንለፈው ፡ ብዬ ፡ መለስኩላት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የልጃችን ፡ የጋብቻ ፡ ቀን ፡ ስለደረሰ ፤ ስለማናቸ ውም ፡ ዝግጅት ፡ ቡርክትን ፡ ጠርተን ፡ እንድንመካከር ፡ ፀሐይን ፡ አስታወስኳት ።



ውዴ ፡ ሆይ ፤ አልነገርኩህም ፡ እንጂ ፡ ለሥርጓ ፡ ወር ፡ ሲቀረው ፡ ቡርክት ፡ ልትመጣ ፡ ልካለች ፡ አለችኝ ፡ ፀሐይ ። ይህማ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ተባብለን ፡ የበኩላችንን ፡ ስናዘጋጅ ፡ ቡርክት ፡ ከተፍ ፡ አለች ።

ከአክብሮት ፡ ጋር ፡ ፍቅራችንን ፡ ባነጋገር ፤ በአስተያየት ፤ በአስ ተሳሰብ ፡ አሳይተን ፤ ያደረግነውንና ፡ የምናደርገውን ፡ አማከርናት ። በሆነው ፡ ሁሉ ፡ ደስታዋን ፡ ስትገልጽ ፤ አያሌ ፡ ገንዘብ ፡ ብታወጡ ፡ ከሚያስደስተኝ ፡ ያሳዝነኛል። ከማን ፡ አንሼ ፡ እየተባለ ፡ የሚደረገው፡ እንደማይጠቅም ፡ ካሁን ፡ ቀደም ፡ ገልጬላችኋለሁ ። አሁንም ፡ የሚ ደረገው ፡ ዝግጅት ፡ ለቅርብ ፡ ጐረቤትና ፡ ለቤተ ፡ ዘመዱ ፡ በሚበቃ ፡ ተመጥኖ ፡ እንጂ ፡ ከዚህ ፡ ቢያልፍ ፡ ከንቱ ፡ ውዳሴ ፡ ይሆናል ።

ልጄ ፡ ሆይ ፤ አልኩና ፡ የኛ ፡ ጋብቻ ፡ የተፈጸመው ፡ በጠባብ ፡ መሰናዶ ፡ ነበር ። የበኸር ፡ ልጃችን ፡ እንደመሆንሽ ፡ በሰፊው ፡ ማስ ባችን ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ አንቺ ፡ ዋጋ ፡ ካልሰጠሽው ፡ ሐሳ ብሽን ፡ ተቀብለን ፡ በመጠኑ ፡ ይዘጋጃል ፡ አልኳት ።

ልጃችን ፡ እንደተመኘችው ፡ በመጠነኛው ፡ ዝግጅት ፡ ከተሠ ረገች ፡ በኋላ ፡ ለንብረት ፡ ማቋቋሚያ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የገንዘብ ፡ ስጦታ ፡ አደረግንላት ። በቅርብ ፡ ያየ ፡ በሩቅ ፡ የሰማም ፡ አመሰገነን ።

በልጃችን ፡ ጋብቻ ፡ ደስ ፡ አለን ፤ እንደዚህ ፡ ከሆነ ፡ ምን ፡ አለ ፡ ብዙ ፡ ቢወለድ ፡ ብለን ፡ ተነጋገርን ። በተጋቡ ፡ በዓመታቸው ፡ ቡር ክት ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወለደች ፤ የልጅ ፡ ልጅ ፡ ዓይተን ፡ አያት ፡ ሆን ። ከዚህም ፡ ደስታ ፡ የተነሣ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ በአልጋችን፡ ላይ፡ ጋደም ፡ ብለን ፡ ስንጨዋወት ፤ እያንዳንዳችን፡ ለወላጆቻችን ፡ አንድ፡ መሆናችንና ፡ በጋብቻ ፡ ሥርዓት ፡ ተገናኝተን ፡ ሁለት ፡ ከሆን፡ በኋላ፡ ከአብራካችን ፡ አራት ፡ ልጆች ፡ ተገኝተው ፡ ከራሳችን ፡ ጋር፡ ስድስት፡ ቤተሰብ ፡ መድረሳችንና ፡ ከልጅ ፡ ልጆቻችን ፡ ጋር ፡ ሰባት ፡ ስንሆን ፡ በትውልድ ፡ የተባዛን ፡ ቤተሰብ ፡ በመሆናችን ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰ ሰገን ።